# ፯

# ወጣቱ መንፈሳዊ ሠራዊት

ጥበቡ በአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ታዋቂ የሳይንስ ተማሪ ሆኖ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት፣ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሊጠቅመው የሚችል ታላቅ መንፈሳዊ እውቀት ተገልጦለት ነፍሱ አሁን በፈንጠዝያ ተሞልታለች። ከእውቀት ሁሉ የከበረ ታላቅ እውቀት እግዚአብሄርን ማውቅና ማምለክ እንደሆነ ገብቶት፣ በዚህ የዕረፍቱ ወቅት ነፍሱ የአምላክዋን ቃል በማወቅ ሥር እንድትሰድድ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከገሃነም ደጆች ስላስመለጠው አምላኩና ለሰው ልጆች ሁሉ ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ለቤተሰቦቹና ለጓደኞቹ እንዲሁም ለሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ፣ ማውራትና መመስከር የጥበቡ የእለት ተግባሩ ሆኗል። የጥበቡ አባት መምሬ ኃይለሥላሴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ጥበቡ ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳለ ነበር። እናቱ ወ/ሮ ፀዳለ ግን ዲያቆን ይወጣዋል ብለው የጠበቁት ልጃቸው ከጥቂት ቀናት ወዲህ ለሰው ሁሉ የሚናገረው የኢየሱስና በእርሱም አዲስ ልደትን የማግኘት ታሪክ አልጣማቸውም። ልጃቸው ጥበቡ ጠባየ መልካምና ትጉ ልጅ እደነበረ እናቱ ያውቃሉ። ስለዚህ እርሳቸው እስከሚገባቸው ድረስ ጥበቡ ምን ኃጢአት ሰርቶ ነው በርሱ ላይ የመንግሥተ ሰማይ ደጅ የሚዘጋበት? ስለዚህ ጥበቡ በዚያን ሰሞን፡-

- "ሰው ሁሉ በድሏል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎታል"...
- "ከገሃነም መዳን በሌላ በማንም የለም። ከዘላለም እሳትና ስቃይ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከኢየሱስ በቀር ከሰማይ በታች ሌላ የለምና"

እያለ ላገኘው ሰው ሁሉ በድፍረት የሚናገረው ነገር አልገባ ብሏቸዋል።

ጥበቡ ግን የሰው ልጅ ሕይወት ክቡር መሆኑ ግልጽ ሆኖለታል። የአዳምን ዘር ለማዳን የሰማይና የምድርን ጌታ ልዑል እግዚአብሔርን ውድ ዋጋ አስከፍሎታል። ስለዚህ በፈጣሪው ፊት እንዲህ ክቡር የሆውን ሕይወት ከእንግዲህ በዘፈቀደ ወይንም በጭፍን ሊመራው እንደማይገባው አውቋል። የቀለም ትምህርቱን ለመረዳት ብሩህ የነበረው የጥበቡ አእምሮ፣ ጥልቅ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና መንፈሳዊ ምሥጢር ለመረዳትም ብሩህ ሆኖለታል።

የክረምቱ ዕረፍት አልቆ ትምህርቱን ለመቀጠል ጥበቡ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ፣ ይህን አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት የተቀዳጁ መሰል የዕድሜ እኩያዎቹን በማግኘቱ ይበልጡን ደስ ተሰኘ።

በባህሪያቸውና በሕይወት አመለካከታቸው ስለሚመስሉት፣ በጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት በአዲሱ የሕይወት ጎዳና በቁርጠኝነት ለመጓዝ ብቸኛ አልሆነም። ይህ በወጣቶች መካል የተነሳው ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንደ ሰደድ እሳት በአዲስ አበባም ሆነ በመላ ኢትዮጵያ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መስፋፋት ጀምሯል። በሕዝባችንና በዘመኑ በነበረው በኃይለሥላሴ መንግሥት እንደ እንግዳ እንቅስቃሴም ተቆጥሯል። አንዳንዶች "ጴንጤ" የሚል ስም አውጥተውለታል። ሌሎችም በመርከብ ተጭኖ የመጣ "መጤ" ሃይማኖት ብለው አውግዘውታል። የካህኑ ልጅ ጥበቡ ኃይለሥላሴ ግን በዚህ ሁሉ አልተደናገጠም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የነቢያትና የሐዋርያትን እምነት መያዙን በሚገባ ተረድቷል። ሌላ የባዕድ እምነት አንፀባራቂ፣ እንዳልነበረ፣ ስለራሱም ሆነ በዚያ በመንፈስ ቅዱስ እሳት ስለተገበኘው ወጣት ትውልድ ሁሉ፣ ጥበቡ ጠንቅቆ ያውቃል።

ናዝሬት ከተማ አፄ ገላውዴዎስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የሐረር የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣ እንዲሁም የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ በተመሳሳይ መንገድ በእግዚአብሔር ጉብኝት ተጎብኝተዋል። ከ1956 ዓ.ም. ጀምሮ በምድራችን ላይ የነፈሰው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የብዙ ወጣቶችን ሕይወት ነክቷል።

ልክ በሐዋርያት ዘመን እንደነበረው ታላላቅ ተአምራቶች ይደረጋሉ። እውነትን የተጠሙ ወጣቶች ሕይወት ይለወጣል። ለቤተሰብና ለሰፈር ለትምህርት ቤትና ለከተማ ያሸነፉ ዓመለ ክፉ ወጣት ዱርዬዎች ዓመለ ሸጋ ሆነዋል። የታወቁ ወንበዴዎች እንገታቸውን ሰብረው ታዛገኙችና ትሁቶች ወጥቷቸዋል። ሌቦችና አጭበርባሪዎች የነበሩ ታማኞችና ለአገር ለወገን የሚጠቅሙ ሆነዋል፤ ጠጪዎችና ሰካራሞች ሲጋራ አጫሾችና ዝሙተኞች የነበሩ ብዙዎች ለዓመታት ከገዛቸው ከሱስ የባርነት ቀንበር ነፃ ወጥተዋል። በሽተኞች ተአምራዊ ፈውስ ተቀዳጅተዋል። እርኩሳን መናፍስት መሸገውባቸው ከቁጥጥራቸው ሥር የነበሩ የሰይጣን እስረኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ነፃ ወጥተዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሐዋርያት በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ወቅት እንደሆነው ዓይነት እነዚህም ወጣቶች በተመሳሳይ ልምምድ ውስጥ አልፈው በአዲስ ልሳን ተናግረዋል። በታላቅ መንፈሳዊ ሥልጣንና ድፍረት፣ በፍቅርና በእውነት በሕይወታቸው የሆነውን መስክረዋል።

በአፋቸው ምስክርነትና በህይወታቸውም በሚታየው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ምክንያት ወጣቱ መንፈሳዊ ሠራዊት በምድራችን ቁጥሩ እየጨመረ መጣ። እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ የኃጢአትን ሥር ነቃቅሎ፣ የወጣቶችን ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወረሰው። እኔና ጥበቡም የዚያ ወጣት መንፈሳዊ ሠራዊት አባላት ነበርን። ይህን በታላቅ ፍጥነት በመገዝመት ላይ የሚገኘውን አስደናቂ የእግዚአብሔር ሥራ ግን፣ ምድራችንም ሆነች ሕዝባችን እልል ብለው አልተቀበሉትም።

የቀዳማዊ የኃይለሥላሴ መንግሥት ከባለሥልጣኖችና በጊዜው ከነበሩት የሃይማኖት ሰዎች ጋር በመሆን፣ በወጣቱ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረ። እሳቱን ለማዳፈን ሰይጣን በጊዜው በሥልጣን ላይ የነበሩትን ሰዎች በመጠቀም ብዙ ጥረት አደረገ። በሬድዮ በቴሌቪዥንና በጋዜጣዎች ሁሉ መሰረተ ቢስ የሆኑ በሃሰት የተሞሉ ዜናዎችን በማሰራጨት፣ ለተወሰነ ጊዜ እውነቱ ከሕዝባችን እንዲሰወር ተደረገ። ወላጆችንና ልጆችን ሊያለያይ በሚችል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ሕዝባችን ተሞላ። ስለዚህም በገዛ ልጆቹ ላይ ጥላቻንና ውግዘትን ያዘለ ስደት እንዲያካሂድባቸው፣ አሳልፎም ለእስር ቤት እንዲሰጣቸው አስገደደው። ምንም እንኳ ንጉሡ "አገር የጋራ ሃይማኖት የግል ነው" የሚል አባባል ቢኖራቸውም፣ የቤተክህነት መሪዎችንና የሌሎቹንም ዕውር ሃይማኖታዊ ቅንዓት ግፊት ሊቋቋሙ አልወደዱም፤ ወይንም አልቻሉም። ስለሆነም የጸሎት ሰብሰባዎቻችንን ለመበታተን ፈቀዱላቸው።

የጸሎት ቤቶቻችን መሪዎች በመስፋፋት ላይ የሚገኘውን ይህን ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ፣ መንግሥት ሕጋዊ ፈቃድ ሰጥቶአቸው እንዲቀጥሉ በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። ከአንዴም ሁለት ሶስቴ አፄ ኃይለሥላሴ ፊት አቤቱታ ቢያቀርቡም የንጉሡ ቅን ፍርድ የሰማይ ያህል ራቀ። ከአምስት በላይ ሆነን በአንድ ስፍራ ወይንም ቤት መገኘት በሕግ ባልተፈቀደ ስብሰባ እንደመገኘት ተቆጥሮ እንዲከለከል ተደረገ። ያ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ የነበረው ትልቁ ጸሎት ቤት በ1960ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ተዘጋ። በአዲስ አበባ ውስጥና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙት የጸሎት ጉባዔዎቻችን ሁሉ እንዲዘጉ፣ ተሰብስበው ቢገኙ ታፍሰው እንዲታሠሩ ትዕዛዝ ወጣ። ስለዚህ የጸሎት ቤቱ መሪዎቻችን ሕዝቡን አስታውቀው ስብሰባዎቻችንን ለማቆም ተገደዱ።

ንጹሕ ወንጌልን በማመንና ያላመኑም እንዲያምኑ በመስበክ የአማኞች ቁጥር እያደገ መሄዱ መልካም እንጂ ክፉ አልነበረም። በተለያየ ሱስ፣ በሽታና የአጋንንት እስራት የታሰሩትን እግዚአብሔር በታላቅ ክንዱ ነፃ ማውጣቱም "ድንቅ" ሊባል በተገባ ነበረ። የብዙ ነፍሰ ገዳዮች ሌቦችና ወንበዴዎች ሕይወት በተአምር መለወጡ፣ ለምድራችን የምሥራች ዜና ሊሆን ይገባውም ነበረ። በተቃራኒው ግን ይህ ታላቅ ሥራ እንዲተጓጎል መደረጉ፣ ምዕመኑን እጅግ አሳዘነው። ጥበቡና እኔም እንባ አውጥተው ከለቀሱት በአምላካቸው ፊት ስለ ሕዝባችን፣ በሥልጣንም ላይ በጊዜው ስለነበሩት ሁሉ ምሕረት ከለመኑት መከከል ነበርን። የጸሎት ቤታችን መሪዎች የመንግሥትን ሕጋዊ ፈቃድ ለማግኘት ያደረጉት ጥረት፣ የተስፋ ጭላንጭል የሚታይበት አልሆነም።

ከጥቂት ወራት ጥበቃ በኋላ ከባህር ዳር ፖሊ ቴክኒክ ተመርቀው የመጡና አዲስ አበባ ሥራ የያዙ አራት ወጣቶች፣ ደጃች ውቤ ሰፈር በተከራዩበት መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የጸሎት ፕሮግራም ማድረግ ጀመሩ። እነዚህ አራት የፖሊቴክኒክ ምሩቆች ወንድም ፍቃዱ አፍጋ፤ ወንድም ደሜ ተራሞ፣ ወንድም ኃይሌ ከብረአብ እና ወንድም ዘላለም ተስፋዬ ነበሩ። ያ የተበተነው መንጋም በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደዚያች ቤት መሰባሰብ ጀመረ። በየሰንበቱም ጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ ተጀመረ። በዚያ በትልቁ ጸሎት ቤት ይመላለስ የነበረው ታላቁ የእግዘአብሔር ክንድ፣ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ታላላቅ ሥራን መሥራቱን ቀጠለ። ቤቷ እየጠበበች ሰዉ ቁጥሩ እየጨመረ፣ የታሰበውም የመንግሥት ፈቃድ ተስፋ እየመነመነ ሄደ። መሪዎቻችን ተስማሙና አንድ ትልቅ አዳራሽ ያለው ቤት እዚያው አካባቢ ተከራይተው ሥራው ወደዚያ ተዘዋወረ። ያ ጸሎት ቤት የሚታወቀው "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" /ቻፕል/ በመባል ነበር።

የ"ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" አገልግሎትም በስፋትና በትጋት እስከ1962 አጋማሽ ተካሄዷል፤ የ"ሕጋዊ ፈቃድ" አለመኖር በመሪዎቻችን ልብ አሁንም ስጋትን አስከተለ። ሊመጣ የሚችለውን ስደት ከወዲሁ መከላከል ይሻላል በሚል፣ መሪዎች የ"ጊዮርጊስ ቻፕሉን" አገልግሎት ለማቆም ወሰኑ። የምዕመኑ ኀዘንና የልብ ስብራት ትዝ ይለኛል! ብዙዎቻችንን የእግዚአብሔርን ፊት አጥብቆ ወደመፈለግ፣ ወደጠለቀ የእንባና የጸሎት ሕይወት ውስጥ ከቶናል። የ"ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ሲነሳ ወደ ብዙ ትዝታ ይወስደኛል። ለሰዓታት በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት መሆንን የተማርኩበት የከበረ ስፍራ ስለሆነ። ከአራቱ የፖሊቴክኒክ ወንድሞች መኻል ወንድም ፈቃዱ አፍጋአ (አሁን ፓስተር) እና ወንድም ደሜ ተራሞን (አሁን ኢንጂኔር) ከፊት ይልቅ ቀርቤ ያወቅኋቸው እዚህ ጸሎት ቤት ውስጥ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ጥበቡ ኃይለሥላሴን ያየሁት "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ነው። ለረዥም ሰዓታት ያለማቋረጥ መጸለይን የተለማመድኩት፣ "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" እነዚህ ወንድሞች

በእግዚአብሔር ፊት የሚያሳልፉትን ጊዜ በማየት ነው። ወንድም ፈቃዱ መኖሪያው እዚሁ ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ውስጥ ነበረ። በዚህ ወቅት ወንድም ደሜ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ትምህርቱን ቀጥሏል።ከወንድም ፈቃዱ ጋር አብረው ይኖሩ በነበረበት ወቅት፣ መንፈሳቸውንና ልባቸውን ያስተሳሰረ የጸሎት ሕይወት ልምምዳቸው ግን ቀጥሏል። ጥቂት ሳይቆይ ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ውስጥ ከአምልኮ ሰዓት ውጪ፣ መንፈስ ቅዱስ ወደእነዚህ ሰዎች የጸሎት ሕይወት ቀለበት ውስጥ፣ አንድ በአንድ ሰዎችን እየጠለፈ ያስገባ ጀመር። ጥበቡ ኃይለሥላሴ፣ ገረመው ዴቢሳ (ኢ.ጂኔር) ፍቅሩ ታፈሰ (ወንጌላዊ) ተቀባ አባይነህ (ፓስተር) "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት"ን ከሚያዘወትሩ የጸሎት ሰዎች ነበሩ። ከእነዚህ በተጨማሪ አልፎ አልፎ ከደብረዘይት እንደ እንካሳዬ ደገፋና አበበ ቡኔ እንዲሁም ከአቃቂና ከአካበቢዋ ለጸሎት የሚመጡ ወገኖች እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ይካሄድ የነበረው የተጧጧፈ ጸሎትና ኃይለኛ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴም ትዝ ይለኛል። ከዚህ ስፍራ የተለኮሰው እሳት ወደአቃቂ ነፋስ ስልክና አዋሬ ዘመተ።

የጥበቡ ኃይለሥላሴም ሕይወት በብዙ የተቀረጸው፤ "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ውስጥ ነው። "ለእግዚአብሔር ሥራ ካልወጣሁ" እያለ ከዩኒቨርሲቲ መኝታውን ጥሎ በጸሎት ሲታገል የሚያድረው "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ነበር። ትልልቅ የሕይወቱን መመሪያዎች ከእግዚአብሔር በራዕይ በድምጽና በነብያትም ጭምር የተናገረው እዚህ "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ውስጥ ነው። በጸሎት ሜዳ ውስጥ ሳሉ የሰድሜ ልክ ወንድማማችነት ከእነ ፓስተር ፈቃዱ እና እህት አማረች ተሰፋዬ (የፓስተር ፈቃዱ ባለቤት) ጋር የመሰረተው እዚህ ጸሎት ቤት ውስጥ ነው።

ከጥበቡና አብረውት በጸሎት ከሚተጉት ወንድሞችና እህቶች ጋር በብዙ የተለያየ ጊዜ ጸልየናል። ስለዚህም ከመንፈሳዊ ረሃብና ጥማት በስተቀር ሌላ ዓላማ የሌላቸው የጸሎት ሰዎች መሆናቸውን በብዙ መንገድ ስለመሰከርኩ ጥበቡ አብሯቸው ከሚተጋ ወገኖች ጋር እኔም ለመጸለይ ነጻነት ስለሚሰማኝ ልቤ ሁልጊዜ ፍቃደኛ ነበር። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት እግዚአብሔር በሚደንቅ የጸሎት ሕይወት ከጥበቡ ጋር ያቆራኛቸው ሰዎች ነበሩ። ጥበቡ በሕክምና ትምህርት አብረውት ይማሩ የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ሃብቴ እና ዶ/ር ሚልክያስ ሻሜቦ የትምህርት ጓደኞቹ ብቻ ሳይሆኑ ከጸሎት ጓደኞቹም መኻል ነበሩ። "የአክሌሽያ ተነሽ" አገልግሎት መሥራችና መሪ የነበረው ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ አገልገሎቱ ለምድራችን ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባለው ሁኔታ ለክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በረከትና መነቃቃት የነበረ ሰው ነው። ዶ/ር ብርሃኑ በሕክምና ፋኩልቲ ዲንነት ሲሠራ ሳለ በሕይወቱ ያለው መለኮታዊ ጥሪ አመዝኖ በፍቃዱ የዲንነት ሥራውን ለቆ የሙሉ ጊዜውን አገልግሎት በአምላኩ ፊት አበርክቶ አልፏል። ዶ/ር ሚልክያስ ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑን ተክቶ የህክምና ፋኩልቲው ዲን የነበረ በጣም የቅርብ ጓደኛችን (ሚዜያችን) ነበር። እነዚህ ለልባችን እጅግ ቅርብ የነበሩ ሶስቱ ጓደኛሞች፣ ቀድመውን በሰማያዊው ስፍራ በእግዚአብሔር እቅፍ ውስጥ የሚገኙ የማንረሳቸው ወንድሞቻችን ናቸው።

****

## "ከመታሰር እንዴት እንድላለሁ"

የእግዚአብሔርን ፊት ለመፈለግና ከእግዚአብሔር ኃይል ለመቀበል የነበረንን ጉትት አልረሳውም!! የግሌን ባወራ፣ ከጥቂት እህት ጓደኞቼ ጋር የረዥም ጊዜ ጾም ጸሎት ያዝን። ቤተሰቦቼን ከዚያ የአንደርቢ ምትሃት በሚያስደንቅ ትድግና ያዳናቸው ወቅት ነው። መንፈሳችን የእግዚአብሔርን

ነገር የመራብ የመጠማቱ ብዛት አንዳንዶቻችንን ወደ ረዣዥም ጾምና ጸሎት ውስጥ አስገብቶናል፤ አስታውሳለሁ ከእነዚህ እህቶቼ ጋር እንደ በፈሳሽ (ሻይ/ውኃ) ጾምና ጸሎት ጀምረን ዘጠኝ ቀን አሳልፈናል። ያም ስላልበቃን ከመሃከላችን ሶስታችን፣ ሁለቱ እህትማማች መምህራን (ስንቅነሽና ውድነሽ አዘነ ) እና እኔ ቀጣይ ፕሮግራም ነበረን። ስንቄና ውዴ በክረምቱ ትምህርት ቤት ዝግ ስለሆነ ላሰብነው ዓለማ ይመቻቸዋል። እኔ ደግሞ ከሥራዬ ያጠራቀምኩትን የዓመት ፈቃድ (ከአርባ ቀን በላይ!) ወሰጃለሁ። በዚህ በጀመርነው የረዥም ጊዜ ጾም ጸሎት ከቤታችንና ከከተማችን ርቀን ለመውጣት ፈለግን። ወንድም ፍቃዱ አፍጋ እና ባለቤቱ እህታችን አማረችን ለመሄድ አሰብን። ያኔ የሚኖሩት ለቀምት አጠገብ ቲንፋ ውስጥ ነው። እዚያ መኖሪያቸውን አድርገው አካባቢውን በወንጌል ይደርሳሉ። የጸሎት ሰዎች ስለሆኑና ስለምንቀራረብ መረጥናቸው። አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜም አብረናቸው ብዙ ስላሳለፍን ልባችን ወደነርሱ ለመሄድ ተነሳ። እንዲህ ያለውን የጸሎት ጥማታችንን የምንወጣው እነሱጋ በመሰንበት ነው ተባባልን። ጊዜው ሐምሌ 1964ዓ.ም. ነው።

እነወንድም ፈቃዱም ደስ እንደሚላቸው ስለገለጹልን የቀሩትን ጓደኞቻችንን ተሰነባብተን ወደ ነቀምት ሄድን። መንገዱን ሊያሳዩን ከሚጠብቁን ወንድሞች ጋር የእግር ጉዞአችንን ወደ ቲንፋ ተያያዝነዋ! ይገርመኛል አሁን ሳስበው የነበረን ኃይልና ጸጋ! ምናልባት በሕይወታችን በእግር የተጓዝነው (ምግብ ሳይበላ በቆየ አንጀት)፣ ረዥሙ እሱ ሳይሆን አይቀርም! ሦስት የከተማ ወጣት ሴቶች የእግዚአብሔርን ፊትና ኃይል ፍለጋ!!

ጾም ጸሎታችንን ለሀያ ምናምን ቀናት ቀጠልን። እኛ እዚያው ወለጋ እያለን ነሐሴ 21 ቀን 1964ዓ.ም. በቤተክርስቲያናችን ላይ ትልቁ ስደት አዲስ አበባ ውስጥ ተነሳ። ናዝሬት ትምህርት ቤት አጠገብ ከነበረው ጸሎት ቤታችን ለሰንበት አምልኮ የተሰበሰቡትን ወገኖቻችን በሙሉ ታፍሰው ታስረዋል። ከሦስታችን መሀል እህታችን ውድነሽ፣ ከፌደራል ትምህርት ቤት በመምህርነት ሥራ ለመጀመር የኢንተርቪው ቀጠሮ ስለነበረባት ውዴ አዲስ አበባ ጥቂት ቀናት ቀድማን ተመለሰች።እኔና ስንቄ ፕሮግራማችንን ጨርሰን ከነቀምት ስንመለስ አዲስ አበባ ውስጥ የስደቱ ወላፈን ብዙ ወገኖቻችንን አግኝቷቸው ነው የጠበቀን። ጓደኛችን ሐዳስ ወልደአብ ያን ሐር የመሰለ እስከ ወገብ የሚደርስ ረዥም ጸጉሯን፣ ሌሎቹንም የቅርብ ጓደኞቻችን ወንድሞችና እህቶች ጸጉራቸውን በደረቁ እየላጯቸውና እየፈረዱባቸው እንደ ወንጀለኞች ወህኒ ጥለዋቸዋል። ከእስር ቤት ውጪ የነበሩት ወገኖች በየግሩፑ እየሆኑ ለእስረኞቹ ወገኖቻችን የሚቀርበውን ስንቅ ማዘጋጀት ጀምረው ሳለ ነው እኔና ስንቄ አዲስ አበባ የተመለስነው። ስለዚህ ወዲያውኑ ወደስንቅ ዝግጅቱ ሥራ ተሰማራን።

እኔ ግን እረፍቴን ሳልጨርሰው በቀረኝ አንድ ሳምንት ሌላ ሚሽን አለኝ። ወደ አጋሮ ጂማ የመሄድ። በአንደርቢው ጊዜ እግዚአብሔር ከታደጋቸው ቤተሰቦቼ መኻል አንዷ ወደሆነችው፣ ወደ አክስቴ እትዬ ሙሉወርቅ ካሣጋ ለመሄድ አቅጃለሁ። አጋሮ ስለምትኖር እሷን ለመጎብኘት ነው ሃሳቤ፤ በእግዚአብሔር የተቀዳጀቻውን አዲስ ሕይወት ለማሳደግና ለመርዳት፣ ጂማ ካሉ አገልጋዮችም ጋር አያይዤ ልመለስ ነው። ከእስር ከተረፉት ጓደኞቼ ጋር በወህኒ ለሚገኙት ወገኖቻችን ስንቅ፣ ቀኑን ሙሉ ዳቦ ቆሎ በመቁረጥና በማዘጋጀት እኔ ቤት ውለናል።

ወደአጋሮ ጉዞዬ ሊሸኙኝ ጓደኞቼም አብረውኝ ውለው አድረዋል። ሳምንት እስክንገናኝ ተሳስመን የተለያየነው ጠዋት አውቶቡስ ጣቢያው ላይ ነበር። እኔን እንደሸኙኝም ተያይዘው ለታሰሩት ሲጸልዩ ለመዋል ወደ ወይንሸትና አስግድ ሙላት ቤት አስኮ ይሄዳሉ። አንዱ ሌላውን ለጸሎት ሲጠራ፣ በዚያ ምሽት መንግሥት "ያልተፈቀደ ስብሰባ" ባለው ላይ፣ በቁጥር 19ሰዎች ይደርሳሉ። እሴና

ወይኗ ቤት የአዳር ጸሎት ሲያካሂዱ ተከበውና ታፍሰው ሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታሰሩ!! ጠዋት አውቶቡስ ተራ ወደ አጋሮ የሸኙኝና ሌሎችም የቅርብ ጓደኞቼ በሙሉ ማለት ነው። በሰማሁ ጊዜ አለቀስኩ። "ምነው እግዚአብሔር ሆይ እኔ ለስምህ ክብር ከመታሰር እንዴት እጎድላለሁ?" ብዬ! የእስራቱ ጽዋ ተካፋዮች ያልነበርነውን እንዳንዶቻችንን አስለቅሶናል። አባቴ ግን ቀልደኛ ስለነበረ ሰዎች እንዲህ አለ ብለው ነገሩኝ።"አሆሆ! የኔ ልጅ ናት በመንፈስ የምትመራው!!" አባቴ እንዳለው ሳይሆን እውነቱ፣ ለተረፈው ሕዝብ የእግዚአብሔር መንፈስ የለየው አገልግሎት ነበረው።

"እኛም ከእነርሱ ወገን ነን አትለዩን" በማለትም የተሳካላቸው እስራቱን ተካፍለዋል። ቤተክርስቲያናችን ስትሰደድ ምዕመኑ አብሮ ተሰዷል፤ ያልታሰረው ስንቅ አቀብሏል። ስለወንጌል እውነት ፍርድ ወንበር ፊት ቀርበን ዋስና ጠበቃ ሆነን የታሰሩብንን እህት ወንድሞቻችንን አስለቅቀናል፤ ቤተክርስቲያን ባለፈችበት ሁሉ በማለፋችን የአንድ አካል ብልቶች መሆናችንን ዓይተነዋል። የምድራዊው መንግሥት ፈቃድ በጊዜው እንደተጠበቀው ባይገኝም፡-

> "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። ማቴ. 28፡19

የሚል የሰማይ መንግሥት ፈቃድ እንዳለው ያመነው ወጣቱ ሠራዊት ያን ታላቅ ሰውን የማዳን የእግዚአብሔር ሥራ በትጋት ማስፋፋቱን ቀጠለ። እኔንና ጥበቡን ብዙ ያገናኘን የጸሎቱ መድረክ ነበር። ሁለታችንም በየፊናችን በጸሎት በምስክርነትና በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች የእግዚአብሔርን ቤት ለማገልገል ልባችን ክፍት ነበር። ምንም እንኳ ጌታን እንደግል አዳኜ በመቀበል ጥበቡን በወራት ብቀድመውም በጸሎት ትጋቱና በቃሉ ሙላቷ እሱ የበረታ ነበረ። ባምላኬ ፊት ለመንበርከክ ከነበረኝ ፍቅር የተነሳ እኔና ጥበቡ በንጹሕ እህትነትና ወንድምነት ስድስት ዓመታት አብረን በጸሎት ቤታችን አሳልፈናል። ጥበቡ በጣም የማከብረው ክርስቲያን ወንድም ነበር።

ቀደም ብዬ ባደረግሁላችሁ ትረካዬ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከቡርነት በሚመለከት በሕይወቴ ዘመን በማልረሳቸው በሁለት ገጠመኞች እግዚአብሔር እንዳስተማረኝ ገልጬላችሁ ነበር፤ በተለይም ከአንዱ ወንድም ጋር ስለነበረኝ ሁኔታ። ለጋብቻ እግዚአብሔር ሊያጣምረን የፈለገ መስሎን ብዙ መጓዛችንን። መሳታችንን በተረዳሁ ጊዜ ከገጠመኝ ታላቅ ሰብራት ብዙ ተምሬያለሁ፤ ዳግም ስህተት ላይ እንዳልወድቅ ጋብቻን በሚመለከት ታላቅ ጥንቃቄ የማደርግበት ዘመን ነበር፤ ለእኔ በድል አድራጊነት በሰላምና በዕረፍት ውስጥ መሆን የምችለው አምላኬ ለግል ሕይወቴ ባቀደልኝ ዓላማና ፈቃድ ውስጥ ብገኝ መሆኑን አውቄያለሁ። ከዚህም የተነሳ ጋብቻን በሚመለከት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እርምጃዎች ከመውሰዴም ሆነ ማንኛውንም ዓይነት ውሳኔ በራሴ ከመወሰኔ በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ ልማዴ አድርጌያለሁ። ከዚያ ወዲያ ለጋብቻ የጠየቁኝን ሁሉ ምንም እንኳ በጊዜው የታወቁ አገልጋዮችና ትጉ ክርስቲያኖች ከተሰኙት መካል የነበሩ ቢሆኑም የአምላኬን ፈቃድ ለማወቅ በጸሎት በፊቱ ቀርቤያለሁ። ባገኘሁት አምላካዊ ምላሽ መሠረት፣ በትህትና ሕይወታቸውንም እንዳልጎዳ ብዙ ጥንቃቄ በማድረግ፣ እኔ ለነርሱ ሚስት ልሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠሁ አለመሆኔን ገልጫለሁ። ስለጋብቻም ሆነ መስሏቸው ወደኔ ስለሚመጡ ወንድሞች ትልቅ ክብደት እሰጠው ስለነበር ስለእያንዳንዱ ጥያቄ በጾም በጸሎት ጌታዬን እየጠየቅሁና እርሱም መልስ እየሰጠኝ አራት ዓመታት ያህል አሳልፌያለሁ።

"ሊስትሮ ሆኜ"

ጥበቡ በአእምሮው ብሩህነት አሉ ከሚባሉት ጎበዝ ተማሪዎች አንዱ ነው። የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቹ ስለክርስቶስ አዳኝነት መናገር፣ አላዋቂነትናሞኝነት ይመስላቸዋል። ጥበቡ "የአሮጊቶች ተረት" የሚመስለውን መጽሐፍ ቅዱስን ማመኑም ያስደንቃቸዋል። እሱ ግን ከጓደኞቹ ጋር ለማውራትና ለመመስከር ያገኘውን አጋጣሚውን ሁሉ መጠቀም ይወዳል። ዘወትር ከደረት ኪሱ የማትለይ ትንሿን የአዲስ ኪዳን ይይዛል። ከእነዚህ ባንዱ ቀን የሆነውን ሲመሰክር እንዲህ አለ።

"የሕክምና ትምህርታችንን ለማጠናቀቅ ጥቂት ቀርቶናል። የለገዳዲን የውኃ ግድብ እንድንጎበኝ በዩኒቨርሲቲው አውቶቡስ እየተጓዝን ነው። አጠገቤ አንዲት ሌላ የሕክምና ተማሪ ተቀምጣለች። ጊዜዬን ለመጠቀም ስለፈለግሁ አዲስ ኪዳኔን አውጥቼ በጥሞና ማንበብ ጀመርኩ። ይህቺ ወጣት፣ ዩኒቨርሲቲ ከመግባቷ በፊት የደብረዘይት ኢቫንጀሊካል ትምህርት ቤት ተማሪ እንደነበረች አውቃለሁ። ዩኒቨርሲቲ ከገባች ወዲያ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚያሾፉት አንዷ ሆናለች። ልታዋራኝ ፈለገች፤ ለነገር እንደሆን ከጅማሬዋ ገብቶኛል፡-

"ምን ክፍል ነው አሁን የምታነበው?"

"የሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አምስትን ነው።"

"ስለምንድነው የሚያወራው?"

"ጌታ የሱስ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ሽባ የነበረውን ሰው "ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ" ብሎ እንዴት እንደፈወሰው የሚገልጽ ታሪክ ነው።

"አውቀው ነበር እረስቼው ነው እንጂ፤ አሁን አንተ ይሄ እውነት "ሆኗል" ብለህ ታምናለህ?"

"እኔ? በሚገባ አምናለሁ! ጌታ የሱስ እንኳን ሽባ መፈወስ፣ ከሞተም እንደሚያስነሳ አምናለሁ! አንቺ ግን ድሮ የምታውቂውን ታሪክ አሁን ለምን ማስታወስ እንዳቃተሽ ታውቂያለሽ?

"አላውቅም፤ ለምን?"

"አንቺ ያነበብሽው እንደ አንድ ተራ መጽሐፍ አድርገሽ ነበር። ለእኔ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው የሆነ፣ የመፍጠርና ተአምር የማድረግ ችሎታ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው።"

"ግን እኮ አንድ ሽባ የሆነ ሰው ድንገት፣ ለምሳሌ. . . መኪና ሊገጨው ቢመጣ፣ በሰውነቱ ውስጥ የድንጋጤው ኃይል ከሚፈጥረው ኬሚካል የተነሳ፣ ብድግ ብሎ ሊሄድ ይችላል።"

"ይሄን አንቺ ታምኚያለሽ?"

"አዎን! ሰዎች በሚደነግጡበት ጊዜ ማድረግ የማይችሉትን ነገር የሚያስችላቸው ኃይል ድንገት የሚያገኙበት ጊዜ አለ"

"በጹ እንግዲያው፣ እኔ ጊዜዬን ካንቺ ጋራ አላጠፋም። ቃሉን ባነብበት ይሻለኛል!"

"እንዴ፣ አላምንኝ እንጂ! እንነጋገር! ለምን ዝም ብለህ እንደ ድንጋይ ትሆናለህ። የምታመዛዝንበት አእምሮ አለህ እኮ!"

"አይ! እኔ እውነቱን አልነገርሽም? አልሆንልህ ብሎኝ ነው እንጂ፣ እኔ

*ለእግዚአብሔር ልክ እንደ ድንጋዩ ልሆንለት ነበር የምፈልገው ! !"*

*"ያቺ ወጣት በቃት ! ለእግዚአብሔር እንደ ድንጋይ እስከመሆን ከሚፈልግ ሰው ጋር ለመነጋገር አቃታት። እኔን ያን ያህል ዝቅ አድርጋ "ድንጋይ ራስ ነህ" እንደማለት ያህል ነበር አነጋገሯ፤ አለመሆኔን ለመግለጽ አጉል ክርክር ውስጥ እንድገባላትም ፈልጋ ስለሆነ፣ ወደ ንባቤ ተመለስኩ። አዝናለሁ ዛሬም ሳስበው፣ ያቺ ወጣት ልንመረቅ አንድ ሳምንት ሲቀረን፣ አመጽ ውስጥ ተገኝታ ተገደለች።"*

ጥበቡ የሕክምና ተማሪ ሳለ ከጥናቱ ይልቅ ትኩረቱና ሚዛኑ ለመንፈሳዊው ነገርና ለእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ይገርመኝ ነበር። እንዲያውም በአንድ ወቅት አንዳንድ ወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "ለእግዚአብሔር ሥራ ሙሉ ጊዜያችንን ወጣን" ብለው ትምህርታቸውን በተዉበት ጊዜ ጥበቡም "ሙሉ ጊዜዬን ላንተ ካልወጣሁ" እያለ ከአምላኩ ጋር በጸሎት የሚታገልበት ወቅት ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚፈልገውን መልስ ከእግዚአብሔር አላገኘም። ለጥቂት ቀናት ደብተሩን አጣጥፎ ትምህርት ቤት ሳይሄድ በር ዘግቶ በጸሎት ያሳለፈበት ጊዜ ነበር። ታዲያ ከልብና ከነፍስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈለግ ላይ በነበረበት በዚህ ወቅት እግዚአብሔር አንድ ራእይ አሳየው። ሙሉ ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ ከወጡት የዩኒቨርስቲ ወጣቶች አንዱን። ያ ወጣት እንደ እብድ ልብሱ ተቀዳዶ በ ኀዘን ተሞልቶ በመንገድ ላይ ሲሄድ አየ። ጥበቡም ከራዕዩ እንደነቃ እግዚአብሔር ስላሳየው ነገር በቀጥታ በመውሰድ፡- "ይሄ ወንድም በአገልግሎቱ ችግር ገጥሞታል፤ ተጎድቷል ማለት ነው፣ ስለዚህ ልጸልይለት ይገባል"፤ ብሎ ስለዚያ ወንድም መጸለይ ሲጀምር መንፈስ ቅዱስ፡-

*"አይደለም አልገባህም ! "* ይለዋል። በዚህ ጊዜ *"እሺ እግዚአብሔር ሆይ ! የዚህን ራእይ ትርጉም ግለጽልኝ"* ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀው።

*"የራዕዩ መልእክት ላንተው ለራስህ ነው ! ይህ ልጅ የኔን ፈቃድ ሳይጠይቅ ለሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ወጥቷል። ስለዚህ አሁን ደስተኛ አይደለም። ጸጋውንም አጥቷል። አንተ ደግሞ ትምህርትህን ጨርሰህ በዚያ እንድታገለግለኝ ነው እንጂ፣ ለእኔ ሙሉ ጊዜህን እድትወጣ አልፈልግም። መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣልና ተጠንቀቅ ! ካልታዘዝከኝ ግን የምታገለግለው የራስህን ፍላጎትና ምኞት እንጂ የእኔን ፈቃድ አይሆንምና አስተውል ! "* ሲል ለግሉ ተናገረው።

ጥበቡ ይህን መሳይ መልእክት ከሰማም በኋላ እንኳ ትምህርቱን አቋርጦ ለእግዚአብሔር ሙሉ ጊዜውን ለመስጠት ተደጋጋሚ ሃሳብ መጥቶበታል።

አንድ ምሽት ከሁለት ወንድሞች ጋር አብሮ ቆሞ ሳለ ስለአንዲት እህት ሲነጋገሩ ያዳምጣል፤ በትምህርቷም በመንፈሳዊውም በነበራት ሕይወት ጎበዝ ስለነበረች ዲግሪዋን በዲስቲንክሽን ጨርሳ ሥራ ገብታለች። ሁለቱ ወንድሞች የሚነጋገሩት ልጅቷ እግዚአብሔርን ትታ ወደ ዓለም ስለመመለስዋ ነበር። ጥበቡ በሰማው ነገር እጅግ አዘነ።

*"ታዲያ ትምህርት ጨርሶ ሥራ መያዝ እንዲህ እግዚአብሔርን ለመተው ከሆነ ራሴንስ በምን አምነዋለሁ ? እኔማ ትምህርቴን ስጨርስ "ዶክተር" ልባል አይደለም ወይ? ሊስትሮ ሆኜ እግዚአብሔርን ብከተል ይሻለኛል"* በቃ ! ትምህርቱን ላለመቀጠል ወሰነ። ለጸሎት እንደተንበረከከ አልተነሳም። ጠዋት ላይ እዚያው በጸሎቱ ስፍራ ሳለ ነቢይ ከሌላ ቦታ በመላክ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ሊገዝበት ስለሚገባው የሕይወት ጎዳና ተናገረው።

*" እስከዛሬ የነገርኩህን ሁሉ ብትረሳ ዛሬ የምነገርህን አትርሳ! የምታገለግለኝ በዚያ ነው ስለ ለራስህ የተናገርኩህን አስብ። ምስኪኖችን ትሰበስብልኝ ዘንድ፣ ባሮቼን ታበለጽግ ዘንድ፣ አንዳንድ በጨለማ ያሉትን ወደብርሃን ታወጣ ዘንድ፣ ለቤተሰቦችህም ብርሃን ትሆን ዘንድ ጠርቼሃለሁ"፤*

ከዚህም ሁሉ በኋላ አሁንም እንደገና ሁሉን ትቶ ለእግዚአብሔር ሥራ የመውጣት ሃሳብ አገርሽቶበት በወንድም ፈቃዱ ኦፍጋአ ባለቤት በእህታችን አማረች ተስፋዬ በኩል በመጣ መልእክትና ማስጠንቀቂያ ወደትምህርቱ ተመልሷል። ጥበቡ ሲናገር፦

*"እግዚአብሔር በትምህርቴ እንድቀጥልና በዚያ እንደሚፈልገኝ እንደገና በአማረች ተናገረኝ። እሺ ብዬ ብታዘዘው ለብዙዎች በረከት እንደሚያደርገኝ፤ በዚያ ነቢይ እንደመጣው ቃል ዓይነት "ምስኪኖችን ትሰበስብልኛለህ ባሮቼን ታበለጽግልኛለህ" የሚለውንም ደግሞ አሰምቶኛል፤" ብሏል።*

ጥበቡ በዚህ ጉዳይ ልቡ እስኪያርፍ ድረስ አድራሻው ዩኒቨርሲቲ መሆኑ ቀርቶ በጸሎቱ ስፍራ ነበር። እንዲያ ታዋቂና በመምህራኑም ተደናቂ የነበረው ጥበቡ በዚያ ዓመት ያሳያቸው ዝቅተኛ ውጤቶች ፕሮፌሰሮቹን በእጅጉ አሠያይቋቸዋል። ስለዚህም ትምህርቱ ከብዶት እንዳይደለ ያወቁት ፕሮፌሰሮች ጠርተው ካነጋገሩት በኋላ፣ ያን ዓመት ደግሞ እንዲማር አደረጉት። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሕይወቱ ትምህርቱን ቀጥሎ በዚያ እንዲያገለግለው መሆኑን ከተረዳ በኋላ፣ ቅድሚያን ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለጽድቁ በመስጠት ትምህርቱን እስከ ዘለቄታው በክብር አጠናቋል።

በ1964 ጥበቡ የሕክምና ትምህርቱን በድሮ ልዕልት ፀሐይ (አሁን ጦር ኃይሎች) ሆስፒታል በመከታተል ላይ ነው። የሚያድረው ሕንጻ ኮሌጅ ዶርሚታሪ ውስጥ ነው። በእዚህ ጊቢ ያሳለፈውን ጊዜ ጥበቡ ሲናገር እንዲህ ገልጾልኝ ነበር፦

*"የተሰጠኝ የመኝታ ክፍል ሁለት ተማሪዎች ሆነን የምናድርበት ነበር። ልጁ ስለመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ስለጸሎት ግድ የሌለው ነው። በመኝታ ክፍላችን እኔ ተንበርክኬ ስጸልይ ወይንም መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ እሱ ይዘፍናል፣ ወይንም የዘፈን ቴፕሪኮርደር ይከፍታል፤ ይሰማው እንደሁ ብዬ ጥቂት ታገስኩ ልጁ እየባሰበት መጣ። እኔ ለጸሎቱም ሆነ ለንባቡ አእምሮዬን መሰብሰቡ አላስቸገረኝም፤ ሆኖም ግን እኔ በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኬ ሳለሁ በሚያደርገው ነገር እግዚአብሔርን ብዙ እየደፈረ ስለነበር ስለእርሱ አሳሰበኝ። ስለዚህም ነገር ስጸልይ አንድ ባዶ ክፍል መኖሩን አስተዋልኩና እየወሰድኩ የምመልሰው ቁልፍ አስፈቀድኩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የሁለት ሰው እየከፈልኩ ሙሉ ለሙሉ ብፈልግ ተንበርክኬ የማድርበት የራሴ ክፍል እንዲኖረኝ አደረግሁና ተገላገልኩ። ከሌሎች ጋር ለመጸለይም ተመቸኝ።"*

ጥበቡ በዚህ ዓይነት ነገሮችን አመቻችቶ ጥቂት እንደተጓዘ ነበር እነወንድም ፈቃዱ እና ባለቤቱ እህት አማረች ከለቀምት አዲስ አበባ የመጡት። የተቀበላቸው ወንድም ባለቤቱ መንፈሳዊ አልነበረችም። በጣም ተቃዋሚና ለራሱም የማትመቸው ሰው ስለነበረች እነወንድም ፈቃዱ ማረፊያ ያጣሉ። በጣም ስለተቸገሩ ጥበቡጋ ስልክ ደውለለት መፍትሄ ይገኝ እንደሁ። "ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት" ሳሉ በነበራቸው የመንፈስ ኅብረት ብዙ አብረው ያሳለፉ የሚወዳቸው ወገኖቹ ናቸው። ለእነሱማ ሌላ ቦታ የመፈለግ ሃሳብ ም አልነበረውም።

*"እኔጋ መሆን ትችላላችሁ፤ ኑ!"*

ትልቅ እፎይታ! እነወንድም ፈቃዱን እዚያ ተማሪዎች ዶርም ለአንድ ሳምንት ጥበቡ አኑሯቸዋል። ጥበቡ ባደረገው ስህተት ተቀጣ፤ እነወንድም ፈቃዱም ማረፊያ አጡ! ጥበቡ ወሰነ፤ ከግቢው ውጭ የራሱ የሆነ ቤት ለመከራየት። ቤት ለመፈለግ ሲጸልዩ፣ እግዚአብሔር ለምክረ (የጥበቡ ወንድም) እና ለአሰፋው (የፍቃዱ ወንድም) እንዳቸው ቤቱ ምን እንደሚመስል እንዳቸው ደግሞ ቤቱ የሚገኝበትን ሰፈሩን አሳያቸው። ጥበቡ ባሰቸኳይ እርምጃ ወሰደ፡- ምክረንና አሰፋውን እንዲህ ሲል ላካቸው።

*"እግዚአብሔር ያሳያችሁን ቤት ሂዱና ፈልጉ!"*

መልእክተኞቹም እግዚአብሔር ያሳያቸውን ቤት አግኝተው ተመለሱ!! ጥበቡ ኃይለሥላሴ ቤቱን ወዲያው ተከራየና እንግዶቹን ይዞ ከሕንጻ ኮሌጅ ግቢ ወጣ።

ተከራይተው በገቡ ሌሊት ጥበቡ ሲጸልይ፣ የቤቱ ባለቤቶች ጌታ ኢየሱስን እንደሚቀበሉ ተናገረው። ሲነጋ ጥበቡ ወደሆስፒታል ከመሄዱ በፊት ሰላም ሊላቸው ገባ። ስለእግዚአብሔር መሰከረላቸው። ባለቤቶቹ ሸዋዬና ተሰፋዬ ጌታ ክርስቶስን እንደግል አዳኛቸው ተቀበሉ። በእግዚአብሔር ቤትም ተተክለው ቀሩ። እህታችን ሸዋዬ ቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል በዲያቆንነት ለረዢም ዘመን አገልግላለች። ዛሬም ዲያቆን ናት። እስታውሳለሁ ዶክተር ብርሃኑም እዚህኛው ቤት ከጥበቡ ጋር አብሮ ይኖር ነበር። በእነ ወንድም ፍቃዱ መምጣት ምክንያት እነሱን ለማግኘት ስመጣ ከጥበቡ ጋር እንደገና በጸሎቱ ዓለም የተገናኘነው እዚህ እነሸዋዬ ቤት ነው። ስለእኔና ጥበቡም ትዳር እግዚአብሔር የተናገረን ከእነዚህ ዓመታት በኋላ በ1966 ዓ.ም ነው።

****

*"ሚስትን መውደድ ያውቃል?"*

ጥበቡ ለገበዝ ተማሪዎች በዘመኑ ይሰጥ የነበረውን የኪስ ገንዘብ ከጀርመን መንግሥት በወር 120 ብር ያገኝ ነበር። ያኔ የብሩ ዋጋ ጥሩ ስለነበር ከጌታ አሥራት በመለስ ለቤቱ ኪራይና ለአንዳንድ ለእግዚአብሔር ሥራ አስፈላጊ ጉዳዮች የሚያውለው ይህንኑ ገንዘብ ነበር። ከሚያገኘው ከዚህ የኪስ ገንዘብ 75 ከመቶ ያህሉ ለጌታ አገልጋዮችና ለአሥራቱ ሲውል ጥበቡ ቅያሪ ልብስና ጫማ እስከማይኖረው ድረስ ራሱን የካደ ሰው ነበር። ለእግዚአብሔር ቤት ያለው ቅንዓት፣ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ የጌታ ባሪያዎች ያለው ፍቅር፣ አክብሮትና እንክብካቤ እጅግ ጥልቅ ነበር። ተቀዶ ውኃ በሚያስገባ ጫማ የሕክምና ትምህርቱን ይከታተል በነበረ ከነዚህ ባንዱ ወቅት ታላቅ ወንድሙ ድንገት ሳያስበው መርካቶ ወስዶት ሙሉ ልብስ ከነጫማው የገዛለትን ጊዜ ጥበቡ ይናገራል። ጥበቡ ገና የሕክምና ተማሪ ሳለ ዩኒቨርሲቲ ሆስቴል ውስጥ መኖር ሲችል ምርጫው የቤት ኪራይ ነበር። ምክንያቱም ለእሱም ሆነ ለሌሎች ወገኖች የሚመች የጸሎት ክፍል ሊኖር የሚችለው የግል ቤት ቢኖረው ስለሆነ። ለኪራይ የሚመርጣቸው ቤቶች ለዚህ አገልግሎት ብቁ መሆናቸውን በቅድሚያ ያረጋግጣል።

ስለዚህ ጥበቡ የሚከራያቸው ቤቶች 24 ሰዓት ለጸሎት ክፍት የሆነ አንድ ክፍል እንዲኖራቸው ግድ ነው። ያቺ ክፍል በሰሌን ተነጥፋ ለሚጸልዩ ሁሉ ክፍት ነች። ዳሩ የጥበቡም ሆነ በተለያየ ወቅት አብረውት የኖሩ ወገኖች እልጋቸው ተነጥፎ ይዋል ይደር እንጂ፣ እነርሱ ባብዛኛው የሚያድሩት ሲጸልዩ እንደነበር ትዝ ይለኛል። ስለዚህ ጥበቡ ቤት የሚጸልይ ሰው፣ ከጸሎቱም ወጥቶ በእርጋታና በጥሞና በግሉ ወይንም በህብረት የእግዚአብሔርን ቃል የሚከፋፈል ሰው አይታጣም።አልፎ አልፎ ይሁን እንጂ እኔም የዚህ ህብረት ተካፋዮች ከነበሩት አንዷ ነበርኩ።

ከጸሎት በኋላ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ የሚደረገው ጭውውት በጸጋ የተቀመመ፣ እናም ጠለቅ ወዳለ የቃሉ መገለጥ የሚወስደን እንደነበር አስታውሳለሁ። የሰብከት መድረክና ቅርጽ ያለው ፕሮግራም አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ ግን እንደመውደዱ በዚያ የምንገኛኘውን ሁሉ ሲያስተምረንና ጸጋውን ሲያከፋፍለን ዓይቻለሁ። በጸሎት ጊዜያችን እግዚአብሔር በመከከላችን ሲመላለስ ስላየሁ ያ ስፍራ ለእኔ ቅዱስ ስፍራ ነበር። ከቁስሌና ከሰብራቴ የዳንኩበት አንዱ የመጽናናት ስፍራ። ጥበቡም ከሕክምናው ትምህርት ይልቅ የሚገደው የእግዚአብሔር ነገር ስለሆነ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ የተሰጠ፣ የጾምና የጸሎት ሰው መሆኑን ዓይቼ "ቅዱስና የተባረከ" ብዬዋለሁ።

ከእለታት አንድ ቀን ግን ቤቴ ውስጥ ሌሊት ተኝቼ ሳለ በህልሜ ያየሁት ነገር በእጅጉ አስበረገገኝ። በጣም የሚያንጸባርቅ የጋብቻ ቃል ኪዳን ቀለበት በውስጡ ጥበቡ ኃይለሥላሴ የሚል ስም የተቀረጸበት በጣቴ ሲጠልቅልኝ አየሁ። ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ፊት ተንበረከክሁና፦

*"እግዚአብሔር ሆይ ምን ዓይነት ኃጢአተኛ ነኝ! እንዴት ይሄን ቅዱስ ሰው ደግሞ ለጋብቻ አስበዋለሁ? ይሄ የራሴ ድካም እንጂ አንተ አይደለምህና እኔን ኃጢአተኛዋን ማረኝ!! በዚያ በሚጠዘጥዝ የ ኀዘን ቁስል የተመታሁበት የራሴን ፈቃድ የመከተል አሮጌ ሕይወት ዳግም አንሰራራን? እባክህ አምላኬ ይህን ቅዠት ከእኔ አስወግድ"* ነበር የዚያ ሌሊት ጸሎቴ።

በዚያኑ ሌሊት ለአንዷ የቅርብ እህቴና የጸሎት ጓደኛዬ ወይንሸት ኃይለማርያም የጥበቡና የእኔ ነገር በትዳር እንደሚቋጭ ይህም ከእግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራታል። በማግስቱም ከወይኒ ጋር ስንገናኝ እግዚአብሔር በሌሊት ስለእኔ ያሳያትን ልትነግረኝ ስትፈልግ፦ "በልብሽ ያዝውና እግዚአብሔር ባለ ቀን ፍጻሜውን ስታዪ ምስክር ትሆናለሽ እንጂ አሁን ምንም ነገር አትንገሪኝ" ነበር ያልኳዋት። እኔ ግን በግሌ ስለዚህ ጉዳይ አጥብቄ የሥጋዬንና የራሴን ሃሳብ እየተቃወምኩ መጸለዬን ቀጠልኩ።

*"እንዴት ይህን ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው? እንዴት ወንድሜን?"* ነበር የእኔ ጥያቄ።

ጉዳዩ ግን ከእግዚአብሔር የተወሰነ ስለነበር በተለያየ በሚገባኝ መንገድ እግዚአብሔር ቢናገረኝም ራሴን በመኮነን የጸለይኩትን ሁሉ ጥሶ ለሌሎች ባሪያዎቹም መግለጽ ጀመረ። ነገሩ ከእግዚአብሔር መሆኑ ከገባኝ በኋላ ደግሞ፦

*"እሺ ይሁን! ግን እንዲያው እግዚአብሔር ሆይ! እሱ አንተን መውደድ እንጂ ለመሆኑ ሚስትን መውደድ ያውቃል? ለሚስትስ የሚሆን ፍቅር በልቡ ይኖራል?"* ያልኩትም ትዝ ይለኛል።

ጥበቡም እንዲሁ በሚያየው በውስጡም ይሰማው በነበረው ነገር ሁሉ "ስቼያለሁ አምላኬንም በድያለሁ፤ እንዴት እህቴን?" ሲል ሰንብቶ ጥርት ባለ መንገድ ለግሉ እግዚአብሔር ከተናገረውና ካረጋገጠ በኋላ ነበር የተረዳውን ሁሉ በግልጽ እንድንጋር ወደኔ የመጣው።

****

## *"ዕጣችንን እንቀበላለን"*

ጥበቡና እኔ በትዳር እንድንጣመር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እርስ በእርስ በተገላለጥን ቀን እግዚአብሔርም ሲለን የሰነበተውን ሁሉ በተከፋፈልን በመጀመሪያው ቀን ጥበቡ ያለኝን አልረሳውም።

*"ያዕቆብ በላባ ቤት ሳለ እግዚአብሔር "ወደ አባትህ አገር ግባ" ብሎ ተናግሮት መንገዱን ቢጀምርም ከፊቱ ለሚጠብቀው ወንድሙ ዔሳውም ሆነ ለቀሪ ጉዞው በእግዚአብሔር እጅ መባረክ እንዳለበት የገባው ሰው ነበረ። "ካልባረከኝ አልለቅህም" ሲል ሌሊቱን በሙሉ በጸሎት በመታገሉም ጌታ እግዚአብሔር ስሙንና ሕይወቱን በሚለውጥ ከንዱ ተገናኝቶታል። እኛም በዚህ የትዳር ሕይወት ውስጥ እንድንገባ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አሁን አረጋግጠናል። ወደዚህ ታላቅ ኃላፊነት ለመግባት ግን የአምላካችን እጅ ልትባርከን ያስፈልገናልና በፊቱ በጾምና በጸሎት አብዝተን መሆን ይገባናል"* ነበር ያለኝ።

ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀን በእጮኝነት የቆየንባቸው ሁለት ዓመታት ባብዛኛው ያለፉት በዚህ ሁኔታ ነበር። ጥበቡን በዚህ መንገድ ከቀረብኩት በኋላ ከእርሱ ሕይወት በሚተላለፈው መንፈሳዊ ጉልበት ይበልጡን መትጋትንና በአምላኬ ፊት አብዝቼ መቆየትን ተለማምጃለሁ። የሕክምና ትምህርቱን በሚያጠናቅቅ በመጨረሻው ዓመት ላይ አንድ ቀን በጾምና በጸሎት ላይ ሳለን እንዲህ አለኝ፡- *"ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ "ያላገባው እግዚአብሔርን እንዴት ደስ እንደሚያሰኘው የእግዚአብሔርን ነገር ያስባል። ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል ልቡም ተከፍሎአል"* ስለሚል እኔ ለእግዚአብሔር ያለኝ ፍቅር እንዲከፈልብኝ ስለማልፈልግ ሚስት አላገባም ብዬ ወስኜ ነበር። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር በጸሎት ላይ ሳለሁ፡- ‹እኔ ሚስት እንድታገባ ብፈልግስ?› አለኝ። እኔም

*"ጌታዬ ሆይ ሚስት እንዳገባ የምትፈልግ ከሆነ እሺ ለፈቃድህ እታዘዛለሁ። ነገር ግን አንተ ለኔ ያዘጋጀሃትን እህት መርጠህ አሳየኝ እንጂ እኔ በስጋዬ የማያቸውን እህቶች ሁሉ ይቺ ትሆን ያቺ? እያልኩ ስህተት ውስጥ አልገባም። ደግሞም እግዚአብሔር ሆይ ብቻ አንተ ለእኔ ያዘጋጀሃት ሴት ትሁን። ፊደል የቆጠረች ትሁን ወይም ሀሁ እንኳ የማታውቅ ገጠሬ፣ መልክ ያላት ትሁን የሌላት፣ በፊትህ የማስቀምጠው የእኔ የሆነ አንዳች ምርጫ የለኝም። ሁሉን ላንተ እተወዋለሁ። እግዚአብሔር ሆይ ደግሞ አንተ ባዘዝከኝ መሠረት የሕክምናውን ትምህርት በማገባደድ ላይ ነኝ። እኔን በሕክምናው ሥራ እንድሰማራ የምትፈልግ ከሆነ በሥራ ዓለም በመባከን ብዛት አንተን ስበድልና ሳሳዝን ልገኝ እችላለሁ። ስለዚህ የማገባት ሴት ስለእኔና ስለቤትህ ስለ ሕዝብህና ስለአገልጋዮችህ በቤት ሆና የምትማልድ እንድትሆን እለምንሃለሁ"* ብዬው ነበር።



ጥበቡ ከሚልኪያስ እና ከብርሃኑ ጋር

እግዚአብሔር ደግሞ የሰጠኝ አንቺን ነው፤ ተምረሽ በሥራ የተሰማራሽ ሰው። ስለዚህ ጸልዩና እግዚአብሔር የሚልሽን አድምጪ። አንቺ በሥራው ዓለም መቀጠል ከተሰማሽ ያለምንም ቅሬታ ቤት ሆኜ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት የምቆየው እኔ እሆናለሁ። ምክንያቱም ከሁለት አንዳችን ስለ እኛና ስለ እግዚአብሔር ሥራ የሚማልድ ሰው ያስፈልገናል ብዬ በጥብቅ ስለማምን ነው" አለኝ። ደነቀኝ።

በአእምሮ ቢታሰብ ትዳርን ያህል ትልቅ ጉዳይ በፊታችን ቆሞ ብሎ አዲስ ለምንመሰርተው

ቤት የኔና የእርሱ ደሞዝ ቢቀናጅ ብዙ ቀዳዳ ሊሸፍንልን ይችል ነበር። "ትንሽ እንኳን ትዳራችንን ሳናቋቁም?" የሚያሰኝ ነገር። ጥበቡ ኃይለሥላሴ ግን ትዳሩ ባለመናወጥ ሊቆም፣ በወጀብና ባውሎ ነፋሱም ሰንጥቆ ሊያልፍ የሚችለው ከወዲሁ በእግዚአብሔር ፊት በመሆን ብቻ እንደሆነ የገባው ሰው ነበር! በመዝሙረ ዳዊት 32፥6 ላይ፡- "ስለዚህ ቅዱስ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወደ አንተ ይለምናል ብዙ የጥፋት ውኃም ወደ እርሱ አይቀርብም"፤ የሚለው ቃል ትዝ አለኝ።

ማን ያውቃል? እግዚአብሔር ይህን ጊዜ እያመቻቸልኝ ያለው አሁን ጊዜ ሳለኝ ፊቱን እንድፈልገው ሊመጣ ያለውን ነገር ሊያሻግረን የሚያስችለንን ጸጋ ከወዲሁ እንዲለቀቅልን ወዶስ ቢሆን? ያም ሆነ ይህ ብቻ ምኞቱ ልቤን ነካው። በብዙ መደነቅ፣ እንዲህም ያለ የእግዚአብሔር ሰው ለትዳር የሰጠኝንም አምላኬን በማክበር፣ በብዙ ትህትና በጸሎት ቆየሁ። ለጸሎት ሕይወት ራሴን በመለየት ለሰባት ዓመታት ስሠራ ከቆየሁበት ከሥራዬ መሰናበት ያለብኝ እኔ መሆኔን አወቅሁ። ልቤ በደስታና በሰላም ተሞላ። ግን ያለ ተቃውሞና ከአንዳዶችም ያለ ግሳጼ አልነበረም።

"ገንዘቡ ላንቺ ባያስፈልግሽ እንኳን፣ ሰንት ሊረዱ የሚገባቸው ሰዎች/ዘመዶች አሉ። አብደሻል ወይ? ልክ ነሽ ወይ? . . . ." ሌላ ሌላም ብዙ።

1967ዓ.ም. ጥበቡና ሁለቱ ጓደኞቹ ሚልኪያስና ብርሃኑ የሕክምና ትምህርታቸውን አጠናቀው መንግሥት ወደየሚመድባቸው የአንድ ዓመት የአገልግሎት ስፍራ የሚሄዱበት ነበር። ስለዚህ በሁሉም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን ስንፀልይ ቆይተናል። የዚያን ዓመት የሕክምና ምሩቆች 23 ነበሩ። መንግሥት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሐገራት ሐኪሞቹ የሚሄዱበትን ቦታ ለመመደብ የራሳቸውን ዕጣ እንዲያወጡ ጠየቃቸው። በዚያን ወቅት ጦርነት ይደረግባቸው የነበሩት የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍሎች ዕጣው ውስጥ እንደሚገኙባቸው ለሐኪሞቹ ተነገራቸው። የኤርትራው ሻዕቢያ እንዲሁም ኢህአድግ /ወያኔ ከደርግ ጋር ጽኑ ወጊያ የሚያደረግባቸው እነትግራይና ሌሎችም ክፍላተ ኢትዮጵያ መጨመራቸው ችግር አስከተለ። ሐኪሞቹ "እነዚህ ጦርነት የሚካሄድባቸው ቦታዎች ከዕጣው ውስጥ ካልወጡልን ወደነዚህ አደገኛ ቦታዎች ገና ከሁኑ መሄድ አንፈልግም፤ ዕጣውንም አናወጣም" ሲሉ አደሙ።

ጥበቡና ሁለቱ ጓደኞቹ ግን የእነርሱ ዕጣ በአምላካቸው እጅ እንደሆነ ስለሚያውቁ እሱ የሚመርጥላቸው ሁሉ በጦርነትና በእሳት መካከል እንኳ ማለፍ ቢሆን እግዚአብሔር ከነርሱጋ እንደሆነ በማመናቸው ዕጣውን ለማውጣት ዝግጁ ሆኑ። የቀሩትን ሐኪሞች ሃሳብ ለማስለወጥ ጥቂት ቀናት አለፈ። በዚህ መሀል ሚልኪያስ ወደ አዋሳ ሄዷል። ጥበቡና ብርሃኑ ግን ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሄደው "እኛ ዕጣውን ለማውጣት ፈቃደኞች ነን ጦር ግንባርም ቢደርሰን ዕጣችንን እንቀባለለን" አሉ። ለባለስልጣኖቹ ይህ ልብ የሚነካ ነገር ነበር። ዕጣቸውን ሲያወጡ ዶ/ር ብርሃኑ ባሌ ጎባ ጥበቡ ደግሞ ቀብሪደሃር ደረሳቸው። ከጥቂት ቀናት በኋላ ዶ/ር ሚልኪያስ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ የእርሱን ዕጣ ለማውጣት ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሄደ። ዶ/ር ሚልኪያስ ባሌ ጎባ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር እንዲሠራ ዕጣ ወጣለት።

ዕጣው በእርግጥ የወጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበር በቅርብ ላስተዋለው። ምንም እንኳ ሶስቱም ከጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት አንስቶ፣ ኋላም በክርስቶስ ወንጌል አመካኝነት ሕይወታቸው የተሳሰረ የቅርብ ጓደኞች የነበሩ ቢሆኑም፣ የጥበቡ ከነርሱ ርቆ ቀብሪደሃር መድረሱ ለእኔ ትርጉም ነበረው። አንዱ፡- ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ሚልኪያስ ትዳር የሚመሰርቱት ጥቂት ዓመታት እንደቀረው ያወቀው ጌታ እግዚአብሔር የሁለቱን በአንድነት መሆንን መፈለጉ ይመስለኛል።

ሌላው ደግሞ፡- ገና በፊታቸው ለዘረጋላቸው የአገልግሎት ዓመታት፣ የሕይወትና የኑሮ ዓላማ ይመስለኛል። ለሥራም ሆነ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ስኮትላንድ መሄድ፣ በአዋሳኝ መሬት ላይ ቤት ሰርቶና በፍቅር ተጎራብቶ ለመኖርም ሆነ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋኩሊቲ በመመህርነትና በዲንነት መመረጥ፤ ... ብቻ አንዱ ባለበት ሌላኛው እንዲገኝ በማድረግ እነዚህን ሁለቱን እንደ መንትያ ወንድማማች ከሶስተኛ ጓደኛቸው ከጥበቡ ለየት በማድረግ ሊመራቸው መፈለጉ ነው። ያምላኬን አሰደናቂ እቅድ ዛሬም መለስ ብዬ ሳስበው እደነቃለሁ።

እኔንና ጥበቡን በሚመለከት ደግሞ፣ ራሱ በቀጠረልን ጥቂት ወራት ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ትዳራችንን እንደሚመሰርትልን ያውቅ ነበር። የእኛም ኅብረት ለእርስ በርሳችን ኃይል እንዲሆነን በክርስቶስ በጌታችን እርሱንም በሚመለከት ባለን የሕይወት አቋም የማንነቃነቅ የማንናወጥ ጽኑዎች ሊያደርገን ፈለገ። ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ሚልኪያስን ሁለት አድርጎ ወደ ጎባ እንደላካቸው፣ እኔንና ጥበቡን ደግሞ ሁለት አድርጎ ሊልከን የልቡንም ሃሳብ ፈጻሚዎች ሊያደርገን እቅድ አወጣ። ብቻ እግዚአብሔር በድንቅ አሠራሩ እንደቃሉ "ሁለት ሁለት" እያደረገ ወደ ቀጣዩ መለኮታዊ ተልእኮአችን በየፊናችን የማያስገባንን በር በፊታችን ከፈተው። ሊመጣ ያለውን የሚያውቀው አምላካችን ከእኔና ከጥበቡ ጋር የብቻ የዝግጅት ዘመን አስፈለገው። ከኖርንበትና ከለመድነው ኅብረትና አካባቢ ነጠል አድርጎ ወስዶ እኔንና ጥበቡን በምድረ በዳ ሊያባብለን ወደደ። ጥበቡ ቀብሪደሃር በዕጣ ከደረሰው በኋላ ስለ ሥራው ሁኔታና ስለ መኖሪያ ሰፍራ የተደረገለትን ገለጻ ሲነግረኝ ልቤን ገረመው። አምላኬን ሂሳብ በማወራረድ ማንም የማይችለው ደግሞም የማንም ባለዕዳ ያለመሆኑ!

> *"ቀብሪደሃር የምትኖረው መንግሥት በሚሰጥህ ቆንጆ ቪላ ቤት ከተሟላ እቃው ጋር ነው፤ ሻንጣህን ይዞ መግባት ብቻ ነው! ደግሞም ስፍራው ቆላ ቀመስ ስለሆነ ደሞዝህ ከነአበሉ ሲታሰብ፣ አብረውህ ከተመረቁ ጓደኖችህ ከእጥፍ በላይ ነው። የምታገኘው የወር ደሞዝ 1650 የኢትዮጵያ ብር ነው!"* ብለውታል የዘመኑ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባለሥልጣን፤ የጥበቡ ደሞዝ ሂሳቡ ቢሰላ በጊዜው ከነበረ ከአንድ ሚኒስቴር ደሞዝ በላይ ሆነ! ጭማሬው ብቻ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በዜና አዘጋጅነት እኔ አገኘው የነበረውን ደሞዝ ከእጥፍ በላይ የሚያጥፍ! ማነው ታዲያ ሊሻን ሥራዋን መተዋ ስህተትና ሞኝነት ነው ወይም ኪሳራ ነው ሊል የሚችል?

እሱን እንከተለው እንጂ አምላካችን የወደረኞቻችንን አፍ የሚዘጋ ሥራን መሥራት ያውቅበታል!! የኔንና የጥበቡን ትዳር እንዲህ አድርጎ አምላካችን ስላመቻቸልን የሠርጋችን ቀን መስከረም 10 ቀን 1968 ዓ.ም. እንዲሆን ተወሰነ። በተጋባን በሳምንታችን አዲስ አበባ የሚገኙትን ቤተሰቦቻችንን በጌታም አብረን ብዙ ያሳለፍን ጓደኞቻችንን ተሰነባብተን ወደ ቀብሪደሃር ጉዞ ጀመርን። የእኔን አራተኛ ታናሽ ወንድም ሰይፉ አንጎናፍርን እንዲሁም ወጣት ኢያሱ ደርበውን ጨምረን ነበር የቀብሪደሃሩን ኑሮአችንን ለመጀመር ከአዲስ አበባ የተነሳነው። ኢያሱ ደርበው በእምነቱ ምክንያት በቤተሰቦቹ የተባረረ ስደተኛ ሲሆን፣ ጥበቡ እንደ ልጁ ከራሱ ጋር ያኖረው ልጃችን ነው። ከአዲስ አበባ በሌሊት ባቡር ተጉዘን በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ድሬ ደዋ ገባን።እግረ መንገዳችንን በደረስንባት ድሬ ደዋ ከተማ ግን ለአሥር ቀናት ያህል የሙሽርነት ጊዜያችንን አሳልፈንባታል። በእነዚህ ቀናቶች ውስጥ ድሬደዋ ከነበሩ ክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር ኅብረት ስናደርግ ቆይተን በመጨረሻም በሱማሌ ክልል ወደምትገኘው ቀብሪደሃር አመራን።

****

# 8

## ቀብሪደሃር

ቀብሪደሃር የምትገኘው ኢትዮጵያንና ሶማሊያን በደቡብ ም ሥራቅ ከሚያዋስነው ጠረፍ 280 ኪሎ ሜትር ወደ መሃል ገብቶ ነው። ጎረቤታችን ሶማሊያን ኦጋዴንንና ጅቡቲን እንዲሁም ከኬንያ የሰሜኑን ክልል ከራሷ ቀላቅላ "ታላቋ ሶማሊያ" የሚባል አገር የመፍጠር ምኞት ሲያናውዛት ዓመታት ተቆጥረዋል። ይህን ምኞቷን እውን ለማድረግ በተደጋጋሚ ስውርና ግልጽ የሆኑ ሙከራዎች ማድረጓ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። ሆኖም እንዲህ መሰል ሙከራዎቿ ባብዛኛው እዚያው በተመደቡ የኢትዮጵያ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ስለሚቀጭ ቀብሪደሃር ከተማ ድረስ ዘልቆ የገባ ችግር ለረዥም ዘመናት ኖሮ አያውቅም።

ቀብሪደሃርን በአጫጭር ጊዜዎች ውስጥ አሁን ሳያት ሁለተኛ ጊዜዬ ነው። የጥበቡን የሥራ ምድብ ካወቅን በኋላ ለቤት የሚያስፈልጉትኝን ነገሮች በዝርዝር ለመረዳትና የአካባቢውን ሁኔታ ለማየት ከሠርጋችን ከሦስት ወራት በፊት ቀብሪደሃር ነበርኩ። የጅጅጋን፣ የደገሀቡርንና የሌሎችን ትናንሽ መንደሮች በግራና በቀኝ እያቆራረጠ፣ ጭው ያለ ሜዳ እየሰነጠቀ፣ መኪናው ሲከንፍ የምድር ጫፍ ለመድረስ የቸኮለ ይመስል ነበር። ቀብሪደሃር ብቅ ስትልልኝ ሃሳቤ እንደ ተደላደለ ትገዘ ይለኛል፤ ከሐረር አንስቶ ቀብሪደሃር ያስገባን ብቸኛው ጎዳና ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር እንዲያመቻት የሠራችው አሮጌ መንገድ ነበር።

ቀብሪደሃር በጌታም ሆነ በሥጋ የተወለድንባቸውን ቤተሰቦቻችን በ1000 ኪሎ ሜትር ርቀት ተለይተን የመጠንባት ምድር ነች። ከተማ ተወልደን ከተማ ላደግነው ለእኔና ለጥበቡ ዓይነት ወጣቶች ቀብሪደሃር በእርግጥ ጭው ያለች ገጠር ነች። ሆኖም ግን ገና ምድሪቷን በመጀመሪያው ዙር ስረግጥ "የእኔንና የጥበቡን ትዳር የመሠረተው ልዑል እግዚአብሔር ከዕጣዎች ሁሉ የምትበልጠውን ዕጣ ከፍቅር ጉያው አውጥቶ የመረጠልን ስፍራ" ብያት ነበር። በጌታ ፍጹም ፈቃድ ውስጥ ለምንገኘው ለእኔና ለጥበቡም አምላካችን እግዚአብሔር እርሱ ራሱ *"እንደ ደማቅ ከተማ ብርሃን ይሆንልናል"* ብዬ በሙሉ ልቤ የከተማዋን ኋላ ቀርነት ተቀብያለሁ።

እንዲያው ለመሆኑ አምላካችን እግዚአብሔር የፍቅራችንን እፍታ በፊቱ ሆነን በሰከነ



ጥበቡ በነሐሴ 1967 ዓ.ም.

መንፈስ እንድናጣጥመው አስቦልን ይሆን፤ ከዚያ ሁሉ ኅብረት አውጥቶ ፈንጠር አድርጎ ወደዚህ ያመጣን? በእርግጥ እግዚአብሔር እኔና ጥበቡ በአንድ ቤት ጣሪያ ሥር ሆነን የአምላካችንን ታላቅ ሥራ እንድናስፋፋ ፤ እዚህ ኢትዮጵያ ደቡባዊ ጫፍ አምጥቶናል ብዬ የራሴን ግምት ወስጃለሁ። ብቻ አምላኬ ከሰጠኝ ከዚህ የተባረከ መንፈሳዊ የትዳር ጓደኛ ጋራ ይሁን እንጂ ምድረበዳም ቢሆን ለምለም ስፍራ፣ ከተማ ቢሆን የገጠር ገጠር፣ ደስታዬ ፍጹም ይሆናል ብዬ ዕጣዬን ያላንዳች ቅሬታ ተቀብያለሁ። አዎን ከጥበቡ ጋር በትዳር ዘመናችን ሁሉ ልብ ለልብ እጅ ለእጅ ተያይዘን የአምላካችንን ሥራ እንሠራለን፤ ቀብሪደሃር በወንጌሉ ብርሃን ትጥለቀለቃለች፤ ይሄ በ ዓይነ ሕሊናዬ የሳልኩት የለጋው ትዳራችን ውጥን ነበር።

ቀብሪደሃር ከተማ የተቆረቆረችው ከፍ ባለ ኮረብታማ ስፍራ በመሆኑ በአራቱም ማዕዘን ለዓይን እስከሚታክት የሚታየውን ሜዳ ለመቆጣጠር ያመቻል። ከከተማው በርቀት ከሚታየው ጫካ ድኩላዎች የሜዳ አህዮችና የመሳሰሉ የዱር አራዊት መጠለያ ነው። በመሃል አገር ፈረስ፣ አህያና በቅሎ በዝተው የሚታዩትን ያህል በረሃማውን የአየር ንብረት መቋቋም የሚችሉ የግመል መንጋም በብዛት ይታያል። ያ አንድና ብቸኛ ጎዳና ከተማዋን መሃል ለመሃል ይሰነጥቅና ወደ ከተማው ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚያመራሩ አቧራማ የስፈር መንገዶች ይሰበጣጠራል። ከእነዚህ የሚሰበጣጠሩ መንገዶች መሃል ጥቂቶቹ ከሞቃዲሾና ከሀርጌሳ በኮንትሮባንድ የሚገቡ እቃዎቻቸውን የሚሸጡባቸው ባለ ደማቅ ቀለም ጨርቃ ጨርቅና እቃዎች ወደ ተሞሉ ሱቆች ያደርሳሉ። ለ መንግሥት ሥራ ጉዳይና ለንግድ በከተማው ከሚኖሩት የተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ አገራት ከመጡት ሌላ፣ ባብዛኛው የከተማው ነዋሪ ብሔረሰቦች የኦጋዴን ሶማሌዎች ናቸው። በባህላቸው አርብቶ አደር ስለሆኑም የሶማሌዎቹ ባህላዊ ጎጆዎች/ቱኩሎች ከከተማው ጠርዝ ይታያሉ። ታዲያ የአገሬው ሰዎች ተንቀሳቃሽ አርብቶ አደር በመሆናቸው ቋሚ የሆነ የአኗኗር ስልት ባይኖራቸውም፣ ጣልያን በገባ ጊዜ የሠራቸው አንዳንድ የድንጋይ ቤቶች በከተማዋ ውስጥ አልፎ አልፎ ይታያሉ። ከእነዚህ አብዛኛዎቹ የ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ናቸው፤ ሕዝቡ የሚኖርባቸው አንዳንድ የንግድና የግል መኖሪያ ቤቶች የተሠሩት በጭቃ ግድዳና በቆርቆሮ ጣሪያ ነው።

ኮረብታማው አካባቢ ካሉት የመንግሥት ተቋሞች መሃል፤ የጦር ካምፑና ደጃዝማች ገ/ ማሪያም ሆስፒታል በመባል ይታወቅ የነበረው ይገኛሉ። ሆስፒታሉ በኦጋዴን ክልል መሀከል የሚገኝ አጠቃላይ ሆስፒታል ነው። ጣልያን በጥሩ ሁኔታ ከሠራቸውም የድንጋይ ቤቶች መሃል አንዳንዶቹ የሚገኙት እዚሁ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ነው። ያን ሁሉ እርቀት አቋርጦ ለሄደ ሰው ያን የመሰለ መልክ ያላቸውን ቤቶች እዚሁ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲያይ ልዩ ስሜት ይፈጠርበታል። ከተማን የለመደም ሰው ትንሽ ከተማ የገባ ይመስለውና ዓይኑ የሚያርፍበት ያገኛል። ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ገብቶ በስተግራው በኩል ዓይኖቹን የሚያማትር ሰው ቢኖር ጥቂት ራቅ ራቅ ብለው የተሰሩ ሌሎች ቤቶችንና፣ ፈንጠር ብሎ የሚገኝ አንድ ብቸኛ ቪላ ቤትን ያያል። እኔና ጥበቡ የትዳርን ሀ ሁ የቆጠርንበት በአንድ ቤት ጣራ ሥር ሆነን የሰማይ አባታችንን ተልዕኮ ልንፈጽም ኑሮን የጀመርንበት ቤታችን ይህ ብቸኛ ቪላ ነው ። ሁለት መኝታ ክፍሎች፣ ባኞ ቤት፣ሳሎንና ምግብ ቤት፣ጥሩ መናፈሻ ያለው ሰፊ በረንዳ ፣ ወጥ

ቤት ከሪፍሪጅሬተር፣ ከኤሌክትሪክ ምድጃና መጋገሪያ ጋር ለልብስ ማጠቢያ ከተዘጋጀ ሰፍራና ለጓሮ አትክልት ከሚሆን ቦታ ጋር ያለው ቆንጆ ቤት ነው። ያስፈልጉናል ብለን ካልናቸው እቃዎች በስተቀር የሠርግ ስጦታዎቻችን ባብዛኛው በየካርቶኑ እንደታሸጉ የተውናቸው አዲስ አበባ ነው።

*የቤቱ ካህን*

ይህ መኖሪያ ቤታችን የእግዚአብሔር መንፈስ የሚመላለስበት ቤት እንዲሆን ደስ የሚያሰኘውንም ሁሉ ለማድረግ የሚከለከለው እንዳች እንዳይኖር ለጌታ በጸሎት አሳልፈን ሰጥተነዋል። ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውም ኢያሱና ሠይፉ ከአዲስ አበባ አብረውን በመምጣታቸው የእኔና የጥበቡ ትዳር የተጀመረው በአራት የቤተሰብ ቁጥር ነው። ሰይፉ በዕድሜው ከኢያሱ ታናሽና ልጅነትም የሚያጠቃው ሲሆን ኢያሱ ግን የጌታ ፍቅር የገባውና ገና በለጋ ዕድሜው ስለጌታ ዋጋ የከፈለ ወጣት ነው። ኢያሱና ሰይፉ የሚማሩት ጧት ጧት ስለሆነ ከሰዓት በኋላ በአብዛኛው እቤት ናቸው። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ከአዲስ አበባ ይዘን የመጣነውን ጓዝ ቦታ ቦታ አስይዘን የቀብሪደሃር ቤታችን ያማረ መልክ ያዘ። እኔም የቤት ውስጥ ኃላፊነቱንና በአምላኬ ፊት ሰፋ ላለ ጊዜ በጸሎት መቆየቱን እየወደድኩት መጣሁ።

ጠንካራ የቤተሰብ የአምልኮ ጊዜ በቤታችን እንዲኖረን እግዚአብሔር የተጠቀመበት የቤታችን ራስ አድርጎ የሰጠንን ጥበቡን ነው። በአዲሱ ቤታችን ሊኖረን ስለሚገባ የቤተሰብ የአምልኮ ጊዜ ተነጋግረን የወሰንነው ጓዛችንን ይዘን ቀብሪደሃር በገባን በመጀመሪያው ቀን ነው። ጠዋት በማለዳ የሁለት ሰዓት የቤተሰብ የአምልኮና የጸሎት ጊዜ እንዲኖረን ፕሮግራም አወጣን። አገሩ በረሀ ስለሆነና ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ሰፊ የ ዕረፍት ጊዜ ስለሚኖረን ቃሉን ለየግላችን የምናጠናበት ጊዜ መደብን። እኛ በየግላችንና እንደ ቤተሰብ ደግሞ በኅብረት፣ በጌታ ፊት ተያይዘን የምናድግበት መስመር ውስጥ ለመግባት ጊዜ አልፈጀብንም። ምንም እንኳ ጊዜዬን በጸሎት ለማሳለፍ ወስኜ ሥራዬን የለቀቅሁትና ባለሙሉ ጊዜዋ እኔ ብሆንም፣ የቤታችንን መንፈሳዊ አመራር የያዘው የቤቱ ራስ ጥበቡ መሆኑ ፤ የጥበቡ ልብ የተሞላው በምን እንደሆነ በግልጽ ያሳያል። ሚዛኔን የጠበቅሁ መንፈሳዊ ሚስት ለባሌም እውነተኛ ረዳት እንድሆን የጥበቡ መንፈስ ጠንካራነት አግዞኛል፤ ቤት የማቆንጀትና የማስማመር፣ የባልትናው ፣ የሹራብና የእጅ ሥራው፣ የልብስ ስፌቱ ሙያዎቼ፣ ከልወጣንና ከልታየን እያሉ ውስጤን ጥቂት አጨናንቀውታል። በኑሮዬ ቅድሚያ ልሰጠው የሚገባኝ ለከበረው መንፈሳዊው ሥራ መሆኑን እንድለማመደው ራሴን ማድረግ ነበረብኝ። ምክንያቱም የጥበቡ እርካታና ደስታ በሁሉም አቅጣጫ የነበረኝን "የሴት ቁንጮነት" አስረግጦ ማየትም ሆነ ማወቅ አልነበረም። ስለዚያኛው ማንነቴ ማለትም ስለባለሞያነቴ የዥላንጭል ያህል ዕውቀቱ ቢኖረውም፣ የጥበቡ ፍላጎት ታላቅ ባለሞያ ሴት ማግባቱን ማወቅ ሳይሆን፣ ታላቅ መንፈሳዊ ሴት ያገባ መሆኑን ማረጋገጥ ነበር። ጥበቡ ለአንዳንድ ጉዳይ ድንገት ወደ ቤት ጎራ ሲል ጸሎት ላይ ሆኜ ወይንም መጽሐፍ ቅዱሴን ሳጠና ካገኘኝ፣ "ጌታ ይባርክሽ! በርቺ! አንቺ እኮ የተባረክሽ ነሽ! ጌታ ሰፊ ጊዜ በፊቱ ሰጥቶሻል" ብሎ ሐሴት በተሞላ ልብ ወደ ሥራው ሲመለስ ብዙ ጊዜ ታዝቤዋለሁ። ጥበቡ በሥጋዊ ነገር ቤቱ ከሚትረፈረፍ መንፈሳዊው በረከት በዝቶለት ጾሙን ቢውልና ቢያድር ቅር የሚለው ሰው አልነበረም።

ባብዛኛው የቀብሪደሃር ቆይታችን አንድና ብቸኛ የሆስፒታሉ ሐኪም ጥበቡ ብቻ ከመሆኑ የተነሳ በሥራው ብዛት ምክንያት ለሚሰማው የሥጋ ድካም እንኳን ፊት መስጠት አይፈልግም። ነፍሱ ያለ ልክ የምትጠማውን መንፈሳዊ ጥማት ለማርካትም፣ አምላኩን በሌሊትና በቀን የሚፈልግ ሰው

እንደሆነ አስተውያለሁ። እግዚአብሔር በሰጠው መንፈሳዊ ሥልጣንና ብርታት የማከብረውና በሕይወቴም ትልቅ ስፍራ የምሰጠው የትዳር ጓደኛ ስለሰጠኝ አምላኬን አመሰግንኩ። ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለው ታላቅ ፍቅርና አክብሮት የጥበቡን የውስጥም ሆነ የውጭ ሕይወቱን ማንነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ከጥበቡ ጋር ጥቂት ጊዜ ያሳለፈ ሰው አምላኩን ደስ ለማሰኘትና አስከብሮ ለማለፍ ዓላማው የሆነ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አይፈጅበትም።

****



ጥበቡ ቀብሪደሃር የጦር መኮንኖች ሆስፒታሉን ሲያስጎበኝ

## እውነተኛ የሕዝብ ሐኪም

ወጣቱ ሐኪም የቤተሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት መጋቢና መሪ ብቻ አልነበረም። በሥራውም ዓለም ሌት ተቀን በቅንነት ሰዎችን ለመርዳት የማይደክመው በፍቅርና በትዕግሥት የሆስፒታል ሠራተኞቹን የሚያስተዳድርና የሚመራም ሰው ነበር ። ለሆስፒታሉ ያለው ሐኪም እርሱ ብቻ ስለሆነ ከሥራ ሰዓት ውጪ ቀን ቢሆን ሌሊት ድንገተኛ በሽተኛ ቢመጣ፣ ወይንም ከተኙት ሕሙማን ስቃይ ቢበዛባቸው የጤና ረዳቶቹ መጥተው ሲጠሩት፣ ያለመሰልቸት ፈጥኖ ለሕሙማኑ ይደርሳል። ብዙም ሳይቆይ ጥበቡ የህመምተኞቹን ስቃይ ለማስታገስ ችግራቸውን ለማቃለል እስከመጨረሻ የሚተጋ እውነተኛ የሕዝብ ሐኪም መሆኑ ይታወቅ ጀመር።

ጥበቡ ኃይለሥላሴ፣ *"የዩኒቨርሲቲው ምሩቅ ሁሉ ትላልቅ ከተማ ውስጥ ብቻ መሥራት የሚፈልግ ከሆነ ገጠሯ ኢትዮጵያ እንዴት ልትለማ ትችላለች? ለገጠሩስ ሕዝብ ከቶ ማን ሊደርስለት ይችላል?"* የሚለውን እምነቱን በተግባር ያዋለ ሰው ነው። ስለዚህም ጥበቡ በቀብሪደሃር ሕዝብ መካከል ራሱን ያገኘው እግር ጥሎት አልነበረም። በፍጹም ልቡ የሚያምንበት ጉዳይና የእግዚአብሔርም ፍጹም ፈቃድ በመሆኑ እንደሆነ ያውቃል። ስለሆነም ጥበቡ ከቀብሪደሃሩ ሆስፒታል የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በክብር ለመወጣት ሁለንተናውን ሰጥቶ በመሥራት ላይ ነው።

ሆስፒታሉ አምሳ ሕሙማን ለማስተኛት የሚችሉ አልጋዎች ያሉት፣ ከኦፕራስዮን ክፍሎችና ከፋርማሲው ጋር ተሟልቶ የተቋቋመው ነው። በተጨማሪም ሆስፒታሉ ለቀብሪደሃር ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን የአውራጃውም አጠቃላይ ሆስፒታል በመሆኑ በሽተኞች ከሩቅ ስፍራ ሁሉ መጥተው የሚታከሙበት ነው። አንዳንዴም ራቅ ወዳለ ስፍራም በቤታቸው በጭንቅ የተያዙ ሕሙማን ለመርዳት ጥበቡ ይጠራል። "አባክህ በነፍስ ድረስልን" የሚሉ ያገሬው ሰዎች መጥተው ሲለምኑት ጥበቡ ወደየግል ቤታቸው ሄዶ እርዳታም የሚሰጥበት ጊዜ ነበር። ታዲያ ከእነዚህ ባንዱ ቀን ሁለት ያገሬው ሰዎች (የኢትዮጵያ ሱማሌዎች) እቤት ድረስ መጥተው የአንዱ ሚስት መውለድ እንዳቃታትና ብዙ ደም እንደሚፈሳት ፈጥኖ አብሯቸው በመሄድ ካልረዳት መሞቷ እንደሆነ ይነግሩታል። የሆስፒታሉን አምቡላንስ ይዞ ሰዎቹን ጨምሮ ለእርዳታ ፈጥኖ ሲነሳ ልቤ ነፃነት አጣ። ስለዚህም እባክህ ብቻህን አትሂድ። ኢያሱና ሰይፉም አብረውህ ይሂዱ ብዬ ለመንኩት። የስጋቴ ምክንያት በጊዜው ግልጽም ባይሆንለት እነ ኢያሱን ይዟቸው ሄደ። ከብዙ ሰዓት በኋላ ቆይተው ወደ ቤት

ተመልሰው የነገሩኝ ነገር ገረመኝ። ምጥ የጠናባት ደም የፈሰሳት የተባለችው ሴትጋ ቢሄዱ ቢሄዱ አልደርስ አሉ። ሰዎቹ አመቺ ሰፍራ ሲደርሱ ጥበቡን ከነመኪናው አፍኖ ለመውሰድ ሃሳብ የነበራቸው እንደሆኑ ሲጠረጥር፣ አቅጣጫውን ቀይሮ ወደ ቤት በደህና መድረስ ችለዋል። በዚያን ቀን ግን ጥበቡን ያልኩትን እስከዛሬ አይረሳውም። "አሁን የቤተሰብ ኃላፊም ጭምር መሆንህን አትርሳ፤ ብቻህን በነበርክ ጊዜ እንደምትኖረው ዓይነት ኑሮ አይደለም የምትኖረው። የአንተ በአደጋ ላይ መውደቅ የቤተሰብህ በሙሉ አደጋ ላይ መውደቅ ማለት ነውና እባክህ ስለእኛም ስለምንወድህ ሰዎች ኑር" ነበር ያልኩት።

በቀብሪደሃር ሆስፒታል ታሪክ እንደ ጥበቡ ሕዝቡን ለማገልገል ቆርጠው በሰፍራው ለረዥም ጊዜ የቆዩ ቀደምት ሐኪሞች አልነበሩም። ስለዚህ የሆስፒታሉ ችግሮች እንደየአመጣጣቸው ሳይቃለሉ የኖሩ በመሆናቸው ከሕንጻው እድሳት አንስቶ የጥበቡን መላ የሚጠባበቁት አንድ ሺህ አንድ ጉዳዮች ተደንቅረዋል። እግዚአብሔር ግን የጥበብንና የማስተዋልን መንፈስ ያደለው ሰው ስለሆነ እሱ ከመጣ ወዲያ የሆስፒታሉ ችግሮች ተራ በተራ መቀረፍ ጀምረዋል። ጥበቡ በሕክምና መስክ ብቻ ሳይሆን ሆስፒታሉ እንደሚጠበቅበት አገልግሎት መስጠት እሚችልበት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ባለው ኃይሉና ችሎታው ሁሉ፣ ነገሮችን እንዲያያዙ አደረገ።

ሆስፒታሉን ማደስ በሚለው ዕቅዱ ውስጥ ካካተታቸው ዐቢይ ጉዳዮች አንዱ ሆስፒታሉ ውስጥ የተዘረጉትን የውኃ ቧንቧዎች በትክክል እንዲሰሩ ማድረግ ነበር። መድኃኒትና የመሳሰሉትን የሚያመላልሰው የሆስፒታሉ የጭነት መኪናም ተበላሽቶና ከአገልግሎት ውጭ ሆኖ ስለቆመ ተጠግኖ ሥራውን እንዲጀምር ማድረግ ሌላው ዕቅዱ ነበር። ሆስፒታሉ የደም ባንክ እንዲኖረውና ደም ለጋሾች ደማቸውን እንዲለግሱ በማድረግ የኦፕራሲዮን ክፍሉን አገልግሎት አጠናከሯል። ጥበቡ ራሱ ለሌሎች ዓርዓያ ለመሆን የራሱን ደም በየወሩ ይለግስ ነበር። ከጤና ጥበቃም ጋር ተጻጽፎ ለሆስፒታሉ አዲስ አምቡላንስ የማስመጣት ዕቅዱ ቻሳክቶለታል። እነዚህና እነዚህን የሚመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ የጥበቡን ታላቅ ትጋትና መሥዋዕትነት የሚጠባበቁ ነበሩ።

ጥበቡ ሰዎችን የማስተባበርና ነገሮችን ስርዓት የማስያዝ ተሰጥዖም ያለው ሰው ነው። ስለዚህ ለሥራው የሚያስፈልጉትን ሰዎችና የገንዘብ ኃይል በማሰባሰብ ሆስፒታሉን እንዲህ መልክ ባለው ሁኔታ ላይ ለማድረስ ያደረገውን ጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ስላሳካለት ደስ ብሎታል። ከእነዚህ አስተዳደር ነክ ከሆኑት ጉዳዮች ሌላ ግን ጥበቡ ዋናውና ሕዝቡን የሚረዳበት አገልግሎቱ የሕክምና ሙያው ነው። ቀብሪደሃር አብረን በነበርንበት ጊዜም ሁሉ፣ አስቸጋሪ ዓይነት ኦፕራስዮኖችን ማድረግ፣ በተለያየ ሕመም የሚያሰቃዩትን ሰዎች መርዳት፣ በአስጨናቂ የምጥ ስቃይ ተይዘው የሚመጡትን ሴቶች ማዋለድ የጥበቡ የዕለትና ዐቢይ ተግባራቱ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ የጥበቡን የማያቋርጥ መገኘት ቢጠይቁም ተፈፅመው በሚያያቸው ቁም ነገሮች ሁሉ ደስታው ትልቅ ሆኖለታል። ለዚህ ሕዝብ ማድረግና መሆን ለቻለው ሁሉ አምላኩን ያመሰግናል፤ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ ውስጥ እንዳለ በሕይወቱም ላይ ባለው መለኮታዊ ጥሪ ምክንያት በዚያ እርሱና ቤተሰቡ እንዳለን ያምናል።

****

*የድንጋዩ እሩምታ!*

በጥቂት ጊዜ ውስጥ ጥበቡ ለሕዝቡ ያለው ፍቅር የገባው ሁሉ አክብሮቱንና ፍቅሩን ሊገልጽለት ወደኋላ የማይል ሆነ። ከጥበቡ ጋራ ለአንዳንድ ምክንያት ወደ ከተማ ወጣ ያልን እንደሆነ በየመንገዱ ሰላምታ እየሰጡ ፍቅራቸውን የሚገልጹለት የአገሬው ሱማሌዎች እንኳን የቁጥራቸው ብዛት ያስገርመኝ ነበር!! የጥበቡ መለኮታዊ ጥሪ የእኔም ጥሪ እንደሆነ ገብቶኛል። ያ ሕዝብ ከዚያ የጥበቡ ሁለንተናዊ መሰጠት በስተጀርባ ያለውን ጌታ እንዲያይ ጸሎቴ ሆነ። የክርስቶስን ወንጌልና የመስቀሉን ፍቅር ወደ መረዳት ሕዝቡ እንዲመጣ ውስጤ መቃተት ጀመረ። ስለዚህም ቤታችንንና ልባችንን ለከተማው ሰዎች ክፍት አድርገን የትዳራችንን አምላክና ጌታ እንዲያውቁልን የቤተሰብ ጸሎታችንን ቀጠልን።

ሆኖም ግን በጊዜው በመስፋፋት ላይ የነበረው የኮሚዩኒዝም ፍልስፍና ተከታዮች የጥበቡንና የቤተሰቡን መንፈሳዊ ሕይወትና ኑሮ አልወደዱትም። የእርሱን ተወዳጅ ሐኪም መሆን በሚጻረር ኃይለኛ ጥላቻቸው ተመርዘው ሊቃወሙን መንቀሳቀስ ጀመሩ። ያ ዘመን የደርግ መንግሥት "እድገት በኅብረት" በሚል ተማሪዎችን ወደየገጠሩ ሁሉ ያዘመተበት ዘመን ነበር። ለዚሁ ዘመቻ ቀብሪደሃር የተመደቡ ወጣቶች በቤታችን እናደርግ ወደነበረው የቤተሰብ የአምልኮና የጸሎት ጊዜ መማረክ ጀመሩ። በአይዲዮሎጂው ተጽእኖ ምክንያት ከነበራቸው እምነት ደክም ብለው እንጂ አንዳንዶች ፊትም ጌታን ያውቁ የነበሩ ናቸው። የቤተሰባችንን ያለመናወጥ መቆም ሲያዩ ከእኛ ጋር ኅብረት ለማድረግ መምጣት ጀመሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቤታችን የወጣቶች መሰባሰቢያ ሆነ። ጌታ ያንዳንዶችን ሕይወት በቃሉና በመንፈሱ መለወጥ ስለጀመረ መንፈሳዊው እንቅስቃሴ ከሰዎች ግምት በላይ ሆነ።

ስለዚህ የሰውን ልጆች መዳን የማይወደው የጽድቅ ጠላት የሆነው ዲያቢሎስ ተቃዋሚዎችን አሰባሰበ። "አምላክ የለም" ባዮች፣ የኮሚዩኒዝም አይዲኦሎጂ ተከታይ ወጣቶች፣ ከጥቂት የሆስፒታሉ ሠራተኞች ጋር በማበር በታላቅ ቁጣ ተነሳሱ። በጥበቡና በእኛ በቤተሰቦቹ ላይ ጉዳት ለማድረስ የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ። ማታ ማታ ጨለማን ለብሰው "ሞት ለዶ/ር ጥበቡና ለቤተሰቡ"፥ "ጴንጤ ይውደም! የኢምፔሪያሊዝም ቡችሎች ይውደሙ!" እያሉ በመጮህ እቤታችን ላይ የድንጋይ እሩምታ መወርወር የየምሽት ተግባራቸው ሆነ። በጣሪያችንና በቤታችን ላይ በየማታው በሚወረወሩት ድንጋዮች አንድ ምሽት ከፊት ለፊት ያለውንና ወደ ቤታችን ውስጥ የሚያስገባውን ትልቅ የመስታወት በር በድንጋይ እንክትክቱን አወጥተውታል። ሆኖም ግን በዚህ እድራጎታቸው በማንኛችንም ላይ የሰውነት ጉዳት ሊያደርሱ እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። እንዲህ መሰል ሌሊቶች አንዳንዴ የሚነጉ ባይመስሉኝም ሁሉን በሚችል አምላካችን ጥላ ሥር ተተግነን ያልፉ ነበር። መንግሥትንም ሆነ ሕዝብን የበደልንበት አንዳች ነገር እንደሌለ እናውቃለን፤ ታዲያ ጠዋት ሲነጋ እነዚያ ጨለማን ተገን አድርገው ሲንጫጩ፥ ሠፈርም ሲረብሹ ከሚያመሹት ወጣቶች መሃል አንዱ እንኳን መጥቶ ጥበቡን ፊት ለፊት ደፍሮ የሚያናግረው አልነበረም።

በቤቱ የሚያካሂደውን የጸሎት ፕሮግሞችና ጥበቡም በግሉ የሚኖረውን መንፈሳዊ ኑሮ ያልወደዱት እንዲህ መሰል ሰዎች አመቺ ጊዜ እየተጠባበቁ እንዳሉ ከገባን ሰንብተናል። ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች የጥበቡን ትጉ ሠራተኛነት ሊያስተባብሉት አቅቷቸዋል። በሕዝብ ተወዳጅነቱም እንዲያ በቀላሉ ሊደባበቅ የማይቻል ሐቅ ሆኖባቸው ተቸግረዋል። በመሆኑም የወጠኑት ስውር ደባ ተግባራዊ እንዳይሆን ክፉ ደንቃራ ሆኖባቸዋል። አሁን ግን የተማሪዎቹ ተቃውሞ እየደራ ሲመጣላቸው የጥበቡ

መንፈሳዊነት ፈፅሞ ያልተስማማቸው አንዳንድ የሆስፒታሉ ሠራተኞችም እድሉን ለመጠቀም የተመቻቸላቸው መሰላቸው። ስለዚህ የወጣቶቹን ተቃውሞ በመደገፍ በስውር ሲጠነስሱ የሰነበቱትን ሴራ የሚያንጸባርቅ የክስ ደብዳቤ ጽፈው ወደ አዲስ አበባው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ላኩ።

*"ዶ/ር ጥበቡ በሽተኞቹን ሁሉ ልጸልይላችሁ እያለ በሕክምና አይረዳቸውም። መድኃኒት አይሰጣቸውም። በሽተኞችን እንዲያይ ስንጠራው አሁን መምጣት አልችልም ጸሎት ላይ ነኝ ይለናል"* የሚል ከእውነት የራቀ የክስ ደብዳቤ ነበር አዲስ አበባ ዋናው መሥሪያ ቤት የደረሰው። ስለዚህ ይህን ጉዳይ በሚመለከት አንድ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ቀብሪደሃር ተላከ። ኮሚቴውም በተሰጠው የማጣራት ሃላፊነት ከአዲስ አበባ ቀብሪደሃር ሲደርስ ክሱ ሁሉ መሰረተ ቢስ መሆኑን አገኘው። ስለዚህም ጥበቡ ኃይለሥላሴን ስለትጋቱና በሕዝብ ስለተወዳጅነቱ አመስግኖ ተመልሷል። ጥበቡ ግን ኮሚቴው የማጣራት ተልእኮውን ሲጀምርም ሆነ ሲጨርስ ከሆስፒታሉ ሠራተኞች መሃል ሴረኞቹ እነማን እንደነበሩ ቢያውቅም በእነርሱ ላይ ምንም ዓይነት የመከፋት ልብ አልነበረውም። እንደልማዱ በፍቅር አብሯቸው ሕሙማንን ሲጎበኝ፣ መሬት ተሰንጥቃ ብትውጣቸው እስኪመርጡ የደረሱም ነበሩ። የቀብሪደሃሩ የመጀመሪያው የአገልግሎት ዘመናችን ይህን በመሳሰሉ ትዝታዎች የተሞላ ብቻ አልነበረም። እምላካችን ስለሰጠን መንፈሳዊ ፍሬዎች በመንፈስ ዳግም ልደትን በማግኘት ወደ እግዚብሔር መንግሥት ስለተጨመሩልን እህቶችና ወንድሞች ጌታን ያመሰገንበት ፍሬያማ ዓመትም ነበር።

****

*"እምነት"*

እምነት የሚል መጠሪያ ስም ያወጣንላት የመጀመሪያዋን የበኩር ልጃችንን ከአምላካችን የበረከት እጆች የተቀበልነው የኔና የጥበቡ ትዳር በተመሠረተ በአሥር ወር ከአሥራ አራት ቀን ዕድሜው ነበር። ይህችን የበኩር ልጃችንን ለመውለድ ከቀብሪደሃር ይልቅ በቤተሰብ መሃል መሆን እንደሚሻል አስበን አዲስ አበባ መጥተናል። ፕሮፌሰር ሐምሊን የተሰኙት ጥበቡ በጣም የሚያከብራት ክርስቲያን ፕሮፌሰር፣ እንድታወልደኝ ለቀሩኝም ጥቂት ቀናት ከትትል ወደርሷ ወሰደኝ። ጥበቡ በመውለጃ ቀኔ ቢሆንለት ከምታዋልደኝ ሐኪም ጋር እማዋለጃው ክፍል ተገኝቶ የመጀመሪያ ልጁን አቅፎ ሊስም በናፍቆት ይጠባበቃል። ሆኖም ግን የቀብሪደሃሩ ሆስፒታል ሃላፊነት እንዲህ የሚያዝናና አልነበረምና እኔን አድርሶኝ እርሱ መመለስ ነበረበት። የእርግዝናዬ ወራት በፍጹም ጤንነት የተሞላ ነበር። ፕሮፌሰሯ የምትወደው ተማሪዋ የነበረው የጥበቡ አደራም ስለተሰማት፣ በማንኛውም ሰዓት ደውዬልኝ ብላ የቤቷንና የቢሮዋን የስልክ ቁጥሮች ሰጥታኛለች።

ጥበቡ ወደ ቀብሪደሃር በተመለሰ በሁለተኛው ሌሊት ወደ 10 ሰዓት ከሌሊቱ ሲጠበቅ የነበረው ምጥ መጣ። ከጠዋቱ 12 ሰዓት ቤተሰቦቼ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ወሰዱኝ፤አስፈላጊውን ምርመራ አድርጋ ከማዋለጃው ክፍል አልጋ እንድይዝ ያደረገቺኝ ነርስ "አሁን የመጀመሪያ ልጅሽን ስለሆነ የምትወልጂው ገና ወደ ምሽቱ 12 ሰዓት ገደማ ምጡ ቢያፋፍምሽ ነው" አለቺኝ። እኔም መለስ አደረግሁና "እሺ መልካም። ግን ፕሮፌሰር ሐምሊንን ስልክ ደውላችሁ ብትጠሩልኝና ብታየኝ የቤቷ የስልክ ቁጥር ይሄው" ያልኳት ነርስ ብስጭት በተሞላ አነጋገር "እሷ በራሷ ጊዜ ዋርዱን ለመጎብኘት ስትመጣ ታይሻለች እንጂ ስላንቺ ስልክ ልደውልላት አልችልም" አለችኝ። በዚያን ሰዓት ቤተሰቦቼን ገና ወደ ማታ ነው ምጡ የሚያፋፍማት ደግሞ፣ "እዚህ ማዋለጃ ዋርድ ውስጥ ማንም

ሰው መግባት ስለማይችል በአካባቢው ብትቆሙም ድካም ነው እንጂ ማንም አያስገባችሁም" ብላ አሰናበታቸዋለች። በወላጆቼ እንክብካቤ ሥር አብረን ያደግን ያጎቴ ልጅ ሲስተር አየለች ታየወርቅ የጋንዲ ሆስፒታል ነርስ ነች። "እሺ ይሁን እኔ ግን እንዳንቺው ነርስ ስለሆንኩ ልረዳትም ስለምችል እባክሽ ለእኔ ብትፈቅጂልኝ" ብትላት አሁንም ነርሷ ተበሳጭታ "እንኳን አንቺን ከሌላ ሆስፒታል የመጣሽውን ቀርቶ፣ እዚሁ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከሌላ ዋርድ የመጡ ነርሶችም እዚህ ማዋለጃ ክፍል አይገቡም። ስለዚህ ዘወር ብትሉ ይሻላል" በሚል ቁጣ አባራቸዋለች።

ስለዚህ መልእክቴን ለፕሮፌሰር ሐምሊን የሚነግርልኝ እንደሌለ ስላወቅሁ እርሷኑ መልሼ እሺ እንግዲያው ፍቀጂልኝና ወጥቼ ከሕዝብ ቴሌፎን ደውዬላት ልመለስ ብዬ ብጠይቃት *"ይቅርታ እዚህ ክፍል ከገባሽ በኋላ የምትወጪው ስትወልጂ ብቻ ነውና አርፈሽ ተኚ ሴትዮ"* ብላኝ አንድ አልጋ ብቻ ከሚገኝበት ክፍል ውስጥ አስተኝታኝ በሩን ዘግታብኝ ወጣች። አደራ ባዩ ጥበቡም ሆነ አደራ ተቀባይዋ ፕሮፌሰር ሐምሊን፤ እኔም የበኩር ምጥ የያዘኝ ባለጉዳይ ማንኛችንም ከገመትነው ውጪ ብቻዬን ነኝ። ከሚወዱኝና አጠገቤም ሆነው ሊንከባከቡኝ ከፈለጉት ቤተሰቦቼ ሁሉ ተለይቼ አንድ ክፍል ውስጥ በተዘጋብኝ በዚያ ማለዳ ልቤ ሊረባበሽ ዳዳው። አይ የእኔ ውድ ጥበቡ፤ ይሄን ሁሉ ታሪክ አላየ! አልኩ በውስጤ። እርሱ እንኳን እኔን አይደለም ማንኛዋንም ምጥ የያዛትን ሴት አዋልዶና እስከመጨረሻው ረድቶ ሳያጠናቅቅ ለነርሶች እንኳን አምኖ ትቶላቸው እንደማይሄድ አውቃለሁ። ለዚሁ ሲል ነበር ልቡ ወደሚያርፍባት ፕሮፌሰር ሐምሊን የወሰደኝ። የጋንዲ ሆስፒታልዋ እህቴ ሲ/ር አየለች "ለምን እኔጋ አትወልድም " ብላ እየጠየቀችው። ምነው እህቴ በምትሠራበት ለእኛም ልክ እንደቤታችን በነበረው ጋንዲ ሆስፒታል በሆንኩ ኖሮ፤ ይሄኔ እህቴና ጓደኞችዋ በግራ በቀኝ ሆነው በተንከባከቡኝ ነበር እያልኩ ለራሴና ለገባሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ አዝኜ ሆድ መባባት ይዘኝ ማለቃቀስ ስጀምር፣ ድንገት ከእንቅልፍ የመባነን ያህል ነቃሁ። ለካስ እነዚህ ሁሉ የሚወዱኝና አጠገቤ ኖረው ቢረዱኝ እያልኩ ከምፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ በላይ ሊረዳኝ ችሎታ ያለው አምላክ አለኝ! ጥበቡም ሆነ ሌሎች ቤተሰቦቼ ከሚወዱኝ ሁሉ በላይ የሚወደኝ የነፍሴ ወዳጅ ጌታ አምላኬ በውስጤና በዙሪያዬ አለልኝ። ድንገትም በዓይነ ህሊናዬ የእግዚአብሔር መላእክት እኔን ሊረዱኝ፣ የተረሳሁ ያህል ብቻዬን ከምገኝበት በዚያ መኝታ ክፍል ውስጥ ሽር ጉድ ሲሉ ታዩኝ። ብቸኝነቴና የሆዴ መባባት በሚገርም ዓይነት መጽናናት ተተካ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የምጡ ፍጥነትና መጠን እየጨመረ በላብ እየተጥለቀለቅሁ መጣሁ፤ አሁን ከጠዋቱ ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ሆኗል። ነርሷ ባደረገችው ምርመራና በእርግጠኝነት በተናገረችው መሠረት ከሆነ፣ እኔ ገና የምወልደው ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ ነው። *"ወይኔ አምላኬ! ምጥ ማለት ላካ ይሄ ነው? እንዴት አድርጌ ነው እስከ ምሽት ድረስ እንዲህ እያመመኝ የምቀጥለው?"*

የሚያጣድፈኝን የምጤን ሁኔታና የመውለጃሽ ሰዓት ገና ወደ ማታ ነው ተብሎ ተደጋግሞ የተነገረኝን ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ማስታረቅ አቅቶኝ፤ አምላኬና ጌታዬ ሆይ እንዴት አድርጌ ነው እስከ ማታ የምቆየው? አሁን ፈጥነህ እርዳኝ። እንዲህ ብቻዬን ባለሁበት ሁኔታ አትተወኝ፤ አሁን ድረስልኝ፤ ሆነ የእኔ ጸሎት። እኔ ይህን የሚመስል ሁኔታ ውስጥ በምገኝበት በዚያች ማለዳ ከምጥ የመገላገያ ሰዓታቸው የደረሰላቸውን ሴቶች *"ግፊ፤ አንድ ጊዜ እባክሽ፤ ጨኸቱን ተዪውና ይልቅ ዝም ብለሽ አምጪ፤ አሁን ግፊ"* ፤ አዋላጆቹ ነርሶች ሲሏቸው ላንዴና ለመጨረሻ ኃይለኛ የምጥ ጩኸት ካሰሙ በኋላ፣ ወዲያውኑ ተከትሎ የተወለደውን የሕፃን መራራ ልቅሶ ድምጽ ካለሁበት

ክፍል ባሻገር ከሚገኘው የማዋለጃ ክፍል በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ። በቁጥር ከሦስትና ከአራት የማያንሱ ሴቶች በአዋላጆቹ ቁጣና የሚያመነጫጭቅ ተግሳጽ መሃል ልጆቻቸውን ወልደዋል። *"ታድለው! እሰይ አምላኬ፤ እንኳን ደረሰላቸው"* ብዬ አመሰገንኩት። የሰውን ልጆች ሁሉ ለመርዳት በምሕረት ዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን ጌታ። እነዚያን የሚያስጨንቅ የምጥ ጣዕር ውስጥ በማለፍ ላይ የሚገኙትን ሴቶች ከማበራታትና ከማጽናናት ይልቅ ርህራሄ በጎደለው አነጋገር ስለሚያመናጭቋቸው አዋላጆች ግን መጸለይ ጀመርኩ። *"እባክህ ጌታ ሆይ የርህራሄ መንፈስ ስጣቸው! ምናልባት ሌሊቱን በሙሉ ያለዕንቅልፍ በሥራ ብዛት በማደራቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል እንዲህ የሚሆኑት . . ."* የሚገርመኝ እንዲህ በየመሃሉ በሚያጣድፈኝና ፍጥነቱ እየጨመረ በመጣው የምጥ ግፊት መሃል አምላኬ ይሰጠኝ የነበረው ሽልብታ፤ የሚጣፍጥና በዚያው ተኝቼ በቀረሁ የሚያሰኝ ዓይነት መሆኑ ነበር። ሆኖም በፊት ከነበረኝ ይልቅ ከፍተኛ በሆነ የምጥ ግፊት ኃይል ለመንቃት ተገድጄና በላብ ተዘፍቄ እንደገና ራሴን አገኘዋለሁ። አሁን በእኔ አስተያየት የመጨረሻው መጨረሻ ላይ ደርሻለሁ።

"እእእ... እእኡ... ኧረ ጌታ የሱስ ሆይ ድረስልኝ! በጌቴሴማኔ የደም ላብ እስኪያልብህ፤ ስለዓለምና ስለእኔ ኃጢአት ያማጥህ፤የጣር ሰው ጌታ የሱስ! እእ... እእእ...በቀራንዮ መስቀል ላይ ደምህን ያፈሰስክልኝ እእ.... በኃጢአት ምክንያት በሰው ልጅ ላይ ለወደቀው መከራና አበሳ ዋጋ ክቡር ነፍስህን አሳልፈህ የሰጠህ! እእ... እእእ...አንተ እኮ ለዚህ ሁሉ ጣዕሬ ነው ዋጋ የከፈልክልኝ። አሁን ድረስልኝ! እእእ . . . ሰዎችን ለስቃይ ጥሎ የማይዘነጋው የዚያ የቅን አገልጋይህ የጥበቡ አምላክ! እእእ...አልቻልኩምና ቶሎ ናልኝ!" ብዬ የእንባ ጸሎቴን ወደ አምላኬ ረጨሁ። ድንገትም አንድ የሚያስደንቅ ነገር ሆነ። የስጋዬና የነፍሴ ጌታ በዚች ክፍል ውስጥ የሆንኩትን ሁሉ አየና ከሰማያት አንገዳገደ ለረድኤቴም በደመናት ላይ እየተራማመደ ከተፍ አለልኝ። በዚህ ዓይነት የምጥ ጣዕር እስከማታ እንድትቆዪ አይሆንልኝም ሲል። ልጄን እምነትን በተኛሁበት አልጋ ላይ እንዳለሁ አምላኬ ያገላግለኝ ገባ። በዚህ ጊዜ ነበር በድንገት ልጄ ታፍና እንዳትጎዳብኝ አሁን እንኳን ሊረዱኝ ቢመጡ ብዬ "ኧረ ሰዎች ድረሱ! ልጅ ተወለደ! (ወንድ ይሁን ሴት የምወልደው ገና ስላላወቅሁ)... ኧረ እባካችሁ ድረሱ!" እያልኩ ጩኸቴን አቀለጥኩት! በአጠገቤም የነበረውን መጥሪያ በእጄ የምችለውን ያህል ሙጭጭ አድርጌ ይገፍ እየደወልኩ። በማዋለጃው ክፍል በዚያን ጠዋት ከነበሩት ወላጆች ብዛት የተነሳም የታከታቸው አዋላጆች ገና ማታ እንደምትወልድ የነገርናት ይቺ ቀበጥ ደግሞ ምን ያስጮሃታል? በሚል ልብ ይመስላል አመጣጣቸው፤ ዘና ብለው ነውና። ሆኖም ከማዋለጃው አልጋ ላይ ሳይሰቅሉኝ ከፍሌ ከተኛሁበት ልጄን በመውለድ ላይ እንደምገኝ የሚያየውን ዓይናቸውን ለማመን ያቅታቸዋል። ከዚያ በኋላማ *"እባክሽ አንድ ጊዜ ማዋለጃው አልጋ ላይ እስከናደርግሽ! ወደ ላይ ተንፍሺ! ወደ ላይ ተንፍሺ! እርጂን እባክሺን! ወደ ላይ... !"* በዚህ ሁኔታ ነበር የመጀመሪያ ልጃችን፤ እምነት ጥበቡ ሐሙስ ሰኔ 24 ቀን 1968 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4 ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ላይ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ የተወለደችው።

ምንም ዓይነት ያልተጠበቀ ነገር ቢከሰት በደስታ ሊረዱኝና ችግሩን ሊያስወግዱ የሚችሉ የጥበቡ መምህራንና ወዳጆች በብዛት እዚያ ስላሉ ተብሎ። ለካስ ለእኛ በጌታ ላለን ሰዎች የአምላካችን በውስጣችን መኖር ነው ዋና ቁም ነገሩ። ለካስ የትም ቢሆን የት በውስጣችንና በዙሪያችን በጎናችንና በአጠገባችን መሆን የሚቻለው አንድና አንድ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ለካስ ጊዜያትና ሁኔታዎች ሊከለክሉት የማይችሉት ጌታ እግዚአብሔርን ብቻ ነው! ለካስ በሌሊትም ቢሆን በቀን ደውዬልኝ ወዲያው እደርስልሻለሁ ያለቺኝ ፕሮፌሰር ሐምሊንን ፈቃደኝነቷ ብቻ በቂ አልነበረም! ሊያግዷት

የሚችሉ ደንቃራዎች፥ እክሎችና ሁኔታዎች፣ ከሺ በላይ ሊያጋጥሙ ይችሉ ኖሯል! በዚያን ቀን ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር፣ በጥልቅ ጸጋውና ምህረቱ ምክኒያት ውስጤን መኖሪያውና መቅደሱ ሊያደርግ ስለወደደው፣ ስለአምላኬ ስለእግዚአብሔር ፈጥኖ ደራሽነት ነው። ስለዚህም በሰው እንደተገመተው፣ ኋላ ወደ ማታ...እምሽቱ ላይ ሳይሆን... ገና በጠዋቱ አምላኬ በሰላም ገላግሎኛል።

****


ጥበቡ ሕፃን እምነትን ሲያጫውታት

## ልጄን ልያት!

አሁን ምጤን ብቻዬን ወደ ጨረስኩበት ወደ ቀድሞው ክፍሌ መልሰውኛል። ውጭ ውጪውን ሲንከራተቱ የዋሉ ወላጆቼና ቤተሰቦቼ በሰላም መገላገሌ የተነገራቸውም ከሰዓታት በኋላ ነው። አሁንም ሊገቡ አልተፈቀደላቸውም፤ እስር ቤት ውስጥ ያለሁ ያህል ተሰማኝ። ሁሉን እረስቼው ከቤተሰቦቼ ጋር ተቃቅፈን ተሳስመን ጌታን ለማመስገን ልቤ ቸኩሏል። ልጄንም አጸዳድተው ሌላ ሕፃናት ክፍል ስላስተኟት ገና አላየኋትም። ሆዴም ምግብ ፈልጎ እጅጉን ረሃብ ይሰማኛል። ከረሃቡ ይልቅ ግን የልጄን ዓይኖች ባይኔ ለማየት በእጆቼ እቅፌ ክንዴ ላይ ለማስተኛ ናፍቆቱ አስቸግሮኛል። አንዱ የዋርዱ ሐኪም በመጨረሻ ሊያየኝ ሲገባ "እባካችሁ ልጄን አጠገቤ አምጡልኝ ላያት እፈልጋለሁ" አልሁት። "ደግሞስ መቼ ነው ወደ ተያዘልኝ መኝታ ክፍሌ የምትወስዱኝ? ከቤተሰቤም መገናኘት አልቻልኩም?" ብዬ ሆድ በባሰው መልክ መጠየቄን አስታውሳለሁ። ሐኪሙም "እስካሁን ለምን ልጇን አላመጣችሁላትም? ወደ መኝታ ክፍሏም ትወሰድ እንጂ" ብሏቸው ከክፍሉ ወጣ። ከብዙ ጥበቃና ትዕግሥት በኋላ ልጄን እምነትን በሕፃን አልጋ አምጥተውልኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያት በውስጤ ተቀርጾ የቀረውን ትዝታ አሁንም አስታውሳለሁ። በጸጥታና በሚያስደንቅ ሰላም የተሞላው ገጽታዋ የሚነግረኝ ነገር ነበረው።


እኔና ጥበቡ ከእምነት ጋር

የሆነ መለኮታዊ ዕረፍት የተሞላበት በጸጥታና በእርጋታ የተሞላ ማንነት ያላት መንፈሰ ውብ ልጅ እንደሆነች። ምቾቱና ሙቀቱ በሚስማማት መጠን ሆኖላት፤ ለሕይወት የሚያስፈልጋትን ምግብ ሁሉ ያላንዳች ችግር ታገኝ ከነበረችበት የዘጠኝ ወር ቤቷ ወጥታ፤ እንግዳ ወደ ሆነው ዓለም ስትመጣ፤

ሌሎች ሕፃናት ምርርና እሪ ብለው እንደሚያለቅሱት ዓይነት ዋይታ አለማሰማቷ ትዝ ይለኛል። ይህቺ ከጥቂት ሰዓታት በፊት ከአብራኬ የተገኘች ሕጻን እንዲህ የሚል ድምጽ የለሽ አዋጅ የምታውጅልኝ መሰለኝ።

"ማሚዬ!"
ኀዘን ቢሆን ድንጋጤ ወይ ሁካታ
የሰይጣን ሽብር ጋጋታ
የመንፈሳዊ ሕይወትሽ ግንባታ
ቢጠናከርልሽ በጌታ ብትቆም ነፍስሽ ጸንታ
ባምላክሽ ኃይል ትሻገሪያለሽ የማዕበሉን ድንፋታ
አዲስ ኑሮን ለመጀመር የእፎይታ የማይበገር ሕይወት የማይረታ
የሰላም የፀጥታ የመታመን የእርጋታ።

ስለዚህ እኔና ልጄ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓይን ለዓይን የተያየን ዕለት ያ በመታቀፊያ ጨርቅ ተጠቅልሎ አጠገቤ የተኛ አዲስ ሕይወት በታላቅ እርጋታና ጸጥታ ተሞልቶ ያጫወተኝና የመከረኝ ታላቅ ቁም ነገር እንዲህ የሚል ነበር። እና እኔም "እሺ ልጄ! አሜን ይሁንልኝ!" በማለት በልቤ ጠብቄዋለሁ። የመልዕክቱ ዝርዝር ሃሳብ የገባኝ ግን በፊቴ በተደቀነው ቅርብ ዘመን ውስጥ ሊሆን ያለው ከሆነ በኋላ ነበር።

የገዛ ልጄን አዋልዶ ለማቀፍ እንዲያ በጉጉት ሲጠባበቅ ከነበረው አባቷ ቀድሜ ፤ የማቀፍና እነዚያን ውብ ለጋ ጉንጮቿን ለመሳም የታደልኩ እኔ እናቷ ነበርኩ። ከአልጋዋ ውስጥ አውጥቼ አጠገቤ ያስተኛኋት ይቺን መንፈስ ውብ ሕጻን የተጠቀለለችበትን ጨርቅ ፈትቼ ትናንሽ እግሮቿንና እጆቿን ሁለመናዋን አገላብጬ አየኋት። እጆቿንና እግሮቿን ጉንጮቿን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳምኩ፤ ያ አስጨናቂ ምጥ የተረሳው ወዲያው እንደወለድኩ ነው። እንኳን ምጡ፣ ተተከቶ ሆድ ሆዴን ይልሰኝ የነበረውም ረሃብ አሁን ተረስቷል። በሕጻን እምነት ላይ የሰፈነው መለኮታዊ እርጋታና ጸጥታ ከውስጧም የአዋጅ ያህል በነፍሴ የተሰተጋባው መልእክት ሁለንተናዬን ይዞታል። ከሰዓት በኋላ ወደ 10 ሰዓት አካባቢ ከቤት ተዘጋጅቶ በብዙ ልመና አጥሚት በፔርሙዝ ገብቶልኛል። ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ "ወደ መኝታ ክፍልሽ እንውሰድሽ" ተብዬ ያን የመሰል የማይረሳ ውሎ የዋልኩበትን የማዋለጃ ክፍል ለቅቄ ወጣሁ።

ጥበቡ ወደ ቀብሪደሃር ከመመለሱ በፊት ነበር ወልጄ የምተኛበትን የአንደኛ ማዕረግ ክፍል የያዝነው። አሁን ግን አምጥተው ያስተኙኝ ብዙ አልጋዎች ከሚገኙበት ከሶስተኛ ማዕረግ መሆኑን ሳይ ላመጡኝ ሰዎች ብነግራቸውም ጆሮ የሚሰጠኝ አጣሁ። ቤተሰቦቼ የሚጠብቁኝ በተያዘልኝ አልጋ አካባቢ እንደሚሆን ማለዳ ተነጋግረናል። አሁን እዚህ መሆኔን በምን ያውቃሉ? እንዴትስ ይሆን በመጨረሻ ልንገናኝ የምንችለው? እያልኩ አውጠነጥንና እጸልይም ገባሁ። ከተኛሁበት አልጋ አጠገብ የተኛች እመጫት ባለቤቷ አጠገብዋ ሆኖ ምግብ ያጎራርሳታል። ድንገት የጥበቡ ናፍቆት አገረሸብኝ። ዓይኖቼ እንባ ማቆርዘዝ ጀመሩ። እንባ በጋረዳቸው ዓይኖቼ ቁጋግ ውስጥ በሆስፒታሉ ኮሪደር እናቴና እህቶቼ ግራ በገባው መልክ ዝግ እያሉ ሲራመዱ ድንገት አየኋቸው። ከማዋለጃ ክፍል ከወጣሁ በኋላ የት እንዳለሁ ስለማያውቁ ነው። ከጎኔ ባለው አልጋ ላይ ባለቤቱን በመንከባከብ ላይ የሚገኘውን ሰው ፤ "እባክህ የኔ ወንድም ይቅርታ! ላስቸግርህ? አሁን በኮሪደሩ ውስጥ በዚያ አቅጣጫ (እያመለከትኩ) የሂዱት የእኔ ቤተሰቦች ናቸው የት እንዳለሁ ስለማያውቁ ብትነግርልኝ"

አልኩት። እግዜር ይስጠውና እሮጦ ሄዶ መልእክቴን አደረሰልኝ። ከምሽቱ ወደ 12፡45 ገደማ አገኘኋቸው። የቀኑ ውሎዬ ሁኔታ ነው መሰል እናቴንና እህቶቼን ሳይ የብሶት እንባዬን እስኪደነግጡ ለቀቅሁት። ከዚያ በኋላ ነበር ወደ ተያዘልኝም የመኝታ ክፍል የተወሰድኩት። ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር እርዳታ በጤናማ አወላለድ ከጤናማ ልጅ ጋር ስለተገላገልኩ ከሆስፒታሉ ብዙ የሚያስነብተኝ ችግር አልነበረኝም።

እኔም ሆንኩ ሕጻኗ ትንሽ እስክንጠነክር ናዝሬት ወደ ወላጆቼ መኖሪያ ቤት ተወስደን አንድ ወር ያህል እንደታረስኩኝ። እናቴ ኦጋዴንን እንድታየው፣ ለጥቂት ቀናትም አብራን እንድትሰነብት በአውሮፕላን ወደ ቀብሪደሃር ተጓዝን። በአውሮፕላን ማረፊያው ተገኝተው የተቀበሉን ጥበቡ ፥ ኢያሱና ሠይፉ ነበሩ።

ቀብሪደሃር ከገባን አንስቶ ልጃችንን ጥንቃቄና ፍቅር የተሞላበትን አባታዊ እንክብካቤ ሲያደርግላት ሳይ ፣ ጥበቡ ኃይለሥላሴ ተወዳጅ ሐኪም፣ መንፈሳዊ መሪ . . እግዚአብሔር የረዳው አፍቃሪ ባል . . እና ተንከባካቢ አባትም እንደሆነ ተመልክቼአለሁ። ለልጃችን ለእምነት ጤናማ እድገት የሚረዷትን የምግብ ዓይነቶች በፕሮግራም አውጥቶ የተመጣጠነ አመጋገብ እንድታገኝ ጥረት አድርጓል። ልጃችን እምነት የምግብ ፍላጎት እጅግም አልነበራትምና ከሥራው ሲመጣ እርሱ በዘዴ አንዳንዴም በማስገደድ ለሰዓቱ የተዘጋጀላትን ይመግባታል። አሁን ሕጻን እምነት እኔን ከምታውቀው ባልተናነሰ መንገድ አባቷን ታውቀዋለች። ገና ድምጹን ከሩቅ ስትሰማ በደስታ እግሮቿን ታወራጫለች። በንቃት ከቴውን ትጠባበቃለች። ስታየው ጥርስ ያላወጡትን ድዶቿን በደስታና በፈገግታ ትከፍታለች። በሰው ደረጃ ከእኔ ሌላ ጥበቡ የሚወዳት ልጅ ከአብራካችን ስለተገኘች ደስ አለኝ እንጂ አልቀናሁም። አንድ ወቅት ግን ሁለታችንም ወደርሷ የሚያደላ ፍቅር ስለታየብን ለእርስ በርሳችን ያለን ፍቅር እንዳይረሳ የተዋወስንበት ጊዜ ትዝ ይለኛል።


በዚያን ዓመት ከአብራካችን ከተገኘችው ከዚች ውብ ብላቴና ከእምነት ሌላ ትዳራችን ያፈራቸው መንፈሳዊ ልጆች ነበሩትና ልጃችን የተወለደችው እየሰፋ በመሄድ ላይ በነበረውና የእኔንና የጥበቡን የማያሰልስ መንፈሳዊ እንክብካቤ የሚያስፈልገው የጌታ ቤተሰብ መሃል ነበር። እምነት አሁን መዳህ ጀምራለች ። በዚያው አካባቢ ጥበቡ ለሥራ ጉዳይ አዲስ አበባ ሊሄድ ሆነ። እኔም እድሉን በመጠቀም ከትንሽ ጊዜ በኋላ በእግሯ ለመሄድ እንዲረዳት የሕጻናት ጋሪ (walker) ገዝቶላት እንዲመጣ ነገርኩት። እርሱ ግን በጌታ ሥራ ላይ በየዳራጉሩ ስለወንጌል የሚንከራተቱትን አገልጋዮች ጥቂት ጊዜም ቢሆን ገለል አድርጎ ወደ ቀብሪደሃር ማምጣትና ማሳረፍ እንዳለበት በልቡ በጣም ይጉላላል። ስለዚህ ከሄደበት የሥራ ጉዳይ ባሻገር በነበረው ትርፍ ጊዜ ለእነዚህ ወገኖች ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አጓጉዞ ማምጣት የልቡ ሸክም ሆኗል። ጥበቡ ወደ አዲስ አበባ ከሄደበት ጊዜ አንስቶ ልጃችን እምነት ከመዳህ አልፋ አንዳንድ እቃዎች እየያዘች መቆም ስለጀመረች የጋሪውን መምጣት በናፍቆት እጠባበቃለሁ። ጥበቡ እንዲያርፉ ካሰበላቸው አገልጋይ ቤተሰቦች ጋራ መጣ። በደህና በመድረሳቸው እጅግ ደስ ብሎኝ በመልካም አቀባበል ተቀበልኳቸው።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጥበቡ ካመጣቸው ጓዝ መካከል በጉጉት የምጠባበቀውን የልጃችንን የእምነትን ጋሪ ለማየት ስለቸኮልኩ ጠየቅሁት። የጥበቡ መልስ ጊዜ ስላጠረኝ እሱን አልገዛሁም የሚል ስነበር ከፋኝና ወደ መኝታ ክፍላችን ገብቼ አለቀስኩ። የእኔና የልጄ ነገር በጥበቡ የተረሳ መሰለኝ። ለእኔና ለልጄ ያለው ፍቅር ወሰኑ የተደፈረ መሰለኝ። ጥበቡ ደንግጦ ቢያባብለኝም እንዳዘንኩ ቆየሁ፤ በዚያ ሁኔታ ሳለሁ ለጸሎት ስንንበረከክ ልክ ጌታ ለማርታ የተናገራት ቃል ወደ እኔ መጣ። "...ማርታ

*ማርታ በብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ ትታወኪያለሽ የሚያስፈልግሽ ግን ጥቂት ወይንም አንድ ነገር ነው ማርያም መልካም እድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም" ያላት (ሉቃስ 10፡42) ።* በዚያን ጊዜ ነው ደንግጬ ንስሃ ገባሁ። ይቺ የሰጠኸን ብላቴና ፣ በጋሪም ሆነ ያለ ጋሪ እርዳታ አንተ በሰጠሃት እግሮቿ ጊዜው ሲደርስ ትሄዳለች። ስለዚህ እኔን ደካማዋን ይቅር በለኝ ፤ በማለት እራሴን አስተካከያለሁ።

ጥበቡ በጣም የሚያስደንቅ አክብሮት ለእግዚአብሔር ያለው ሰው በመሆኑ፤ ከሕይወቱ ብዙ ልማር የሚገባኝ ጉዳይ መኖሩን ልቤ ተረድቶታል። ከተጋባን ጊዜ አንስቶ ለጌታ አሥራት የምንሰጠው ከደሞዛችን 15 ከመቶ እንዲሆን ነው የወሰንነው። ለጌታ አሥራት ብለን ከለየነው ገንዘብ ዝርዝር ፍራንክ እንኳን አስፈልጎኝ ከዚያ በለውጥ እንድወስድ እስከማይፈቅድልኝ ለጌታ የለየነው ቅዱስ እንደሆነ ከጥበቡ ተምሬያለሁ። በጊዜው የጌታን ሥራ ለመሥራት በዱር በገደሉ ራሳቸውን ጥለው ወንጌልን በመስበክ ላይ የሚገኙ፤ ቤተክርስቲያናችን እንኳን ገና ያልተቀበለቻቸው፤ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ጉዳይ ታላቅ ኃላፊነት ይሰማው ነበር። ስለሆነም፣ የተላኩት ከጌታና በጌታ መሆኑን ስለእነርሱ የመንፈስ ምስክርነት ጥበቡ ላገኘባቸው የሚሰማው ሸክም ከፍተኛ ነበር። እግዚአብሔር በሕይወቱ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንደሰጠው ያህል ስለነዚህ ጥበቡ ሲገደው አውቃለሁ። ስለዚህ ተስማምተን እንዲህ ለመሰሉ የወንጌል አገልጋዮች ከደሞዛችን የለየነው አለ። ጥበቡ ግን በዚህም አይበቃውም። እንዲህ የመሰሉትን የወንጌል አርበኞች ቀብሪደሃር በነበረው ቤታችን እያመጣ ገለል አድርጎ ሊያሳርፋቸው በትህትና ዝቅ ብሎ እግሮቻቸውን እያጠበ ሊያገለግላቸው ይናፍቃል። ደስታውና እርካታው ያን ማድረግ ሲሳካለት እንደሆነ ገብቶኛል። ስለዚህ ይህን የክርስቶስን ዓይነት ልብ እኔም በአምላኬ ፊት ወድቄ ለመለመን ቆርጬ ተነሳሁ።

****



ቀብሪደሃር ጥር ወር 1969 ዓ.ም.

# 9

## ሰርኩላሩ !

ጥበቡ አዲስ አበባ በሄደበት አካባቢ ለየት ያለ ነገር ይሰማኛል። እርግዝና መሆኑን ግን አላወቅሁትም ነበር። ለካስ ሁለተኛ ልጃችንን የአራት ወር ነፍስ ጡር ኖሬያለሁ ! በመጀመሪያውም ሆነ በዚህ በሁለተኛው እርግዝናዬ ጤናዬ ከወትሮ ምንም ስላልተዛባ የቤት ውስጥ ፕሮግራሜም ሆነ ሥራዬ ያለመተጓጎል ቀጥሏል። የመውለጃ ጊዜዬ ሲደርስ ግን አንድ ነገር ወሰንኩ። ለመውለድ አዲስ አበባ ድረስ መሄድና እንዳለፈው መጉላላት እንደማያስፈልገኝ። እዚህም ሆነ አዲስ አበባ እኔን የሚያዋልደኝ እግዚአብሔር እንደሆነ ተምሬያለሁ። *"ባንተ ሥራ ጫና ምክንያት ዳግም በሌለህበት መውለድ አልፈልግም። ስለዚህ ሁለተኛ ልጃችንን የምወልደው እዚሁ ቀብሪደሃር ነው"* ስል ለጥበቡ ውሳኔዬን ነግሬዋለሁ።

በዚህ ዓመት አጋማሽ ላይ የቀብሪደሃር አካባቢ የፀጥታ ሁኔታ በጥቂቱም ቢሆን ደፈራርሷል፤ የሱማሌ ደፈጣ ተዋጊዎች ከሐረር ወደ ቀብሪደሃር የሚመጡትን የጭነትና የሕዝብ መመላለሻዎች ለመዝረፍ የተደጋገመ ሙከራ አድርገዋል። ስለዚህ እንዲህ መሰል የጭነትና የሕዝብ መመላለሻዎች በወታደር ኮንቮይ እየታጀቡ ሆኗል አጋዴንን የሚያቋርጡት። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አውሮፕላን ወደ ቀብሪደሃርና ጎዴ ያደርግ የነበረው ሳምንታዊ በረራ ከተቋረጠ ሰንብቷል። በጊዜው ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በነበራት ጦርነት ሳቢያ የደርግ መንግሥት "ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር" በማለት ወታደሮቹን ወደ ሰሜን ያጓጉዝ ስለነበር። በዚህም ምክንያት ከጂጂጋ የተነሱና በቀብሪደሃር አልፈው እስከ ጠረፍ ወዳሉት የሚሽን ጣቢያዎቻቸው የሚሄዱ አንዳንድ ሚሲዮናውያን በቤታችን የሚከርሙና የምናስተናግዳቸውም እንግዶች ብዙ ነበሩ። ከዚህ ሁሉ ሁኔታ ቀደም ሲል ከጥበቡ ጋር አብሮት ሊሠራ የተመደበ ዶ/ር ኤፍሬም ዓለማየሁ የተባለ ከነርስ ባለቤቱና ከቤተሰቡ ጋር ቀብሪደሃር መጥቷል። ደስ አለኝ። ከጥበቡ ጋር አብሮ ሊሠራ የሚችል እቻ የሥራ ጓደኛ መገኘቱ። ነርስ ባለቤቱም ሆስፒታሉ ካሉ ነርሶች በተጨማሪ የቆየ የሥራ ልምዷ ሆስፒታሉን ይረዳል ብዬ። የእነርሱ መምጣት ያደረገልን ሌላ በጎ ነገር ጥበቡ የዓመት ፈቃዱን ሊወስድ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠሩ ነበር። ስለዚህ ጥበቡ ለመውለድ ብዬ አዲስ አበባ መሄድ እንደማልፈልግ በመገንዘቡ ስፍራውን የሚሸፍንለትም ሁለተኛ ሐኪም አሁን ስላገኘ የሥራ ፈቃዱን

ለመውሰድ ወሰኖ እንዲህ አለኝ። "አንቺ አዲስ አበባ ለመውለድ ካልፈለግሽ እንገዲያው ለምን የዓመት ፈቃዴን ወስጄ ትንሽ አርፈን ዘመድ አዝማዶቻችንን ወገኖቻችንን ዓይተን አንመጣም? በዚያውም የመውለጃሽ ጊዜ ሲቃረብ እማማ (እናቴ) እዚህ እንዲመጡና አጠገብሽ እንዲሆኑ አመቻችተን እንምጣ፤ ለማንኛውም የምንሄደው በአውሮፕላን ስለሆነና በረራው መቼ እንደሚጀመር ስለማናውቅ በአእምሮአችን እንዘጋጅ። ምናልባት ጌታ ቢፈቅድ የዛሬ አ ሥራ አምስት ቀን እንበል?"

እኔም በሃሳቡ እጅግ ተስማምቼ ጌታ ቢልና አውሮፕላኑ ቢመጣ መዘጋጀት ጀመርኩ። በዚያን ወራት የአውሮፕላን ተሳፋሪዎች በየሳምንቱ እቃቸውን እየያዙ ምናልባት በዚያን ቀን በረራው ቢጀመር በማለት ሄደው ከንጓዛቸው በቤታችን በኩል በሚያልፈው መንገድ ወደየመጡበት ሲመለሱ ሳይ ስንብቻለሁ። ጥበቡና እኔም ለዕረፍት ወደ አዲስ አበባ የመሄድ እቅድ ስናወጣ የዛሬ አሥራ አምስት ቀን የሰዎቹ ዕጣ ሊደርስን እንደሚችል ማንም ሊገምት ይችላል። ቢሆንም እኔ ለመዘጋጀት ቆርጫለሁ። ይህን በተመካከርን በሦስት ቀን ጊዜ ውስጥ ግን ጥበቡ ከሥራ ሲመጣ አውሮፕላኑ ጌታ ቢፈቅድ በዚህ ሳምንት ይመጣል ብለን እንመንና ሻንጣችንን እናዘጋጅ አለኝ። በበረራው መቋረጥ ምክንያት በዚያን ወራት የነበረውን የመንገደኞች መጉላላት በ ዓይኖቼ ሳይ ከርሜያለሁ። ሆኖም ግን አውሮፕላኑ ላይመጣ ይችላል የሚለውን ግምት ወዲያ ጥዬ የጥበቡን አነጋገር በእምነት ተቀበልኩ።

ዝግጅታችንን አጠናቀን እቤት ለሚቀሩት ለኢያሱና ለሠይፉም አስፈላጊውን ሁሉ አመቻችተን ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ሄድን። በዚያች በማትረሳኝ ቀን ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲያስተጓጉል የከረመውን በረራ ቀጥሎ በናፍቆት የሚጠባበቁትን ተጓዦች ሊወስድ ከተፍ አለ። የተሳፋሪዎቹ መጠን ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ሁሉን ሰው ማሳፈር አልተቻለም። እኔና ጥበቡ ግን ከልጃችን ጋር በዚያን ቀን ቀብሪደሃርን እንድንለቅ ከአምላካችን የተቆረጠ ጉዳይ ነበር። ስለዚህም መቀመጫ ተሰጥቶን ወደ ድሬዳዋ በረራ አደረግን። አዲስ አበባ ከመሄዳችን በፊት ሐረር ከተማ ለሚገኘው የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት የሚያደርሰው መልእክት ነበረው። በዚያም የሚገኙትን የሥራ ባልደረቦቹንም ለማየት ከድሬዳዋ ከተማ ወደ ሐረር አመራን። እኔንና ልጃችንን እምነትን ከሻንጣችን ጋር ሐረር ራስ ሆቴል አሳረፈንና ጥበቡ ወደ ጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት ሄደ። መልእክቱን ካደረሰ በኋላ የዓመት ዕረፍቱንም ወስዶ ወደ አዲስ አበባ ቤተሰቡን ይዞ እየተጓዘ እንደሆነ ይነግራቸዋል። በዚህን ጊዜ ነበር ሰዎቹ በመገረም አልሰማህም እንዴ ያሉት። ባገሪቱ ማንም የጤና ባለሙያ ላልተወሰነ ጊዜ የዓመት ዕረፍት እንዳይወስድ ከአዲስ አበባው ዋና መሥሪያ ቤት ሰርኩላር መተላለፉን። ነገሩ ሲመረመር ለካስ የተባለው ሰርኩላር ቀብሪደሃር እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያልደረሰው የአውሮፕላኑ በረራ ለረዥም ጊዜ በመተጓጎሉ ኖሯል። እኔና ጥበቡን ከቀብሪደሃር ያወጣው አውሮፕላን ነው ገና ያን ሰርኩላር እዚያ የሚያደርሰው!! ቀደም ሲል ባወጣነው እቅድ መሠረት ከቀብሪደሃር የምንነሳው ከሁለት ሳምንት በኋላ ቢሆን ኖሮ የሚሆነውን መገመት ትችላላችሁ። በሰርኩላሩ ወደ ቀብሪደሃር መድረስ ምክኒያት ጥበቡ ዕረፍቱን ላይወስድ ኖሯል። እኔም በእርግጠኝነት ስለራሴ እንደማውቀው የጥበቡን ዕረፍት ማግኘትና ከሥራ ጫናው ገለል ማለቱንም ናፍቄው እንጂ፣ እሱ ለዕረፍት መውጣት እንደማይችል ስረዳ የእኔንም ጉዞ ጭምር መሰረዜ የማይቀር ነበር። ለካስ ሁለተኛ ልጃችንን ቀብሪደሃር የመውለዱ ሃሳብ የእኔ እንጂ የጌታ አልነበረም። ስለዚህም ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን እቅዳችንን ከፍቅር በመነጨ እቅዱ ለመተካት ወስኗል። ለካስ ከፊታችን ባሉ ገና ባላየናቸውና ባላወቅናቸው ቀኖቻችንን ውስጥ ሊሆን ያለውን ሁሉ በዝርዝር የሚያውቀው አምላካችን እግዚአብሔር የተላለፈውን ሰርኩላርና ጥበቡ እንዳይገናኙ በኪነ ጥበቡ አድርጓል። ያ

ወቅት ሊያስከትል ከሚችለው አስደንጋጭ ፍጻሜ ቤተሰባችን እንዲጠበቅ ለካስ አምላካችን ጣልቃ መግባቱ ኖሯል።

የሐረሮቹ ባለስልጣኖች ጥበቡን ለሥራ ጉዳይ አዲስ አበባ ብቅ ካለባቸው ወቅቶች በስተቀር የዓመት ፈቃድ የሚባል እስከአሁን እንዳልወሰደ ያውቃሉ። ምንም ቢሆን ምን ለትጉ ሠራተኝነቱ የሚገባውን ይሄን ዕረፍት መነፈግ እንደሌለበት ያስባሉ። ስለዚህ እንዲህ አሉት። "አንተ ይህ ዕረፍት እንደሚገባህ እናምናለን። ዝም ብለህ ድምጽህን አጥፍተህ ሂድ። መልካም ዕረፍት ! " ጥበቡ በሆነው ነገር እየተገረመና እየተደነቀ ወዳረፍንበት ወደ ራስ ሆቴል ሲመጣ ያለኝን አልረሳውም። እግዚአብሔር አምላክ በዚህ ዕረፍት ምክንያት አድርጎ ከቀብሪደሃር አውጥቶናል።እንደ ደንቡ ቢሆን ከቶ ልንወጣ በማንችልበት ወቅት። ስለዚህ ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ ያለውን የጌታን ሃሳብ ለመረዳት አጥብቀን መጸለይ ይኖርብናል። ሆኖም ግን ያለ ደንቡም ቢሆን ጥበቡን እንዲሄድ ስለፈቀዱለት ሰዎች ይበልጡን ተገርሜ በእርግጥ በዚህ ጊዜ ያወጣን ጌታ ምን ዓላማ ይኖረው ይሆን?ብዬ ጥቂት አሰብኩ።

ያም ሆነ ይህ አሁን ዋናው ነገር ከጥበቡ ጋር ነኝ። አብረን እናርፋለን፤ አብረን እንጸልያለን፤ አብረን የጌታን ሃሳብ እንጠይቃለን። ብቻ እንኳን ይህ የ ዕረፍት ጊዜው ከጥበቡ አልተወሰደ፣ በማለት እውነተኛና ጻድቅ ፈራጅ የሆነውን አምላኬን ከልቤ አመሰገንኩት። ሕጻን እምነትን ይዘን ሁለተኛ ልጃችንን የአምስት ወር እርጉዝ ሆኜ አዲስ አበባ ገባን። ከቤተሰቦቻችንና ከወገኖቻችን ሁሉ ጋራ መልካም ናፍቆት የመወጫያና የሰከነ ኅብረት ማድረጊያ ጊዜ አምላካችን ሰጠን። ከዚሁ የዕረፍት ጊዜው ጥቂት ቀናት ወስዶ የቅርብ ጓደኞቹንና ወገኖቹን ዶ/ር ብርሃኑና ዶ/ር ሚልኪያስን ለማየት ባሌ ጎባ ሄደ። ለእኔ የአውቶቡሱ ጉዞ ስለማይመቸኝ ቀረሁ እንጂ። የእኔ ወላጆች መኖሪያ ቤታቸው ናዝሬት ስለነበር ዕረፍታችንን በአዲስ አበባም በናዝሬትም ነበር ያደረግነው።

ናዝሬት ከሳለፍናቸው የዕረፍት ቀኖቻችን መሃል በአንዱ ቀን የናዝሬት ኃይለማሪያም ማሞ ሆስፒታል ዳይሬክተር የነበሩት አሜሪካዊው ዶ/ር ዮደር ጥበቡን ሊያነጋግሩ እንደሚፈልጉት መልእክት ደረሰን። ከዚህ በፊት ጥበቡም ሆነ እኔ በግል አናውቃቸውም። የደርግ መንግሥት ሆስፒታሉን ከሚሸኑ የመውረስና ሚሲዮናውያኑን የማሰናበት እቅድ እንዳለው ዶ/ር ዮደር አውቀዋል። ሆስፒታሉን ያቋቋመው ሜኖናይት ሚሽንም ሆነ ዶ/ር ዮደር የናዝሬትና አካባቢዋን ህዝብ ለዓመታት አገልግለዋል። ስለዚህ ሆስፒታሉን የማስረከቡ ጉዳይ እንደማይቀርላቸው ሲረዱ በተመሰከረለት ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ሐኪም እጅ ቢተዉት እንደሚሻል ያስባሉ። ዶ/ር ዮደር ይህን ሸክማቸውን ያካፈሉዋቸው ክርስቲያኖች የጥበቡን ናዝሬት ለዕረፍት መምጣት ይነግሯቸውና በቀጠሮ እንዲገናኙ ይሆናል። ዶ/ር ዮደር ለጥበቡ በልባቸው ያለውን ሸክም በዝርዝር አጫውተውት የኃይለማሪያም ማሞን ሆስፒታል የዳይሬክተርነት ቦታ ጥበቡ ቢወስድላቸው ደስ እንደሚላቸው ነገሩት። እርሱም በጥሞና ካደመጣቸው በኋላ የእርሱ በዚህ ሆስፒታል የመሆን ጉዳይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በሀሳቡ ሙሉ በሙሉ እንደሚስማማ ይገልጽላቸዋል። የተረጋገጠውን መልስ ግን የሚነግራቸው ጥቂት ጊዜ ወስዶ ከጸለየና ከጌታ መልስ ካገኘ በኋላ መሆኑን አስረድቶ ወደ ቤት ይመጣል። የተከፈተው ይህ በር ከጌታ መሆኑን ለማወቅ በጉዳዩ አጥብቀን ጸለይን።

በአእምሮ ቢታሰብ ናዝሬት ያኔም ቢሆን ሞቅ ያለች ከተማ የእግዚአብሔርም መንግሥት ወንጌል የወደረኞቹን ስደትና ተቃውሞ እየጣሰ ብዙ መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራባት ከተማ ናት። ወላጆቼም እዚያው ከተማ ስለሚኖሩ ለእኛ በዚያ መኖር በብዙ መልኩ የተመቸ ስፍራ ይሆናል፤

በፊታችን ወለል ብሎ እንዲህ በተከፈተው በር አለመግባቱ በስጋ ቢታሰብ ቂልነት ነው። ሆኖም ግን የአምላካችንን ሃሳብ አስረግጠን ለማወቅ ፈለግን። ለጸሎታችን ምላሽ ጌታ ስላልሰጠን ደፍረን መወሰን አቃተን። የቀብሪ ደሃሩ ተልእኮአችንን ገና እንዳልጨረስን ስለተሰማን ለዶ/ር ዮዶር የ"አይሆንም"ን መልስ ሰጥተን ወደ ቀበሪደሃር ለመመለስ ልባችን ተነሳሳ።

ወደ ቀብሪደሃር የምንወስዳቸውን አስቤዛ ያመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ አዘጋጀን። እናቴም በምወልድበት ጊዜ ቀብሪደሃር እንድትመጣ ባሰብነው መሠረት ልታርስኝ የሚያስፈልገውን ሁሉ ከወዲሁ እንድታዘጋጅ ተመካከርን። ከእነዚህ የመጨረሻ የዕረፍት ቀኖቻችን መሃል ግን ናዝሬት እያለን በሁለት ተከታታይ ቀኖች ውስጥ ጥበቡ ያየው ህልም አሳሰበን። ለእኔና ለእናቴ እንድንጸልይበት ነበር የነገረን። የሕልሙ ትርጉም በጊዜው እኛም ሆንን እርሱ አልገባንም። ለቀብሪደሃርም ሆነ ለእኛ እውን እንዲሆን የማንፈልገው ነገር ነበርና። በተከታታይ ያያቸውን ሕልሞች ጥበቡ ሲነግረን እንዲህ ነበር ያለን። *"የሱማሌ የጦር አውሮፕላን ቀብሪደሃር አርፎ ታላቅ ጦርነት ሲደረግ አየሁ! በማግስቱ ደግሞ ሌላ ተመሳሳይ ሕልም አየሁ። አንቺ ከእኔ ጋር የለሽም፤ እኔን ግን የሶማሌ ወታደሮች ሲያባርሩኝ አየሁ እንጃ ምን ይሆን የዚህ ትርጉም ? በፊታችን ጠላታችን ያዘጋጀው ክፉ ወጥመድ እንደሆነ ይሰማኛል። አምላካችን ግን በዚሁ ሁሉ ላይ ድል እንዲሰጠን እንጸልይ።"* ለጌታም ሁለንተናችንን አሳልፈን ሰጠነው። ከአምላካችን ዘንድ የተሰጠን እድል ፈንታችን ቀብሪደሃር መሆኑን አሁንም አምነን ተቀበልን። ለእኛ ሰላማችንና ደህንነታችን በእሳት ውስጥም እንኳን ማለፍ ቢሆን በአምላካችን ፍጹም ፈቃድ ውስጥ መገኘት ነው አልን።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለን ዕረፍታችንን አገባደድነው።ማብቂያው ላይ ግን ወደ አዲስ አበባው ጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት አንዱን ቀን ጥበቡ ብቅ አለ።ከላም ለማለት በመጀመሪያ የገባው በጊዜው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ወደነበሩት አቶ ወጋየሁ ቢሮ ነበር። ከኃለ ሰላምታቸው በስተጀርባ ጥበቡን በማየታቸው እጅግ የተደሰቱም ይመስላል። ከሰላምታቸው በኋላም ቀጠል አድርገው *"ዶ/ር ጥበቡ ለዕረፍት ወደዚህ መምጣትህን ሰምተን እንዴት እንደምናገኝህ ተቸግረን ሳለን ነው አሁን የመጣኸው ። መቼም ዕረፍት የሚገባህ ሰው እንደሆንክ አውቃለሁ። እስከዛሬ ያለ ዕረፍት ቀብሪደሃር ወስጥ መሥራትህን አላጣነውም። ያን ሕዝብ እንዳንተ ያገለገለ ስለሌለ በጣም ነው የምናመሰግንህ። አሁን ግን በቅርብ ቀብሪደሃር የተመደበው የሥራ ባልደረባህ ዶ/ር ኤፍሬም እንዲቀየር በጠየቀው መሠረት ባሁኑ ወቅት ወደ ለቀምት ተዛውሮ ጓዙን በማንቀሳቀስ" ላይ ነው። እንግዲህ ለዚያ ሕዝብ ያለኸው ያው አንተ ብቻ ነህ። እና የሆስፒታሉ ሥራና በሽተኞች እንዳይበደሉ እባክህ በቶሎ ብትመለስልን ? ካይሆን ዕረፍትህን በሌላ ጊዜ ደግሞ ትወስዳለህ።"*

ከቀብሪደሃር በወጣን በዚህ አራት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የተለዋወጠው ሁኔታ ጥበቡን ገረመው። የሥራ ባልደረባው እንዲህ ባጭር ጊዜ የቀብሪደሃር ነገር በቅቶት ወደ ነቀምት መዛወሩም። ለቀብሪደሃር ሆስፒታል ይህ አዲስ ታሪክ እንዳይደለ ያውቃል። እኔና ጥበቡ ግን ሁለተኛ ዓመታችንን ልናጠናቅቅ ነው። እኛን ወደዚያ ስፍራ የወሰደን የእግዚአብሔር ሃሳብ ገና እንዳላበቃ ስለገባን። የያዘን የጌታ ፈቃድ ጉዳይ ስለሆነ እንጂ ከቶውኑ ናዝሬትን በመሰለ ጥሩ ከተማ በተከፈተልን የሥራ በር ዘው ማለቱ አቅቶን አልነበረም። ስለዚህ የእኛ አድራሻ የአምላካችን ፈቃድ ባለበት በዚያ ነውና ልቡ ቅንጣት ያህል ወደ ኋላ ሳይልና ሳያመነታ *"እግዜር ይሰጥልን ስለ መልካም ሃሳብዎ። ዕረፍቴን ጨርሻለሁ። ቤተሰቤንም ይዤ ለመመለስ በዝግጅት ላይ ስለምገኝ ባስቸኳይ ወደ ቀብሪደሃር እጓዛለሁ"* አላቸው።

****

*ያቺ ማለዳ!*

ይህ ትልቅ እፎይታ ነበር ለአቶ ወጋየሁ። ስጋታቸው ጥበቡም ወደዚያ አልመለስም ቢል ነበርና። የመብትና የግዴታ ነገር ቢነሳ ጥበቡ ከሚጠበቅበት በላይ ግዳጁን የተወጣ ሐኪም እንደሆነ ያውቃሉ። እይደለም ሌሎች ትናንሽ ከተሞች አዲስ አበባም ቅያሬ ቢጠይቅ የሚገባው ሰው እንደሆነ። አሁን ግን የጤና ጥበቃ ስጋት ተወገደ። እኔም ቤት ነበርኩና የሆነውን ሊነግረኝ ከዚያው ከጤና ጥበቃ ቢሮ ስልክ ደወለልኝ። እኔ እንግዲህ ባስቸኳይ ቀብሪደሃር መድረስ ስለሚኖርብኝ አንቺ ትንሽ ዕረፍትሽን አራዝመሽና ቆይተሽ ብትመጪስ አለኝ።



የእምነት ጥበቡ አንደኛ ዓመት

ጥበቡ ሌት ከቀን ከነበረበት የሥራ ጫናና ኃላፊነት ለጥቂት ቀናትም ቢሆን ገለል ብሎ በማረፉ፤ ትልቁን ደስታዬን እምላኬ ፈጽሞታል። ከዚህ በኋላ ተጨማሪ ዕረፍትም ሆነ ቆይታ ጥበቡ በሌለበት አያምረኝም። ስለዚህ እኔም አብሬህ ነው የምሄደው እንጂ እኔ ካንተ ተለይቼ እዚህ አልቆይም። ልናደርግ ያሰብነውን ሁሉ እንድንፈጽም አምላካችን እረድቶናል አልኩት። ከዚያም ተያይዘን ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ትኬት ቢሮ ሄድን። ወደ ቀብሪደሃር ለመጓዝ የቦታ ጥበት መኖሩ ተነገረን። ቦታዎች ሁሉ በመያዛቸው ቢያንስ ሁለት ወር መጠበቅ እንደሚኖርብን አወቅን። በሕዝብ ማመላለሻው አውቶቡስ እኔን በዚያ ሁኔታ ከሕጻን ልጅ ጋር ይዞ ለመሄድ ፈጽሞ አይታሰብም። ኮንቮይ በመጠበቅ ብዙ መጉላላትና ጊዜ መፍጀትም አለበት። ጥበቡ በጣም ተጨነቀ። ዶ/ር ኤፍሬም ወደመሃል አገር በመጓጓዝ ላይ ካለ የቀብሪደሃሩ ሆስፒታል ያለ ሐኪም መቆየቱ ነው። ሕሙምተኞችም ሊቸገሩ ነው። ሆስፒታሉ ለሕዝብ ሊሰጥ የሚገባው አገልግሎት ሊተጓጎል ነው። ያን የቀብሪደሃርና ያካባቢውን ምስኪን ሕዝብ በፍቅር ያገለግል ዘንድ ጥበቡ የእግዚአብሔርና የአገር አደራ እንዳለበት ያምናል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባስቸኳይ ቀብሪደሃር ሊያደርሰው ባይችል ሁለት ወርና ከዚያም በላይ እጁን አጣምሮ መቀመጥ አይሆንለትም። ጥበቡ ሁለት መንገዶች ብልጭ አሉለት። የፈንጣጣ መከላከያ ድርጅትና የአየር ኃይል፤ ሁለቱም በተለያየ ጊዜ ወደ ቀብሪደሃር በረራ ያደርጋሉ፤ ስለዚህ በመጀመሪያ የፈንጣጣ መከላከያ ድርጅትን አነጋገረ። በቅርቡ የሚያደርጉት በረራ ካላቸው እንዲወስዱን። እንደሌላቸው ሲነግሩት ወዲያውኑ ደብረዘይት ወደሚገኘው አየር ኃይል ስልክ ደውሎ ችግሩን አስረዳ። በጊዜው የአየር ኃይል አዛዥ ከነበሩት ከጄኔራል ታዬ ጥላሁን ጋር በስልክ አገናኙት፤ የእርሳቸውም መልስ *"በሁለት ቀን ጊዜ ውስጥ ለወታደሮች ራሽን የሚያቀብለው አይሮፕላናችን ስለሚሄድ በደስታ ልንወስድህ እንችላለን"* የሚል ነበር። ጥበቡ ይህን ሲሰማ እጅግ ደስ አለው፤ ፈጥኖም ሌላ አንድ ተጨማሪ ጥያቄ ጠየቃቸው፤ *"ጄኔራል መቼም በጣም ነው የማመሰግነው፤ ነገር ግን እኔ ብቻዬን አይደለሁም። ባለቤቴና የዘጠኝ ወር ሕጻን ልጅ ከነጓዛችን ነን። ለሁላችንም ቦታ ይገኝልን ይሆን?"* ሲላቸው ጄኔራል ታዬ አፍታም ሳይዘገዩ፤ *"ምንም ችግር አይግባህ ዶክተር! ሁላችሁንም ከነጓዛችሁ ልንረዳችሁ እንችላለን። አንተ ብቻ ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት ደብረዘይት አየር ኃይል ድረስ ቤተሰብህን ይዘህ ተገኝ!"* ሲሉት ጥበቡ ከልብ አመስግኖ ስልኩን ይዘጋል። ሁለቱንም ስልኮች ሲደዋውል አዲስአበባ ካረፍንበት ከታላቅ ወንድሜ እቤት ሆነን ነበርና አጠገቡ ሆኜ ሁኔታውን

ተከታትያለሁ። ሁለታችንም ደስ አለን። አብረን የምንሄድበት መንገድ ስለተገኘ። ወዲያው ለወላጆቼ ስልክ ደወልንና መሄጃያችን በሁለት ቀን ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ስንነግራቸው ሊሰናበቱን መጡ።

ያን ምሽት ሁላችንም ባረፍንበት በወንድሜ ቤት ተሰባስበን ሳለን ስልክ ተደወለ።ከቀብሪደሃር ወደ ለቀምት ተቀይሮ ጓዙን ያነሳው ዶ/ር ኤፍሬም ነበር። ለትልቅ ምክር ነበር አደዋወሉ፤ አዲስ አበባ እስኪደርስ ምናልባት እንዳንተላለፍ ብሎ መስጋቱ ነው ከድሬዳዋ ሆኖ የሚደውለው፤ *"ቀብሪደሃር እናንተ ለዕረፍት ወደ አዲስ አበባ ከመጣችሁ ጊዜ አንስቶ የጸጥታ መደፍረስ ይታይባታል፤ የሶማሌ ደፈጣ ተዋጊዎች ከተማው ውስጥ እንኳን ሰርገው እየገቡ ነው። ስለዚህ እኔ ወደ ቀብሪደሃር እንድትመለስ ፈጽሞ አልመክርህም፤ ወደሌላ ቦታ ቅያሬ ጠይቅ ይበቃሃል። አንተ ብቻ ነህ እንዴ እዚያ መሥራት የሚኖርብህ?"* ነበር የዶክተር ኤፍሬም የስልክ ጥሪው ቁም ነገር። ጥበቡ ወደ ቀብሪደሃር የመመለሱ ጉዳይ የጌታ ፈቃድ እንደሆነ ያውቃል። ሆኖም ግን ይህን መንፈሳዊ ነገር ለዚህ የሥራ ባልደረባው መንገሩ ግራ ሊያጋባው እንደሚችል አስቦ ከቀብሪደሃር የማይቀርበት ሁለተኛውን ምክንያቱን ይገልጽለታል። *"ኤፍሬም የምትለው ይገባኛል። ግን እኮ ለአቶ ወጋየሁ እኔ ቀብሪደሃር እንደምመለስ አረጋጨላቸዋለሁ። እንደ ገና ቃሌን ማጠፍም ይቸግረኛል። አሁን ደግሞ አንተም ስለሌለህ ያ ሕዝብ ያለ ሐኪም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይወድቃል።"* ዶ/ር ኤፍሬምም መልሶ *"እንግዲያው አንተ መሄድ አለብኝ ብለህ ከወሰንክ ሊሻንና ልጆቻችሁን እምነትን በዚህ ሁኔታ ይዘህ ወደ ቀብሪደሃር እንድትመለስ አልመክርህም"* አለው። ጥበቡም *"ያን ማድረግ እችላለሁ። ሊሻንና እምነትን ይዤ መሄድ አሁን አይኖርብኝም። እስቲ እኔ መጀመሪያ ልሂድና ያለውን ሁኔታ በግሌ ልመልከተው"* ብሎ ጥበቡ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ጆሯችንን ጥለን በከፊል እናዳምጥ የነበረውን ጉዳይ በዝርዝር ተረከልን።

በሁሉም ሰው ፊት ላይ ጥልቅ ሃሳብ ውስጥ የመግባትና የመደናገጥም ሁኔታ ይታያል። የኔው ግን ከእንባ ጋር ተቀላቅሎ ከውስጤ የወጣ ውሳኔ ነበር። በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የሠርጋችን ዕለት የገባሁት ቃል ኪዳን ትዝ አለኝ ። ከሞት በቀር እኔን ከጥበቡ የሚለየኝ አይኖርም። "እንዴት እንዲህ ያለ ውሳኔ ትወስናለህ? ባይሆን ካስፈለገ ልጆችንን ቤተሰቦቻችንጋ ትተን መሄድ እንችላለን እንጂ እንዲህማ እየተባለ አንተ ሄደህ እኔ በምንም ተአምር እዚህ አልቀርም!" ቤተሰቦቻችን በሙሉ ድምጽ በእኔና በልጆችን በእምነት እስከጊዜው አዲስ አበባ መቆየት ተስማሙ፤ ባለቅስ ብንሰቀሰቅ በዚያ ምሽት ማን ሰምቶኝ ።

*"እንዲህ ነፍሰ ጡርና ደካማ ሆነሽ፤ ከሕጻን ልጅ' ጋር ወደዚያ ልሂድ ብለሽ እኛንም አታስጨንቂን ። እንዲህ ሆነሽ ልሂድ ብትይ ጥበቡንም ሆነ እዚህ ያለነውን ሁሉ፣ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው የሚሆነው። እንዲያውም ከመጣሽ አይቀር ለምን አንደኛውን ከወለድሽ ወዲያ አትሄጅም። እስከዚያ አገሩም ይረጋጋል"* አሉ ወላጆቼና ወንድሜ። ጥበቡ ደግሞ የተሻለ ሃሳብ እኔን ለማጽናናት ሲል አቀረበ፤ *"አሁን እኔ ቀብሪደሃር እንደ ደርስኩ ሁኔታውን በደንብ አጣራለሁ።ደህና ጥለነው የመጣነው ከተማ፤ ኤፍሬም እንደሰጋው ዓይነት ሁኔታ ይኖራል ብዬ ለማሰብ ያስቸግረኛል። ሆኖም ግን ኤፍሬም ለእኛ አስቦ አንተ እንቢ ካልክ እሺ ሊሻንን አትወሰዳት እያለኝ ብወስድሽ መልካም አይሆንም። እኔ አሁን ልሂድና ሁሉንም ላጣራ። ደህና ከሆነ እዚያ መጥተሽ ነው የምትወልጂው። ጌታ ቢፈቅድ እንዳሰብሺው፤ እኔ ባለሁበት።"*

የእኔ ሃሳብና ለቅሶ የማናቸውንም ተቃውሞ ሊያሸንፍልኝ ባለመቻሉ ከፋኝ። ከዚያች ምሽት በኋላ ጥበቡ ባለበት እኔ እንዳልገኝ የተፈጠረው አዲስና ያልታሰበ ሁኔታ በጽኑ ሆደን አባባው።

ሆኖም ግን ከአቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ለቀረበው ሃሳብ መረታት ነበረብኝ። በድንገት ጥበቡ ብቻውን ሂያጅ እኔና ልጃችን እምነት ቀሪዎች መሆናችን እንደ ከፋ ቅዠት ያህል ሆነብኝ። ጥበቡ ከእኛ ተለይቶ ወደ ቀብሪደሃር በሚሄድባት በዚያች ማለዳ እንባ ባቆረዘዙ ዓይኖቼ፣ ባስቸኳይ ሁኔታውን አጣርቶ እኛም ከእርሱ ጋር እንድንሆን እንዲያደርግ ቃል አስገባሁት። እርሱም በእኔ ሆድ መባባት መንፈሱ ታውኮአል። እኔን ቢያጽናናኝ ብሎም፤ ቃል ገባልኝና ተሰነባበትን። ዓይኖቼ በእንባ ጭጋግ እንደተሸፈኑ ጥበቡ ከእኔ እየራቀ እጆቹን እያውለበለበ ሄደ። ያቺ ማለዳ እኔና ጥበቡ በማንገናኝባቸው አስደንጋጭ ዓመታት እንደምትተካ ከምላከችን በቀር ማን ያውቃት ኖሯል?

****

*"እዚያው ብትወልጂ ይሻላል"*

ጥበቡ ቀበሪ ደሃር ከደረሰባት ቀን አንስቶ የእኔ መባባት ትዝ እያለው በሚያረጋጋው ድምጹ በሬድዮ ኦፕሬተር አማካይነት ያነጋግረኝ ጀመር። የስልክ መስመር ቀብሪደሃር ስለሌለ የምንነጋገረው በዚያ መልኩ ነበር። በእርግጥ ሁኔታዎቹን እንዳመዛዘነው ከሆነ የሚታይና የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ነገሮኛል። ጥበቡ የእኔ ነገር ስላሳሰበው በሬድዮ ብቻም ሳይሆን ረዣዥም ደብዳቤዎችም ይጽፍልኝ ነበር። እኔ እሱ ወዳለበት ለመሄድ በጉጉት እየተጠባበቅሁ ሳለ የጥበቡ ደብዳቤዎች እንደ ወትሮው ሁሉ በእምነትና በእግዚአብሔር ቃል የተሞሉ ከመሆናቸው ሌላ አንዳንድ የማይገቡኝ ድርጊቶችና ውሳኔዎች ይዘው ይደርሱኝ ጀመር። በአንደኛው ደብዳቤ ለምሳሌ፤ ትምህርት ቤት በሰኔ እንደተዘጋ ኢያሱንና ሠይፋን ወደናንተ እልካቸዋለሁ። አንቺም እኮ ከእንግዲህ መውለጃሽ ሐምሌ ስለሚሆን አንደኛሽን እዚያው ብትወልጂ ይሻላል ብዬ አሰብኩ ብሎኛል። እኔም ለምን ይህ ይሆናል? የእኔ ባጠገብህ አለመኖር ሲገርመኝ ለምን ልጆቹን ትልካቸዋለህ? አገሩ ሰላም አይደለም ወይ? ካልሆነስ አንተ ራስህ ይዘሃቸው ለምን በቶሎ ወደኛ አትመጣም?

እነዚህ ጥያቄዎቼ ሳይመለሱ ጥቂት ቆይቶ ሌላ ደብዳቤ ደረሰኝ። የቤት እቃዎቻችንን በዝርዝር ጽፎና በተለያዩ ካርቶኖች በጥንቃቄ አሽጎ ከላከበት ሊስት ጋር። ይሄኛውም ደብዳቤው በብዙ የሚያጽናኑና እምነት የሚጨምሩ የተስፋ ቃሎች የተሞላ ነው። እቃዎቹን በሚመለከት ሲጽፍልኝ ግን "እንዲሁ አንዳንድ እያልኩ ብልክ ይሻላል ብዬ ነው" ነበር ያለኝ። እናም ግራ ገባኝ፤"ከቀብሪደሃር ተቀይረን ይሆን? ከሆነስ ለምን በደብዳቤው አይገልጽልኝም?"

ለእነዚህ ጥያቄዎቼ መልስ ሳላገኝ ጥበቡ የእኔንም የእሱንም ልብሶች በሻንጣ እያደረገ በሚመጣ ሰው ሁሉ ይልክልኝ ገባ። ትምህርት ቤቱም ሲዘጋ ኢያሱ ብቻህን ጥዬህ አልሄድም ስላለው ታናሽ ወንድሜን ከሌላ እቃዎች ጋር ባይሮፕላን አሳፍሮ ላከው። በዚህ ጊዜ ነበር በውስጤ የታጨቁትን ጥያቄዎቼን የሚመልስልኝ አሁን አገኘሁ ያልኩት። ወንድሜን ፊትለፊት ሳገኘው የሚሰጠኝ ፍንጭ ቢኖር ብዬ አጥብቄ መረመርኩት። ያም ለእንቆቅልሼ መልስ አልሆነም። ምክንያቱም ትንሹ ወንድሜ በውል የገባው የሰማውም ሆነ ያየው አስፈሪ ነገር ስላልነበረ ነው። ቀብሪደሃር ሰላም ነው። ጋሽ ጥበቡ እቃዎቹን ዝም ብሎ መላክ ስለፈለገ ነው ሆነ የወንድሜ መልስ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እኔም ቀብሪደሃር ሳለሁ ይቀርበንና እንጠያየቅ የነበር አንድ የአየር ኃይል ወጣት የመጨረሻውን ሻንጣ ይዞ ከሌላ ደብዳቤ ጋር ናዝሬት ወላጆቼ ቤት መጣ። አሁን ገና ለጥያቄዬ ሁሉ መልስ የሚሰጠኝ ሰው አገኘሁ ብዬ ደስ አለኝ። የዚያ ወጣትም ስም ጥበቡ ነበርና "እባክህ ጥበቡ እውቱን ንገረኝ፤ ቀብሪደሃር ሰላም አይደለም? የሚያሰጋ ጦርነት ካለም ሁሉንም አንድም ሳታስቀር ንገረኝ፤ ለምን

እንደሆነ ሳይገልጽልኝ፤ ጥበቡ የቤታችንን እቃ ልብሶቻችንን የራሱም ሳይቀር እያነሳ ይልካል፤ ነገረኝ! እጸልያሁ እንጂ እኔ ምንም አልሆንም፤" ብዬ እንባ ባቀረሩ ዓይኖች ተማጸንኩት። እስከዛሬ የጥበቡን ደብዳቤዎች መልእክቶች እየያዙ የመጡ ሰዎች ሁሉ ምንም አጥጋቢ መልስ አልሰጡኝም። ይህ ሰው ግን የሠራዊቱ አባል ነው። እንግዲህ እሱ የሚሰጠኝ መልስ የእንቆቅልሼ ፍቺ ይሆንልኛል። የቀብሪደሃርንና ያካባቢዋን ሁኔታ እርግጠኛውን ያሳውቀኛል አልኩ በውስጤ፤ የዚያ ወጣት የአየር ኃይል ባልደረባ መልስ ግን "የዶ/ር ጥበቡ ነገር ለእኛም ሁሉ ገርሞናል።እኔ አሁን ያመጣሁልሽ የመጨረሻውን ሻንጣ ነው። አልጋችሁንም እንኳን ሊልክ አዘጋጅቶ ግርግዳ አስይዞ አቆሞታል። የአውሮፕላን ቦታ እስኪያገኝ። እሱ የሚተኛው የሆስፒታል አልጋ አስገብቶ ነው። እኔ ግን የተቀየራችሁ ነው የሚመስለኝ። ይሄንኑ ጠርጥሬ እኔም ጠይቄዋለሁ። አብረውት የሚሰሩ ነርሶች አጠገቡ ስለነበሩ እንዳይከፋቸው ብሎ ነው መሰል አይ ምንም ነገር የለም እንዲያው ዝም ብዬ ነው የምልከው ብሎኛል" ነገሩ አሁንም ስላልገባኝ አቋርጬው፣"እሺ ታዲያ ለእናንተ እንደዚያ ይበላችሁ፤ ለእኔ ግን ለምን በደብዳቤው እንኳ አይገልጽልኝም" አልኩት። እሱ ግን ለራሱም ጥያቄ የሆነበትን ጥያቄዬን በመመለስ እንቆቅልሼን ሊፈታ እንደማይችል ስለገባው በግልጽና በሰው ደረጃ፣ እንደ አንድ ወታደር ያለውን እውነተኛ ግንዛቤ ሊያስረዳኝ ንግግሩን ቀጠለ።

"ስለቀብሪደሃር ግን አንዳች ስጋት አይግባሽ። ቀብሪደሃር የሰፈረው የኢትዮጵያ የጦር ብርጌድ የዋዛ እንዳይመስልሽ። ሱማሌዎችን ምን ያህል እንደሚያርበደብዳቸው መቼም ሳታውቂ አትቀሪም። እርግጥ የሱማሌ ደፈጣ ተዋጊዎች ቀብሪደሃርን ለማጥቃት አንዳንድ ሙከራዎች አድርገው ነበር። የቀብሪደሃር ነዋሪ ሱማሌዎች ራሳቸው ምናልባት የደፈጣ ተዋጊዎቹ መዘዝ እንዳይመለከታቸው ስለፈሩ በአንድ ሌሊት ውስጥ ከተማዋን እንዳለ ጥለው ጠፍተዋል። እንደምታውቂው የኦጋዴን ሶማሌዎች የሁለቱም አገር ዜግነት ያላቸው ያህል በፈለጉት ጊዜ እዚያና እዚህ የሚሉ ናቸው። ታዲያ ቀብሪደሃርን ባንድ ሌሊት ጥለው ከጠፉ ወዲያ ጦሩ ከተማዋን 24 ሰዓት አሁን በመቆጣጠር ላይ ነው። በከተማዋ ዙሪያ በሙሉ ሌትና ቀን ጥበቃ ይደረጋል። አንድም ሱማሌ በሌትም ሆነ በቀን ዝር እንዳይል። ከዚህ በተረፈ የሆስፒታሉ መግቢያዎች ሁሉ በታንክ ይጠበቃሉ። ምንም እንኳን የእናንተ ቤት እዚያው ግቢ ውስጥ ቢሆንና የተሟላ ጥበቃ በዙሪያው ቢኖር ቤታችሁን ብቻ የሚጠብቅ አንድ ታንክ ቆሞላችኋል። ደግሞ ዶ/ር ጥበቡ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ቢያስፈልገው ሙሉ ጥበቃ ተደርጎለት ነው። ቀብሪደሃር ሰላም ነው። ይልቅስ ኢሃፓ አሁን ካሁን ደፋቹኝ እያልኩ በመገላመጥ ብዛት እኔ እዚህ ከመጣሁ ነው በመንገድ ላይ እንኳን ለመሄድ ነጻነቴን ያጣሁት። የቀብሪ ደሃር ሰላም በስንት ጣዕሙ! ደግሞ ሶማሌ በየትኛው አቅሟ የኢትዮጵያን የጦር ኃይል ትችላለች?" ሲል ከልቡና እውነቱን በሰው ደረጃ የሚያውቀውን ሁሉ ነገረኝ። ይህን የምለው ከጊዜ በኋላ ከዚያ ሰው ጋር ተገናኝተን እሰቲ እንደው አሁን ካለፈ እውነቱን ንገረኝ። ያኔ የነገርከኝ ሁሉ ከልብህና ከእውነት ነበር ወይንስ እኔን ለማጽናናት? ብዬ ጠይቄው እርሱ እስከተረዳው ድረስ የነገረኝ ትክክለኛ ሪፖርት እንደነበር አረጋግጦልኛል። ለነገሩ በእለቱ የሰጠኝን ዝርዝር ማብራሪያዎች ሁሉ ከልቡ እንደነገረኝ እኔም በውስጤ አልጠረጠርኩትም። የቀባባውና የደባበቀው ነገር እንደሌለ ያኔም ቢሆን ገብቶኛል። እሱ ያላወቀው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሊሆን ያለውን ነው እንጂ የነገረኝስ ሁሉ የሚያውቀውን እውነት ነበር። የሰው ልጅ ዕውቀት ውስን ነው። እነዚህም የጦር ሰዎች ምንም ዓይነት የጦር ስልትና ልምምድ ኖራቸው ዕውቀታቸው ምድራዊ ዕውቀትና ውስን ሊሆን ግድ ነውና።

****

## *ፍጻሜው ምንድነው?*

ጥበቡ ኃይለሥላሴ መንፈሳዊ ሰው ነው። የእርሱ መረዳት የተለየ ነበር። በውጭ በስጋ ዓይን በገሃዱ ዓለም የሚታይና ተጨባጭ ነገር ባይኖርም ነፍሱን ግን የገባት የሆነ ነገር ነበር። ቀብሪደሃር ከተመለስ ወዲህ ሲጸልይ በመንፈሱ የተገነዘበውና ሊሆን ያለውን ዝርዝር ሁኔታ እግዚአብሔር አምላክ ግልጥልጥ አድርጎ አይንገረው እንጂ መንፈስ ቅዱስ በጭላንጭል ያሳየው ነገር አለ። እንዲያውም በዙሪያው ካለው የመንፈሱ ግንዛቤ የተነሳ አምላኩን በጾምና ጸሎት፤ ጌታ ሆይ የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድነው? እባክህ ግለጽልኝ ብሎ ጠይቶት አንድ ሕልም አሳይቶታል። ስለዚያ ሕልም ሲነግረኝ እንዲህ ነበር ያለኝ። *"በሕልሜ እራሴን አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አካባቢ ሙሉ ልብስ እንደለበስኩ በመንገድ ላይ ስሄድ አያለሁ። ሰዎች ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ ድረስ በመገረምና በመደነቅ ይመለከቱኛል። ከታላቅ ጦርነትና መከራ እንደወጣሁ ስለራሴም በሕልሜ ውስጥ እረዳለሁ፤ የሰዎቹም መደነቅ "አንዳች ጉዳት እንኳን ሳይደርስበት!" ከሚል የተነሳ እንደሆነ ይገባኛል።"*

ስለዚህ ጥበቡ የዚህ ሕልሙ ትርጓሜ ሙሉውን አይሁን እንጂ በከፊል ገብቶታል። የሚያልፍበት መከራ አለ። ጌታ ግን ብደህና አዲስ አበባ ያስገባዋል። ደግሞም ከዚሁ ጋር አያይዞ ናዝሬት ሰረፍት ላይ ሳለን ያያቸው ሁለት ተከታታይ ሕልሞችም የሚያመለክቱት ያንኑ ይመስላል። ስለዚህ የጌታ እርዳታና ኃይል ስለሚያስፈልገው አምላኩን በጸሎት በመጠየቅ ሰንብቷል።

እኔንም በደብዳቤዎቹና በሬዲዮ መገናኛም አማካይነት ስንገናኝ በጽኑ የሚያጽናኑና እምነት የሚገነቡ የጌታ ቃሎች ሊሞላኝ ይፈልግ የነበረው ያለምክንያት አልነበረም። እኔም እንደተመኘሁት ሁለተኛ ልጃችንን የመውለጂያዬ ቦታ ቀብሪደሃር እንደማይሆን ጥበቡ ተረድቷል። በዚህም ምክንያት ነበር "እዚያው ትንሽ ብትቆዩ" ከዚያም "እንዲያውም እዚያው ከወለድሽ በኋላ ብትመጪ" እያለ የሚያባብለኝ። ጥበቡ ቀብሪደሃር ከእኔ ተለይቶ እንደሄደ ሁኔታውን በልቡ ሲያዳምጥ ትምርት ቤት እንደተዘጋ ኢያሱንና ሰይፉን ወደ እኔ ለመላክ ቢወስንም "ብቻህን ጥዬህ አልሄድም" ሲል እምቢ ስላለው ኢያሱ ከጥበቡ ጋር ቀርቷል። ዝርዝር ሁኔታው ግልጽ ባይሆንም ጥበቡ ቀብሪደሃር ከደረሰ ጊዜ አንስቶ በመንፈሱ "ወታደራዊ" ዓይነት ትጥቅና ዝግጅት ላይ የሚገኝ ንቁ ወታደር ይመስላል።ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ኢያሱንም ሆነ በዙሪያው ያሉትን ሌሎች ሰዎች ግራ እስኪያጋባ ድረስ አቤታችን የሚገኙትን የግል እቃዎቻችንና የእኔንና የእርሱን ልብሶች ሁሉ ሳይቀር በሻንጣ እየሞላ ጥበቡ ሲልክ ሰንብቷል። ለእኔ ምንም ፍንጭ ባይሰጠኝም፤ ትዳር የመሠረትንበትን የቀብሪደሃር ቤታችን፤ እንደ ቤተሰብ እንደገና እንደማንኖርበት ለእርሱ ግን የገባው ነገር አለ። እኔ በጊዜው አልገባኝም እንጂ ሲድራቅ ሚሳቅ አብድናጎን ከሚንበለበለው የእቶኑ እሳት የታደገ፤ ዳንኤልን ከተራቡት አንበሶች አፍ ያዳነ የእስራኤል አምላክ፤ መልእክቱን በሚፈሩት ዙሪያ የሚያሰፍረው የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን በደብዳቤዎቹ ገልጾልኛል።

ሰሞኑን ደግሞ ካለፉት ሁለት ወራት ለየትና ጠንከር ባለ ሁኔታ የሱማሌ ደፈጣ ተዋጊዎች የኢትዮጵያን ጦር ኃይል በሚፈታተን ዓይነት ሁኔታ ጠብ በመጫር ሽብር የሚፈጥሩ ኃይለኛ ፍንዳታዎች በቀብሪደሃር ዙሪያ ሲያሰሙ ቆይተዋል። ከተማዋ ቀን ላይ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሥር ትሁን እንጂ ወታደሮቻችን ላይ ከሚያደርሱት ጉዳትና ከሚጥሉት አደጋ የተነሳ የሌሊቱ ተቆጣጣሪዎች ሶማሌዎቹ መሆናቸው ግልጽ እየሆነ መጥቷል። በኢትዮጵያና በሶማሊያ ጦር ሠራዊቶች መሃል በሚካሄደው ፍልሚያም ከባባድ ቁስለኞችና ለሕክምና እርዳታ ወደ ሆስፒታሉ የሚመጡት ወታደሮቻችን ቁጥር ጨምሯል። ጥበቡ ቀንና ሌሊት የሚያደርገው ቀዶ ጥገናና ሌላ የሕክምና እርዳታ ፋታ አሳጥቶታል፤


የሆስፒታሉ አልጋዎች ሞልቶው ቁስለኞች መተኚያ ስፍራ እስኪያጡ ድረስ አንጀቱ በጦር ሜዳ ለተዘረገፈው እግርና እጁን አጥቶ ደሙ ለሚንዠቀዠቀው አፋጣኝ እርዳታ በመስጠት ያለዕረፍት ሲሯሯጥ የሚያስተውለው ሁሉ፣ ወጣቱ ሐኪም የራሱንም ነፍስ ሳያጣ በፍጥነት ወደ ሚስቱና ልጆቹ እንዲያመልጥ ልባዊ ምክሩን መለገስ ይቃጣዋል።

ጥበቡ ግን ለአፍታም ባይለየን ከሚወደን ከእኛ ርቆ በነበረበት በዚያን ወቅት የእኛን መሃል አገር መቆየት ወዶታል። ሆኖም በበኩሉ በጣርና በሰቃይ ላሉት በዚያ ስፍራ ተገኝቶ መርዳት በመቻሉ እርካታ ይሰማዋል። አምላኩ በሚፈልገው በትክክለኛው ስፍራ እንደሆነም ገብቶታል። በሥራ ውጥረት መሀል ለአፍታ ያህል የማሰቢያ ጊዜ ካገኘ የእኛ የጨቅላ ቤተሰቡ ናፍቆት ሽው ይልበታል። በጸሎቱ ሰዓት ሁሉን በዙፋኑ ሥር በመጣል ጥቂት እፎይታን ያገኛል እንጂ። ደግሞም ባለፈው ሰሞን አምላኬ ሆይ የዚሁ ሁሉ መጨረሻ ምንድነው ለሚለው ጸሎቱ እግዚአብሔር ያሳየው ራዕይ ትዝ ሲለው ይጽናናል። ሰሞኑን ግን በሥራ ብዛት ዝሎ ለጥቂት ሰዓትም ቢሆን ከነበረበት ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ጥበቡን የሚቀሰቀሱት በተለይ ሌሊት የሚሰማቸው ለከተማው እጅግ የቀረቡ ፍንዳታዎች ጥያቄ ፈጥረውበታል። ከኢትዮጵያ ሠራዊት የተሰጠ መግለጫ ባይኖርም በየሌሊቱ ከሚቀፍ ዓይነት ቅርበት የሚተኮሱ መሣሪያዎች ብዛት ራሳቸውን የቻሉ ልዩ መግለጫዎች ስለሆኑበት የሕዝቡ ሁሉ ልብ በታላቅ ጥያቄ ተሞልቷል።

****

*ለምን ትቶኝ ይሄዳል?*

ጥበቡ ወደ ቀብሪደሃር ከሄደ አንስቶ ያለሁት ናዝሬት ወላጆቼ ቤት ነው። ለመውለድ አዲስ አበባ ላለመሄድ ወስኜ ናዝሬት ኃይለማሪያም ማሞ ሆስፒታል የሐኪም ክትትሌን ጀምሬያለሁ።ሃሳቤንና ለመታረሻዬ የሚያስፈልገውን ቅደመ ዝግጅት ሁሉ በእነርሱ ላይ ጥዬ፤ በፍቅር በሚንከባከቡኝ ወላጆቼ ቤት የሁለተኛ ልጄን መውለድ በናፍቆት የምጠባበቅበት ወቅት ላይ ነኝ። አባቴ ምቹውንና ሰፊ አልጋውን ለእኔና ለእናቴ ትቶልን የምተኛው በወላጆቼ መኝታ ቤት ሆኗል።



ሕፃን ረቂቅ ጥበቡ በአንድ ወሯ

ሐሙስ ሐምሌ 14 ቀን 1969 ከጥበቡ ጋር በሬድዮ መገናኛ አማካይነት ተነጋገርን፤ እንደ ስልክ ያህል መደማመጡ ባያረካም ድምጹን በመስማቴ ደስ ብሎኛል። በማግስቱ ዓርብ ሌሊት ግን ያየሁት ሕልም አሳሰበኝ። ትርጉሙ በውል ባይገባኝም ጸሎት የሚያስፈልገው ነው አልኩና ለጥበቡ ላክፍለው ፈለግሁ። ቀኑን ሙሉ ሳስብበት ዋልኩና እንዴትና መቼ እንደሚደርስልኝ ባላውቅም ቅዳሜ ማታ አልጋዬ ላይ እያለሁ ደብዳቤ ልጽፍለት ጀመርኩ። በሕልሜ እኔና ጥበቡ በአንድ ቤት ውስጥ ሆነን

አያለሁ። ትምህርት ቤት ያለ ይመስለኛል። ገና ወደ ቤት ሲገባ ነው የምመለከተው። እቤት እንደገባ አንድ የቀረኝ ፈተና ስላለ እሱን ተፈትኜ እመጣለሁ ብሎኝ እኔን ትቶኝ እርቆ ሲሄድ አየሁት። ከዚህ ሕልም በኋላ ውስጤ በጥያቄ ተሞላ። የምን ትምህርት ቤት ነው? የምን ፈተና ነው? ለምን ትቶኝ ይሄዳል?

ሕልሙና ሁኔታው ውስጤን ይዞታል። ስለዚህም ነው ልቤ ዕረፍት ቢያገኝ ብዬ በዚያ ማታ ደብዳቤ ልጽፍለት የጀመርኩት። ደብዳቤዬ መሃል እንደደረስኩ ግን ወገቤን በጣም ተሰማኝ። ድካምም በእጅጉ ተጫጫነኝ። ስለዚህ ሲነጋ በማለዳ ደብዳቤዬን ለመጨረስ ወሰንኩና ከሃሳቤ ጋር ተሸፋፍኜ ተኛሁ። ጠዋት በማለዳ ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም ከእንቅልፌ ነቅቻለሁ። ያ ሕልምና ትርጓሜው ግን በውስጤ እየተብላላ በዚያች ማለዳ ሳላውቀው በሃሳብ ተመስጬያለሁ። ከገባሁበት ተመስጦ ድንገት በሚያባንን በ"ቶሎ ድረሽ" ጥሪ የመኝታ ቤቱ በር ተንኳኳ። በተደናገጠ ሁኔታ ምነው? ምን ሆናችሁ? ብል እቴሜቴ ታመዋል ፤ አይሰሙም አይለሙም ባስቸኳይ ሆስፒታል ቢወሰዱ ይሻላል አሉኝ።

የእናቴን እናት አያቴን እቴሜቴ እንላታለን መላ ቤተ ዘመዱ ። በዘመንዋ መልከ መልካም ዓይነ ትልልቅ ቆንጆ ነበረች። መጠሪያ ስምዋ ወ/ሮ አሰለፈች ደምሴ ይባላል። በባሕርይዋ ቆፍጣናና የምትፈራም ኃይለኛ ነበረች። ዛሬ ግን ኃይለኛነቷንና ማንነቷን በሚያዳክም ኃይለኛ የጉበት ካንሰር ተይዛ አልጋ ላይ ከዋለች ቀናቶች አልፈዋል። ለእንክብካቤ እንዲያመቻቸው የምትጦርበትን ቤት ወላጆቼ ግቢያቸው ውስጥ ሰርተውላት የምትኖረው ከቤተሰቦቼ ጋር ነው። የህመሟ ምንነት በሐኪም ከተነገረን ወዲያ ስለመዳን ወንጌል ለእኔንና ለእናቴ ጆሮ ከሰጠቼን ጥቂት ሰነባብቷል። ለዓመታት ስትቃወመን ከኖረች በኋላ መዳን በክርስቶስ ብቻ እንደሆ ገብቷት። ባለፈው ምሽት እንኳን የቤተሰብ ጸሎታችንን በአልጋዋ ዙሪያ አድርገናል። በዚያ ምሽት የእሷ ሃሳብ የጥበቡ ብቻውን መሆን ስለነበር እንድንጸልይለት የጸሎት ጥያቄ አቅርባለች። ዛሬ በዚህ ማለዳ ግን እንደበቷ አይናገርም። ጆሮዎቿም የምናደርግላትን ጥሪ አይሰሙም። ከገባችበት የሞት ጥላ እንቅልፍ ውስጥ ልናነቃት አልቻልንም። አባቴም ሆነ እናቴ ማለዳ የሚደርሱበት ለቅሶ ገጥሟቸው ከቤት የወጡት በጠዋት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ፈጣን እርምጃ መውሰድ የሚጠበቀው በጊዜው ከነበርኩት ከእኔ ነበርና ባስቸኳይ አፋፍሰን ወደ ሆስፒታል እንድንወስዳት አደረግሁ። የአያቴ የመጨረሻ ቀን እንደሆነ ውስጤ ገባው። ስለዚህ ዘመድ አዝማድ ከያለበት ስልክ ጥሪ እየተደረገለት ሆስፒታሉና የወላጆቼ ቤት በሰው ተሞልቷል።

እሁድ ሐምሌ 17 ቀን 1969 ዓ.ም እኔ ከጠዋት እንስቶ ቀኑን ሙሉ እለቱ ያመጣቸውን ዘመዶቻችንን ከማስተናገዱ ሌላ ትኩረት የሰጠሁት፣ እንደቤተሰብ ለአያቴ ልናደርገው ስለሚገባ የመጨረሻ እንክብካቤ ነበር። በማደርገው መሯሯጥና እንቅስቃሴ ቀንዋ የደረሰ ነፍሰጡር መሆኔንም የማስብያ ጊዜ አልነበረኝም።

ምሽት ላይ ከእራት በኋላ አያቴን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት ከአዲስ አበባ ለመጡት ዘመዶቻችን መኝታ አዘገጃጅተን አሳረፍናቸው። እኔና እህቶቼ ደግሞ ትንሽ እህል ለመቀማመስ ቁጭ ባልንበት ሆዴን ድንገት የሆነ ነገር ተሰማኝና ስደናገጥ ፊት ለፊቴ የተቀመጠችው ነርሷ እህቴ ተመለከተች። "ምን ሆነሽ? ምጥ ከሆነ ካሁኑ ተናገሪ ሰዓት እላፊው ከመግባቱ በፊት" ነበር ማስጠንቀቂያዋ እህቴ ሲ/ር አየለች። "ምጥ እንዲህ ቀላል ነው እንዴ? ኧረ እኔ ምንም የምጥ ምልክቱም የለኝ" አልኩ ከልቤ። ብቻ ለማንኛውም አዲስ ምላጭና ፈትል አዘጋጁልኝ ብላ ታናናሾቼን አዘዘች። እነርሱም የቀልድ እንጂ የምሯን እንዳልሆነ እየተናገሩ የተባሉትን አዘጋጅተው አስረከቧት።

"ታሾፋላችሁ እንዴ? !" አልኩ አሁንም ከልቤ በመገረም ።

ይሄን ተባብለን በቀኑ ውሎአችን እንደተመሰጥኩ ከእናቴና ከጥቂቶቹ ጋር ለመጸለይ ተንበረከክን። በጸሎት ላይ ሳለሁ ግን ድንገት የሆነ የግፊትና የምጥ ዓይነት ስሜት ተሰማኝ ! ! ሰውነቴ በላብ ተጥለቀለቀ።

"አይ! ጌታ ሆይ አይሁን! እያቴን ቆሜ ልሸኛት እባክህን!" ብዬ ለመንኩት። በቀን ውሎአችን ሁላችንም ተዳክመን ስነበር በተለይም የነገው ነገር ለእናቴ ከባድ እንደሚሆን አሰቤ፣ ጸሎታችንን ባጭር ደምድመን እሷን በቶሎ አስተኛኋትና ከጎኗ ጋደም አልኩ። የምጡ ግፊት ፍጥነቱ እየጨመረ መጣ። እንድታርፍ የተመኘሁላትን እናቴን በማደርገው እንቅስቃሴ ማስደንገጥ አልፈለግሁም። በቀስታ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባሁ። መቀመጥም ሆነ መራመድ የማያስችል ድንገተኛ ምጥ ያጣድፈኝ ገባ። አሁንም እናቴን ላለመቀስቀስ በጥንቃቄ ከመኝታ ቤት ወጥቼ እህቶቼ ወደ ሚገኙበት ሳሎን አመራሁ። አያቴን ለመሰናበት የተሰበሰቡት ዘመዶቻችን በየክፍሉ ተነጥፎላቸው ስለተኙ እህቶቼ በየሶፋው ላይ ለማረፍ ዝግጅት ላይ ናቸው። የሳሎኑን በር በዝግታ ከፍቼ ስገባ "ያልኩት አልቀረም፤ ምጥ ነው!" አለች ለመተኛት ፒጃማዋን በማጥለቅ ላይ የነበረችው እህቴ ሲ/ር አየለች።

የእህቶቼ ዓይኖች በድንጋጤ ፈጠጡ። ሰዓቱ እኩል ሰዓት ነው። ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል፤ የሰዓት እላፊው ከመጀመሩ በፊት ባስቸኳይ ሆስፒታል መወሰድ አለብኝ። አንደኛዋ እህቴ የእኔን ማረጋገጫ መጠበቅም አልፈለገችም አባቴን ከእንቅልፉ ለመቀስቀስ ወደ መኝታ ክፍሉ ስትሮጥ፤ የእነሱ መደናገጥ የባሰ አስደንግጦኝ ወደነበርኩበት መኝታ ቤት ለመመስ በቀስታ የጀመርኩትን እርምጃ እንዴት ልጨርሰው? የምጡ ግፊት እየጨመረ መጣ። መኝታ ቤት ስገባ እናቴ ከሽልብታዋ ነቃችና፣ "ምን ሆነሻል፤ አትተኚም እንዴ?" ስትለኝ፤ "ትንሽ ስላመመኝ ነው። ምጥ ነው መሰል" ነበር የእኔ በማመንታት የተሞላ መልስ። እናቴም በድንጋጤ ምነው ልጄ ቀደም ብለሽ ብትናገሪ እያለች ባስቸኳይ ከአልጋዋ ወረደች።

****

*የቀን ግጥምጥሞሽ!*

የሆስፒታል ካርዴን ያስቀመጠችበትን ስፍራ ለማስታወስ ትርበተበት ጀመር። እኔም እሷን ለማረጋጋትና ካርዱን ያኖረችበትን ለማመላከት ወደ እናቴ አንድ ሁለት እርምጃዎች እየተራመድኩ ሳለ የሽንት ውኃዬ በቁሜ መፍሰስ ስለጀመረ ሳላውቀው በድንጋጤ ጮህኩ ! የምታየውን ሁኔታዬን ማመን የተሳናት እናቴም ጩኸቴን ተቀበላ የ"ቶሎ ድረሱልን" ጥሪዋን በታላቅ ድምጽ አስተጋባቺው ! ነርሷ እህቴ በድምር በተቋረጠው አለባበሷ እንዳለች በሩጫ ከተፍ አለች። የሽርት ውኃው ፊሶ ወለሉ ተጥለቅልቋል። እኔም የሆነውን ማገናዘብ አቅቶኝ በድንጋጤ ወላጆቼ አልጋ አጠገብ ቆሜያለሁ፤ እህቴ ሲ/ር አየለች በቆመኩበት ስፍራ ብዙ ጊዜ መፍጀት እንደሌለብኝ አውቃ ባስቸኳይ አልጋው ላይ ውጪ፤ ባስቸኳይ አለቺኝ በተደነጋገጠ ድምጽ።

እህቴ ሲ/ር አየለች እንደዚያ መደንገጧ እኔንም አስደንግጦኛል። ብቻ ሁኔታውን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ "እሺ ቆይ! እየሉ ትንሽ መለስ ይበልልኝ" አልኳት። እህቴ ሲ/ር አየለች ግን አስቸኳይ እርምጃ በእኔ ላይ ባትወስድ በደቂቃዎች ውስጥ ሊከተል የሚችለው አሰቃቂ ሁኔታ ገብቷታል! የቆምኩበትና የሽርት ውኃዬ የተንጣለለበት ወለል ሲሚንቶ ነው። ከእኔ ጋር

ድርድር ለመግባት ጊዜ የላትም! ስለዚህ "የምን መለስ ይበልለኝ ነው! በየትኛው ጊዜ!" በማለት ስትጯጯህ የገባት ጭንቀት በመጠኑም ቢሆን ገባኝና የምትለኝን ሆንኩላት። በወላጆቼ አልጋ ላይ በጀርባዬ አሳረፈችኝ። ወዲያውኑ ከማንኛችንም ግምት ውጪ በሆነ ፈጣንና ያልተጠበቀ ዓይነት ቀላል ምጥ ሁለተኛዋን ልጄን በድንቅ ተገላገልኩ። ከምሽቱ ለአምስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ድንገት ማንም ሳይዘጋጅ ወደምድራዊው ዓለም የተቀላቀለችው የአራስ ህፃን ድምጽ በወላጆቼ ቤት ተስተጋባ። የቀን ውሏችንን የለወጠው ይህ ቅጽበታዊ ሁኔታ በመላው ቤተሰብ ያልተጠበቀ ደስታን ፈነጠቀ። ልብሱን ለባብሶ ሆስፒታል ሊወስደኝ ከመኝታ ቤቱ በር የደረሰው አባቴ ሴት ልጅ በድንቅ የመገላገሌ የም ሥራች ሲነገረው "ጎሽ ጎሽ! ልጄ አስተካከለችኝ! ይቺ የምትሸለም ነች" አለ። ወላጆቼ የወለዱት አምስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ስለነበርን በእኔ ሁለት ሴቶች መውለድ አባቴ "የጎደሉበትን" ሁለት ሴቶች የተጨመሩለት ያህል ቆጥሮት።

ምጡ ባጭር ጊዜ ውስጥ የተካሄደ በመሆኑ የተነሳ ነው መሰል ሰውነቴም ብርድ እንደገባው ያህል ይንዘፈዘፋል። እህቴ ሲ/ር አየለች የልጄን እትብት እንደቀልድ በተዘጋጀላት በዚያ ምላጭና ፈትል ቆርጣና አዘጋጅታ፤ሕጻኗን በእቅፌ ላይ አኖረቻት። ዓይኖቿ የሚያምሩ ንቁ ሕጻን! የእለቱን ውሎዬንና አጭር የነበረውን ምጤንና መደነጋገጥ ፈጽሞ የምታስረሳ! ከማንም ግምት ውጪ በሆነ ቅጽበታዊ አወላለድ የተወለደች! ከእኔና ከጥበቡ አብራክ የተገኘች ውብ ሁለተኟዋ የአምላካችን ስጦታ!

የኔ ውድ ጥበቡ! ዛሬም ሁለተኛዋን ልጃችንን በዓይኑ ለማየትም ሆነ አቅፎ ለመሳም አልበቃም ። እንደ እኔ ሃሳብና ፍላጎት ቢሆንማ፣ እሱ ባለበት እዚያው ቀብሪደሃር ራሱ እንዲያዋልደኝ አልነበር የፈለግሁት።ባልገመትነውና ባላቀድነው ሁኔታ ይቺ ሕጻን እዚህ እንድትወለድ የፈቀድህ አንተ ጌታ፤ አንተ በነገር ሁሉ ጻድቅ ነህ። ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ እንደቃልህ ለእኛ ለበጎ እንዲሆን አምናለሁ። የኔንና የጥበቡን ትዳር በዚች በምታምር ልጅ እንደገና ስለባረከው ግን ተመስገን።

በዚያው ሌሊት እያቴ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየችን። ውስጤን ፈንቅሎ በገነፈለ እንባ ዓይኖቼ ታጠቡ። ዘመኗን በመልካም ያጠናቀቀችው ከአምላኳዋ ጋር ታርቃ ወደ ሰማያዊ ዕረፍትና ደስታ የገባቺው የእያቴ ከእኛ መለየት እንዲያ የውስጥ የነፍስ ለቅሶ ሊያስለቅሰኝ እንደማይገባ ለራሴም ነገሬዋለሁ። ልቤ ግን መጽናናትን እንቢ ብሏል። የጥልቅ ኀዘን ካባ በላዬ ጠልቆ ውስጤን ያንቀሰቅሰዋል። ነፍሴ የሆነችውን ሆናለች። ዝርዝር ሁኔታው ግን በዓይኔ ፊት የተገለጠ አልነበረም፤ ያም ሆነ ይህ ሐምሌ 17 ቀን ከማለዳ አንስቶ የእያቴ ሁኔታ ባስከተለብኝ ድንጋጤና መሯሯጥ ላይቀጥል አምላኬ ልጄን በሰላም ገላግሎ አልጋ አስይዞኛል። በዘመኔ ይደርስብኛል ብዬ ያልጠበቅሁት ረዥምና አሳዛኝ የሕይወት ጎዳና በፊቴ መደቀኑን የሚያውቀው ጌታ እግዚአብሔር፤ በእለቱ በተረዳሁት መጠን በእኔና በሕጻኗ ሕይወት ላይ የነፍሳችን ጠላት ዲያብሎስ የጠነሰሰውን የሞት አደጋ አምላኬ ጣልቃ ገብቶ አክሽፎበታል። የአያቴንም ነፍስ ከሰይጣን መንጋጋ በክርስቶስ ወንጌል ነፃ አውጥቶ ጌታ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት የዘላለም ዕረፍት አስገብቷታል። ለሐምሌ 17 ቀን ዲያቢሎስ ያጠመደብንን ድርብ ድርብርብ ወጥመድ አምላካችን ሰባብሮልን ጥሶ አሳልፎናል። የኔ ጥበቡ ግን እንዴት ይሆን?

****